# ርዕስ ተኮር ጥናት

- የሥጋ ሥራ
- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬና
- መንፈሳዊ ውጊያ

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች ቤተክርስትያን
ዳላስ ቴክሳስ

## ለቤት ኅብረቶች የተዘጋጀ
## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

Ethiopian Evangelical Believers Church
Dallas, Texas

3001 Saturn Rd. Garland TX 75041 | 214.703.0100 | eebcdallas.org

## መቅድም

በቤተ ክርስቲያናችን የቤት ለቤት ህብረቶች የአገልግሎት ክፍል እቅድ መሰረት የ2024 ዓመት የሚኖረን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ርዕስ ተኮር ሲሆን ሦስት ንዑስ ክፍሎችን አካቷል። ክፍል አንድ እና ሁለት በገላትያ መልዕክት ምዕራፍ 5 ላይ ባሉት የሥጋ ስራ እና የመንፈስ ፍሬ ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን በአማኞች ህይወት ውስጥ በሥጋና በመንፈስ መካከል በሚደረግ ግጭት ላይ ያተኩራል። በዚህ ክፍል በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በመንፈስ ፍሬ ወይንም የሥጋን ሥራ የሚፈጽም ክርስቲያን የአኗኗር ዘይቤ ልዩነትን በንጽጽር እንድናጤን የሚያደርገን ይሆናል።

እንዲሁም ሦስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ በኤፌሶን መልዕክት ምዕራፍ 6 መሰረት መንፈሳዊ ዕቃ ጦርንና መንፈሳዊ ጦርነትን ያብራራል። የዝግጅት ክፍሉ ይህንን ርዕስ ተኮር ጥናት ሲያዘጋጅ እሳቤው ክርስቲያን ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ እየገደለ በአንጻሩም የመንፈስ ፍሬን እያፈራ የሰይጣንን ሽንገላም ለመቃወም መንፈሳዊ ዕቃ ጦርን ሁሉ አንስቶ መንፈሳዊ ጦርነት እየተዋጋ በድል መኖርን እንዲለማመድ ነው።

እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ይህንን ጥናት በማዘጋጀቱ ሂደት የተሳተፉትን፣ የጥናት ቡድን መሪዎችንና፣ እንዲሁም የጥናት ቡድኖቹን የሚያስተባብሩትን አገልጋዮችን ሁሉ ስለ ሚያሳዩት ትጋትና ታማኝነት የአግልግሎት ክፍሉ እግዚአብሔር እንደ ባለጠግነቱ መጠን በነገር ሁሉ ይባርካችሁ ማለት ይፈልጋል። እንዲሁም በጥናት ቡድኖቹ የሚሳተፉትን ቅዱሳንን ሁሉ በምንጀምረው በዚህ ጥናት በእግዚአብሔር ቃል እውቀት

የምታድጉበት፣ ብዙ መንፈሳዊ ጸጋን የምትቀበሉ፣ የምትለወጡበትና፣ የምታፈሩበት እንዲሆን ጸሎታችንና የልብ ምኞታችን መሆኑን መግለጽ እንወዳለን። በመጨረሻም የቤተ ክርስቲያናችን መሪዎችና አገልጋዮች ለእግዚአብሔር ቃል ጥናት ስላላቸው መሰጠትና በምሳሌነት ስለሚያሳዩን ትጋት እግዚአብሔር ይባርካችሁ እንላለን።

ከአግልግሎት ክፍሉ!

## **ንዑስ ርዕስ ሁለት:-** ለወንጌል መሥፋፋት መጸለይ

## **የሥጋ ሥራዎች - የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ**

## **በገላትያ 5፥16-26 ላይ የተመሠረተ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

### **መግቢያ**

ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ ይኖሩ ለነበሩት ምዕመናን በጻፈው መልእክቱ አጽንዖት ከሰጠባቸው ተግባራዊ ምክሮች ውስጥ አንዱ በክርስቶስ በማመን የዘላለም ድነትን ያገኙ ሁሉ በመንፈስ እንዲመላለሱና የሥጋን ምኞት እንዳይፈጽሙ ማሳሰብ ነው። በገላ. 5፥16-26 ላይ እንደምንመለከተው "ሥጋዊ" እና "መንፈሳዊ" ተብለው በተቃርኖ የተቀመጡ ሁለት የሕይወት መርሆዎች አሉ። ሁለቱም የሕይወትን አቅጣጫዎች የሚወስኑና የየዕለት አኗኗርን የሚቃኙ መርሆዎች ሲሆኑ በክርስቶስ የዳኑ አማኞች በሥጋ ፈቃድ ሳይሆን በመንፈስ እንዲመላለሱ ብሎም ፍሬያማ ሕይወትን እንዲያጎለብቱ የማያሻማ ጥሪ ቀርቦላቸዋል።

ይህ ጥናት በተጠቀሰው የገላትያ ምዕራፍ 5 ምንባብ ውስጥ የተነሱትን አሳቦች በዝርዝር የምንቃኝበት ይሆናል። ምንም እንኳን አማኞች በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ቢሆኑም በመንፈስና በሥጋ መካከል የማያቋርጥ ግብግብ እንዳለ ልብ ማለት አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ጥናቱ በክርስቶስ የሚኖሩ አማኞች ሥጋዊነትን ለማሸነፍና በመንፈስ የመመላለስን ልምምድ ለማዳበር እንዲችሉ እገዛን ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

መልእክቱ በገላትያ የሚኖሩ አማኞች የሙሴ ሕግጋትን መጠበቅ በክርስቶስ ከማመን በተጨማሪ ለዘላለም ድነት አስፈላጊ ነው ብለው ከሚያስተምሩ አይሁዳዊ ሐሰተኛ መምህራንና ከትምህርታቸው እንዲጠበቁ የተጻፈ እንደመሆኑ መጠን በሥጋዊነትና በመንፈስ በመመላለስ መካከል ያለውን ትግል በዚህ ዐውድ ውስጥ መረዳት አስፈላጊ ይሆናል። ስለሆነም አማኞች የሥጋ ሥራዎችን እንዳይፈጽሙና በተቃራኒው ግን የመንፈስ ፍሬን እንዲያፈሩ ይህ ክፍል የሚመክራቸው ድነትን ከማግኘት አንጻር ሳይሆን የዳኑ አማኞች በመሆናቸው መሆኑ ሁሌም አጽንዖት ሊሰጠው ይገባል።

በዚህ ጥናት በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚኖረውን ያልተቋረጠ የመንፈሳዊና ሥጋዊ ህይወት ትግልን እንመለከታለን። ይህንንም በአግባቡ ለመረዳት ጳውሎስ በምሳሌነት የዘረዘራቸውን **<u>አሥራ ስድስት</u>** የሥጋ ሥራዎች እንዲሁም **<u>ዘጠኙ የመንፈስ ፍሬን</u>** በአትኩሮት ለመገንዘብ ጥረት እናደርጋለን። በዚህም መሠረት ምንባቡ እንደሚያስተምረን የክርስቶስ የሆንን ሁላችን ሥጋንና መሻቱን በመስቀልና በመንፈስ በመመላለስ ፍሬያማ የሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችለንን መለኮታዊ መርህ የምንማርበት ጥናት ይሆናል።

ከዚህ በታች የቀረቡት ጥናቶች **<u>በሁለት ክፍል የተከፈሉ</u>** ሲሆኑ በክፍል አንድ <u>"የሥጋ ሥራዎች"</u> በመዘርዘር በስድስት ጥናቶች እንዲሁም በክፍል ሁለት "የመንፈስ ፍሬን" በመዘርዘር በአምስት ጥናቶች የመግቢያ ጥናቱን ጨምሮ በጥቅሉ አሥራ ሁለት ጥናቶች ናቸው።

## የመግቢያ ጥናት

## አጠቃላይ ዳሰሳ፡- በመንፈስ መመላለስ

## ገላትያ 5፥16-26

**ዓላማ፡-** አማኞች በመንፈስ በመመላለስ የሥጋን ምኞትን አለመፈጸምንና ፍሬያማ መሆንን የሕይወታቸው መርህ አድርገው እንዲኖሩ ለማሳሰብ

**መግቢያ፡- በገላትያ 5፥16-26** የሚገኘው ምንባብ ዋነኛ ትኩረት በመንፈስ መመላለስ ነው። በክርስቶስ በማመን የዘላለም ድነትን ያገኙ ሁሉ በመንፈስ እንዲመላለሱ፤ ከዚህም የተነሳ የሥጋን ምኞት እንዳይፈጽሙ የሚያሳስብ ክፍል ነው። በምንባቡ አስተምህሮ መሠረት ከሕግ በታች በመሆን ወይም ሕግን ለመፈጸም ጥረት በማድረግ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ በመመራትና ራስን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠት ከሥጋ ሥራዎች ድርጊት መራቅና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ፍሬያማ ሕይወትን ማጎልበት የክርስቲያናዊ አኗኗር ዋነኛ መርህ

ነው። በዚህ የመግቢያ ጥናት ይህ የምንባብ ክፍል በመንፈስ በመመላለስ ፍሬያማ ሕይወትን ስለ መኖር የሚናገረውን አጠቃላይ አሳብ በዳሰሳ መልክ እንመለከታለን።

**<u>አጭር ትንታኔ</u>**

የገላትያ መልእክት አንኳር አስተምህሮ አማኞች በክርስቶስ ጸጋ የተጠሩበትን እንዲሁም በሥራ ሳይሆን በእምነት የጸደቁበትን የእውነት ወንጌል አጥብቀው እንዲይዙና በእምነታቸው ሳይናወጡ ጸንተው እንዲቆሙ ማሳሰብ ነው። ደህንነትና ጽድቅ በሕግ ሥራ የሚገኝ አለመሆኑን፤ ነገር ግን ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን በመስቀል ላይ ከመሞቱ የተነሳ የሰው ልጆች ሁሉ "ከእምነት ጋር በሆነ መስማትና መታዘዝ" ብቻ በመንፈስ ቅዱስ የሚቀበሉት የዘላለም ሕይወት እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልእክት ላይ አጽንዖት ሰጥቶ ያስተምራል (ገላ. 2፥15-21፣ ገላ. 3፥2)። እንዲሁም በእግዚአብሔር ልጅ ላይ እምነታቸውን ያደረጉ ሁሉ ከሕግ የባርነት ቀንበር ፈጽመው አርነት የወጡ መሆናቸውን በተለያየ መልኩ ያስረዳል (4፥9፣ 5፥1)።

በሌላ በኩል ይህ መልእክት ክርስቲያኖች የተቀበሉት ነጻነት በአንዳንዶች ዘንድ እንደሚታሰበው ለሥጋዊነት ወይም ሥጋዊ ምኞቶችን ለመፈጸሚያ ሰበብ እንዳይሆን ግልጽ መመሪያዎችን የሚሰጥ ነው። በተለይ በምዕራፍ 5 ላይ የምንመለከተው አሳብ ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ አማኞች "ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋል፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ" (ገላ. 5፥13) በማለት ምንም እንኳን ከሕግ በታች አለመሆናቸውን ቢያሠምርበትም ሕጉ ቅዱስ ነውና ኑሮአቸውና አካሄዳቸው ሥጋዊነትን የሚያንጸባርቅ ሳይሆን በመንፈሳዊ ፍሬዎች የተሞላ እንዲሆን ይመክራቸዋል። ለዚህም ዓይነተኛው መንገድ ***በመንፈስ የመመላለስ መርህ*** ነው፡- "ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ . . . በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ (ገላ. 5፥16፣ 25)።

**<u>በመንፈስ መመላለስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መራመድ ወይም ራስን ለመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ማስገዛት/አሳልፎ መስጠት ሲሆን በአስተሳሰብ፣ በቃልና በሥራ የእርሱን ምሪት ብቻ መከተል እንዲሁም በእኛ ላይ ተጽዕኖውን እንዲያሳድር መፍቀድ ማለት ነው።</u> "መመላለስ"** የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአንድ ጊዜ ድርጊትን ሳይሆን የዘወትር ወይም የዕለት ተዕለት ተግባራዊ አኗኗርን ነው። አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናቸው በውስጣቸው መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸዋል፤ በውስጣቸው ያደረውን መንፈስ በየዕለቱ ሊሰሙትና ሊከተሉትም ያስፈልጋቸዋል (ሮሜ 8፥14፣ ገላ. 5፥18)።

ታዲያ በውስጣችን በሚያድረው መንፈስና በሥጋዊው ማንነታችን መካከል የዘወትር ግብግብ እንዳለ መረዳት ያስፈልጋል። ለዚህም መሰረታዊ ምክንያቱ መንፈስ በስጋ ላይ ስጋም በመንፈስ ላይ የሚቃወም በመሆኑ ነው። ስለዚህም "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ" (ገላ. 5፥ 24) እንደሚል ዘወትር የሥጋ ምኞታችንን በማሸነፍና በመግራት ፈቃዱንም እንዳያደርግ በመከልከል በተቃራኒው ግን የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ እየፈጸምንና መንፈሳዊ ፍሬን እያፈራን እንድንኖር ያስፈልገናል። ይህም በመንፈስ የመመላለስ ሕይወት በቀጣዮቹ ጥናቶች እንደምንመለከተው በገላ. 5፥19-21 ላይ የተዘረዘሩትን የሥጋ ሥራዎች እና መሠሎቻቸውን ባለማድረግ እንዲሁም በገላ 5፥ 22-23 ላይ የተጠቀሱትን የመንፈስ ፍሬዎች ለማድረግ በመትጋት የሚገለጥ ሕይወት ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በገላ. 3፥13፣ 4፥4-5፣ 31፣ 5፥1፣ 13 መሰረት በክርስቶስ በማመን የጸደቁ አማኞች ከሕግ የባርነት ቀንበር ፈጽመው አርነት የወጡ ናቸው ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. በገላ. 5፥13 ሐዋርያው ጳውሎስ "ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋል፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ" ሲል ለገላትያ ሰዎች ምን እያላቸው ነው?
3. በገላ. 3፥3 ላይ "በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን?"የሚለውን የጳውሎስ ጥያቄ ከክፍሉ ዐውድ አንጻር ከምን ጋር የተያያዘና ለምንስ የተጠየቀ ይመስልሃል/ሻል?
4. በገላ. 5፥16-19 እና በሮሜ 8፥1-9 መሠረት በመንፈስ መመላለስ ምን ማለት ነው? የምትረዱትን ተወያዩበት።
5. በገላ. 5፥17 ላይ ባለው ጥቅስ መሰረት በሥጋና በመንፈስ መካከል በውስጣችን ያለው ግልጽ ጦርነት መነሻ ምክንያቱ ምንድነው? በጦርነቱ ማን ማሸነፍ ይኖርበታል? ስለዚህ ምን ማድረግ ይኖርብሃል/ሻል?
6. ገላ. 5፥17 ከሮሜ 7፥15 ጋር በማነጻጸር እነዚህ ሁለት ጥቅሶች በተጻፉበት ዐውድ መሠረት ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩበት።
7. በገላ. 5፥21 ላይ የሥጋ ሥራዎችን ከዘረዘረ በኋላ "እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም" ይላል። ይህ ምን ማለት ይመስልሃል/ሻል?
8. በገላ 5፥23 ላይ ከመንፈስ ፍሬዎች ዘርዝሮ በማስከተል "እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም" ይላል። ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል/ሻል?

9. ገላ. 5፥24 ከሮሜ 8፡13 እና ቆላ 3፡5 በማንበብ *ሥጋን* ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር መስቀል በተግባራዊ ሕይወታችን ምን ሊመስል እንደሚችል ተወያዩበት።
10. ከዛሬው ጥናት ሃሳብ "በመንፈስ መመላለስን በተመለከተ፡ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ተግባራዊ ልናደርግ የምንችልባቸውን መንገዶች በግል የቀረላችሁን አካፍሉና በጸሎት ደምድሙት።

***<u>መደምደሚያ</u>***

"እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ *ሥጋ* ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለ*ሥጋ* አይደለም። እንደ *ሥጋ* ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ ***በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ*** ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።" ሮሜ 8፥12-12 (አ.መ.ት.)

እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ። ***በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።*** ሞታችኋልና፥ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና። ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ።" ቆላ. 3፥1-4 (አ.መ.ት.)

## **ክፍል አንድ፡-** *የሥጋ ሥራዎች*

## **ጥናት አንድ**

**የንባብ ክፍል፡-** *ገላትያ 5፥19*

**ርዕስ፡-** *ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት*

**ዓላማ፡-** *አማኞች በመንፈስ እንዲመላለሱ የተጠሩ በመሆናቸው የሥጋ ሥራ ተብለው ከሚታወቁት ዝሙት፣ ርኵስትና፣ መዳራት ልምምዶች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማሳሰብ*

***መግቢያ፡-*** *እግዚአብሔር የወሲብን ፍላጎት በሰው ልጆች ውስጥ የፈጠረበት ዋነኛ ምክንያት በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል በተቀደሰ ሕጋዊ ጋብቻ ውስጥ ለእውነተኛ የፆታ ፍቅር መገለጫና ለትውልድ ቀጣይነት አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዲኖረው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሳችን አበክሮ ያስተምረናል (ዘፍ. 1፥28፣ 2፥24)። ከዚህ የእግዚአብሔር ዕቅድና ማዕቀፍ ውጪ የሚደረግ ማንኛውም የፍትወት አሳብም ሆነ ድርጊት ጽዩፍና ግልጽ ኃጢአት መሆኑንም ጨምሮ ይነግረናል (ዘጸ. 20፥14፣ ማቴ. 5፥32፣ 15፥19)። በዚህ ጥናታችን በገላትያ ውስጥ ከተዘረዘሩት የሥጋ ሥራዎች በቀዳሚነት ዝሙት፣ ርኵሰትና መዳራት ተብለው የተጠቀሱትን ሦስት ድርጊቶች በዝርዝር እንመለከታለን።*

### **<u>አጭር ትንታኔ</u>**

*ዝሙት፣ ርኵሰትና መዳራት ተብለው የሚታወቁት ድርጊቶች በየዘመናቱ በየትኛውም ባህል ውስጥ የሚታዩ በመሆናቸው ብዙም ማብራሪያ የማያሻቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይም ደግሞ አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ወቅት በስፋት በተንሠራፋው የግሪክና የሮም ባህል ውስጥ እጅግ የተለመዱ ማኅበራዊ ክስተቶች ከመሆናቸው ባሻገር ሃይማኖታዊ ይዘትም ነበራቸው። እነዚህ ምግባራት በእግዚአብሔር ዐይን አስጸያፊ ከመሆናቸውም በላይ አማኞች በከበረ ዋጋ መገዛታቸውን የሚያቃልሉ የሥጋ ሥራዎች ናቸው። በመሆኑም የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን እነዚህ ድርጊቶች ኀጢአት መሆናቸውን በማሳየትና በማውገዝ ከድርጊቶቹ መታቀብ ክርስትና ከሚጠይቃቸው ተግባራዊ*

የሕይወት ልምምዶች ዋነኛው መሆኑን አጽንዖት በመስጠት በትጋት ያስተማረችበት ጉዳይ ነበር።

**"ዝሙት"** የሚለው ቃል የግሪክ *ፎርኔያ* ፥ የእንግሊዝኛው (አደልተርይ adultery/sexual immorality) አቻ ፍቺ ሲሆን በጥቅል ትርጉሙም ከቃል-ኪዳን ጋብቻ ውጪ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ማለት ነው (1ቆሮ. 5፥1፣ 6፥13-18፣ 1ተሰ. 4፥3-8)። በተለይ 1ቆሮ. 6፥18 እንዲህ ይላል፡- "ከዝሙት ሽሹ፤ ሰው የሚያደርገው ኀጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጪ ነው፤ ዝሙት የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኀጢአት ይሠራል።" ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 5፥32 ላይ የዝሙት ኀጢአት በሁለት ባለ ትዳሮች መካከል አብሮ የመኖርን ህልውና አደጋ ላይ እስከሚጥል ድረስ የከፋ ተግባር መሆኑን በግልጽ አስተምሯል።

**"ርኵሰት"** የሚለው ቃል የግሪኩ *አካታርሲያ*፥ የእንግሊዝኛው (እምፑውሪትይ impurity) አቻ ፍቺ ነው። በንግግር፣ በአሳብና በድርጊት የሚንጸባረቅ ዕድፈት ወይም ንጽህና የጎደለው፤ ተገቢ ያልሆነ ፍትወታዊ ባህሪይን ወይም ድርጊትን የሚያሳይ ቃል ነው። በአዲስ ኪዳን መልእክቶች በአብዛኛው ከዝሙት ጋር በተያያዘ የሚጠቀስ ቃል ነው (ሮሜ 6፥19፣ 2ቆሮ. 12፥21፣ ኤፌ. 5፥3፣ ቆላ. 3፥5፣ 1ተሰ. 4፥7)።

**"መዳራት"** በዚህ ክፍል ውስጥ ከተጠቀሱት የፍትወት ድርጊቶች ሦስተኛው **"መዳራት"** ነው። "መዳራት" የሚለው ቃል የግሪኩ *አሴልጊያ* የእንግሊዘኛው (sensuality ወይም licentiousness) አቻ ፍቺ ነው። የተለያዩ የአማርኛ መዝገበ ቃላት እንደሚያሳዩት "መዳራት" የሚለው ቃል መላፋት፣ መቃበጥ፣ መቆናጠጥ ወይም የተለያዩ ወደ ዝሙት የሚያመሩ ሥነ-ምግባር የጎደላቸው ልቅና ሴሰኛ ድርጊቶችን ማድረግን ያጠቃልላል (ሮሜ 13፥13፣ 1ጴጥ. 4፥3)።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በማር. 7፥20-23 ከተዘረዘሩት መካከል ዝሙትና መዳራት ይገኙበታል። በክፍሉ የተጠቀሱት የሥጋ ሥራዎች ምንጫቸውና ውጤታቸው ምን እንደ ሆነ ተወያዩባቸው።
2. በ1ቆሮ. 6፥13-17 መሠረት አማኝ ከዝሙት መሸሽ የሚኖርበት በምን ምክንያት ነው? በስፋት በዝርዝር ተነጋገሩበት
3. 1ተሰ. 4፥3-8 ዝሙትንና ርኵሰትን በተመለከተ እንደ አማኝ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ኑሮ መኖር የምንችለው ምን ስናውቅና እንዴት ስንኖር ነው?
4. በኤፌ. 4:17-19 መሰረት አሕዛብ በርኵስት የሚኖሩት ከምን የተነሳ ነው ይለናል? ይህ ክፍል ስለ አሕዛብ ኑሮ የሚናገርበት ምክንያት ምንድን ነው?
5. በ2ቆሮ. 12፥21 ሐዋርያው ጳውሎስ "እንዳላዝን" (አ.መ.ት.) በማለት የሚያነሳው ጉዳይ ምንድን ነው? ከንግግሩ ምን እንማራለን?
6. በ2ጴጥ. 2፥7 ሎጥ ይኖርበት የነበረው ማኅበረሰብ እንዴት ተገልጿል? እኛ ስለምንኖርበት ዘመንና ማኅበረሰብስ ምን ያሳየናል? ምን እንማራለን?
7. በማቴ. 5፥27-28 ላይ ኢየሱስ ከማመንዘር ጋር በተገናኘ የተናገረው ምንድን ነው? ተወያዩበት።
8. በዛሬው ጥናት መሰረት የሥጋ ሥራዎች አንጻር ሕይወታችንን በመፈተሽ፤ የንስሃ ጊዜ እንውሰድ። የጌታን ጸጋ ለኑሮችን እንለምን።

## መደምደሚያ

"በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፤ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንዴት መኖር እንደሚገባችሁ አስተምረናችኋል፤ በርግጥም እንደዚያው እየኖራችሁ ነው። ስለሆነም በጌታ በኢየሱስ የምንለምናችሁና የምንመክራችሁ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ በዚሁ እንድትገፉበት ነው። በጌታ በኢየሱስ ሥልጣን ምን ዐይነት ትእዛዝ እንደ ሰጠናችሁ ታውቃላችሁ። የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት ርቃችሁ እንድትቀደሱ ነው፤ ደግሞም እያንዳንዱ የገዛ

ሰውነቱን በቅድስናና በክብር መያዝ እንዳለበት እንዲያውቅ ነው፤ ይህም እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወተ ሥጋ ምኞት አይሁን። በዚህም ነገር ማንም ተላልፎ ወንድሙን አያታልል፤ ምክንያቱም ከዚህ በፊት እንደ ነገርናችሁና እንዳስጠነቀቅናችሁ ጌታ እንደ እነዚህ ያለውን ኀጢአት ሁሉ የሚፈጽሙትን ይበቀላል፤ እግዚአብሔር በቅድስና እንድንመላለስ እንጂ ለርኩሰት አልጠራንምና። እንግዲህ ይህን ምክር ንቆ የማይቀበል፣ የናቀው ቅዱስ መንፈሱን የሰጣችሁን እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም።" 1ተሰ. 4፥1-8 (አ.መ.ት.)

## ጥናት ሁለት

**የንባብ ክፍል፡-** ገላትያ 5፥20

**ርዕስ፡-** ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት

**ዓላማ፡-** በመንፈስ የመመላለስ ሕይወት ከባዕድ አምልኮ ተጽዕኖና ከክፉ መናፍስት አሠራር ፈጽሞ በመቃረን የሚመራ መሆኑን ለማስታወስ

**መግቢያ፡-** እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሰጣቸው አሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ሌሎች አማልክትን እንዳያመልኩ ወይም ምንም ዓይነት ጣዖት እንዳይኖራቸው እንዳዘዛቸው እናስታውሳለን (ዘጸ. 20፥2-5)። ይህም እግዚአብሔር ብቻ አምላክ መሆኑንና ሕዝቡ እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ በየትኛውም ዘመን የማይለወጥ የጸና አቋሙ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምረናል። እንዲሁም የጣዖት አምልኮ ከክፉ መናፍስት አሠራር ጋር የተያያዘ መሆኑን እናስተውላለን። ይህንን መሠረት ባደረገ መልኩ ክርስቲያኖች ይህንን የሕይወት ዘይቤ በመከተል ጣዖትን ከማምለክ እንዲሁም ከክፉ መናፍስት አሠራር የጸዳ ሕይወት እንዲኖሩ አዲሱ ኪዳንም ያስተምረናል። ጳውሎስ በገላትያ 5፥20 ከጠቀሳቸው የሥጋ ሥራዎች ውስጥ ጣዖትን ማምለክና ሟርትን በዚህ ጥናታችን እንመለከታለን።

### <u>አጭር ትንታኔ</u>

ይህ መልእክት የተጻፈላቸው የገላትያ ምዕመናን በዘመኑ ወደ ክርስትና እምነት እንደተመለሱት አሕዛብ ሁሉ በቀደመው ሕይወታቸው ከባዕድ አምልኮ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት የነበራቸው አማኞች ነበሩ። ይህም የባዕድ አምልኮ ከክፉ መናፍስት ጋር

የተገናኘና በርካታ ጣዖታት የሚመለኩበት የአሕዛብ የሃይማኖት ሥርዓት እንደነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምሩናል። በዚህ ክፍል ላይ ጣዖትን ማምለክና ሟርት ተብለው የተጠቀሱት ድርጊቶች የሥጋ ሥራዎች ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ ከአሕዛብ የሃይማኖት ሥርዓት ጋር በተያያዘ የሚታዩ ናቸው።

**"ጣዖትን ማምለክ"** በግሪኩ *ኢዶላትሪያ* ወይም በእንግሊዝኛው (አይዶለትርይ Idolatry) ማለት ሲሆን ከእውነተኛ አምላክ ከእግዚአብሔር ውጪ የሚደረግ ማንኛውንም አምልኮ የሚያመለክት ቃል ነው። ምንም እንኳን በቀጥታ *ኢዶላትሪያ*ወይም የጣዖት አምልኮ በሚል የተጠቀሱት የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ውስን ቢሆኑም (ለምሳሌ፡- 1ቆሮ. 10፥14-22፣ ቆላ. 3፥5፣ 1ጴጥ. 4፥3) አሳቡ በስፋት በአዲስ ኪዳናችን ውስጥ የሰው ልጆች እግዚአብሔርን ከመከተል ውጪ የሚያደርጉትን ኀጢአተኛ የአኗኗር ዘይቤ ያንጸባርቃል (ሮሜ. 1፥18-32፣ 1ቆሮ. 5፥10፣ 11፣ 6፥9፣ 10፥7፣ ራእይ 21፥8፣ 22፥ 15)።

**"ሟርት"** ለሚለው የግሪኩ ይሁም የላትኑ (Latin) ተመሳሳይ በኩረ ቃል "*ፋርማኪያ* "የሚል ነው። የእንግሊዝኛው "ፋርማሲ" ለሕክምና የሚሆኑ መድኃኒቶችን ከመቀመም ጋር የተገናኘው ቃል የመጣው ከዚህ መሆኑን ልብ ይሏል። ነገር ግን በግሪኩ ቃል የተጠቀሰው አሳብ አሉታዊና ሰዎችን ለመግደል መርዝን ከመቀመም ጋር የተገናኘ ነው። በእንግሊዝኛው አዲስ ኪዳን ይህ ቃል witchcraft ወይም sorcery ተብሎ ተተርጉሟል። እንዲሁም በሌሎች የአማርኛ ትርጉሞች "ሥራይ ማድረግ" ወይም "አስማት" ወይም "መተት" ተብሎ እንደተተረጎመ እንመለከታለን (ዘጸ. 7፥11፣ 22፣ 8፥ 3፣ 14፣ ኢሳ. 47፥9፣ ራእይ 18፥23)።

## ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በ1ቆሮ. 10፥14-22 መሠረት በቆሮንቶስ የነበሩት አማኞች ምን ስለሚያደርጉ ነበር “ከጣዖት ሽሹ” የሚል ትእዛዝ የተጻፈላቸው?
2. በ1ቆሮ. 10፥20 ጣዖት አምልኮ ከማን ጋር ተጣምሮል? ለቆሮንቶስ አማኞች የቀረበው የመሞገቻ ሃሳብ ምን ነበር?
3. ቈላ. 3፥5 ጣዖት አምልኮን ከምን ጋር ያዛምደዋል? እንዴትስ ይተረጉመዋል? እንዲህ ያለው ተዛምዶ ወይም ፍቺ ስለ ጣዖት አምልኮ ካለን ግንዛቤ ጋር እንዴት ይነጻጸራል?
4. በ1ጴጥ. 4፥3 ላይ “አጸያፊ የጣዖት አምልኮ” እና ሌሎች የሥጋ ሥራዎች ተዘርዝረዋል። በዚሁ ምዕራፍ ከቁ. 2-5 ያለውን ክፍል በአዲሱ መደበኛ ትርጉም (በአ.መ.ት.) የአሕዛብን ኑሮ እንዴት ባለ መልኩ እንደገለጸው በማስተዋል ለአማኞች የሚሰጠውን ምክር በስፋት ተወያዩበት።
5. በ2ዜና 33፥6 ላይ የተዘረዘሩት የአመጻ ውጤት ምንድን ናቸው?
6. በዘዳ. 4፥15-18 መሰረት እስራኤላውያን እንዳያደርጉ የታዘዙት ምን ነበር? ለምንስ እንዳያደርጉ ታዘዙ?
7. ኢሳ. 44፥9-20 ስለ ጣዖት፣ ስለ አምላኪዎቹና፣ ስለ ቀራጺዎች ቃሉ የሚለውን ተወያዩ።
8. ከዚህ ጥናት ምን ቀረልን? ዛሬ በሕይወታችን እንደጣዖት የሆነብን ነገር ይኖር ይሆን? በጸሎት እራሳችንን እንመርምር።

## ***መደምደሚያ***

“እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን ስለ ተቀበለ እናንተም በዚሁ ዐላማ ታጥቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው መከራን የሚቀበል ሰው ኀጢአትን ትቷል። ከዚህም የተነሣ ከእንግዲህ በሚቀረው ምድራዊ ሕይወት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ምኞት አይኖርም። አሕዛብ ፈቅደው እንደሚያደርጉት በመዳራት፣ በሥጋዊ ምኞት፣ በስካር፣ በጭፈራ፣ ያለ ልክ በመጠጣት፣ ***በአጸያፊ የጣዖት አምልኮ*** የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃል። ይህን በመሰለ ብኩን ሕይወት ከእነርሱ ጋር ስለማትሮጡ እንግዳ ሆኖባቸው በመደነቅ ይሰድቧችኋል። ነገር ግን በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ለተዘጋጀው መልስ ይሰጣሉ።” 1ጴጥ. 4:1-5 (አ.መ.ት.)

## ጥናት ሦስት

**የንባብ ክፍል፡-** ገላትያ 5፥20

**ርዕስ፡-** ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቍጣ

**ዓላማ፡-** ከሌሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናትና ቍጣ ለእውነተኛ መንፈሳዊነት ትልቅ እንቅፋት መሆናቸውን ለማሳየት

**መግቢያ፡-** መልካም ተግባቦትና ፍቅር የሰው ልጆች ሁሉ በተለይም ደግሞ ክርስቲያኖች እንደ ማኅበረሰብ ይኖሩ ዘንድ አስፈላጊ ከሆኑት ዋና ግብዓቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናትና ቍጣ ለዚህ ዓይነቱ አኗኗር ጠር መሆናቸው እሙን ነው። በዚህ ምንባብ ላይ እንደምንመለከተው እነዚህ ድርጊቶች በገላትያ ውስጥ ከተዘረዘሩት የሥጋ ሥራዎች አራቱ በመሆን ተጠቅሰዋል። ይህ ጥናት በክፍሉ የተጠቀሱትን እነዚህን የሥጋ ሥራዎች በዝርዝር የሚዳስስ ይሆናል።

<u>**አጭር ትንታኔ**</u>

በገላትያ መልዕክት ውስጥ የተዘረዘሩት የሥጋ ሥራዎች ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋርም ሆነ እርስ በእርሳቸው ሊኖራቸው የሚገባውን ጤናማ ግንኙነት የሚጎዱ የኀጢአት ድርጊቶች ናቸው። በዚህ ጥናት የምንመለከታቸው ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናትና ቍጣም በሰዎች መካከል መልካም የሆነ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዳይፈጠር ብሎም እንዳይጎለብት አሉታዊ ተጽዕኖን የሚፈጥሩ በተለይም ደግሞ መንፈሳዊውን ሕይወትና የቅዱሳንን ሕብረት የሚያበላሹ ጎጂ ልምምዶች ናቸው። እነዚህ የሥጋ ሥራዎች ከስሜት ጋር የተያያዙና በአግባቡና በጊዜው እርምት ካልተደረገባቸው ሰላምንና አንድነትን በማወክ ብልሹ ግንኙነቶችንና አላስፈላጊ ግጭቶች እንዲፈጠሩ ዓይነተኛ ግብዓት ይሆናሉ።

**"ጥል"**፣ **"ጥላቻ"፡-** በዚህ ክፍል በተለያዩ የአማርኛ ትርጉሞች **"ጥል"**፣ **"ጥላቻ"** ወይም **"ጠላትነት"** በመባል የተጠቀሰው አሳብ የሚያመለክተው አንድ ሰው ለሌላ ሰው ወይም ሰዎች ሊኖረው የሚችለውን የጥላቻ ስሜትና ያንንም ተከትሎ የሚፈጠረውን የግንኙነት መሰበር ወይም መበላሸት ነው። የግሪኩ በኩረ ቃል *ሄክትራ* የሚል ሲሆን hatred ወይም

enmity ተብሎ በእንግሊዝኛው ተተርጉሟል። ጥላቻ በሰው ስሜት ውስጥ የሚፈጠርና በተጠላው ሰው ላይ ጥቃትን ወይም ክፉ ጉዳትን የማድረግ ግፊት የሚጨምር እጅግ አደገኛ የሆነ መርዝ ነው። በጥላቻ የተሞላ አዕምሮ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ እንደወደደን እርስ በእርስ እንደንዋደድ **በዮሐ. 13፥34-35** እንዲሁም ጠላቶቻችንን እንድንወድ በማቴ. 5፥43-48 ከሰጠን ከአዲሲቷ ትእዛዝ ፈጽሞ በተቃረነ መልኩ ክፉን በክፉ ለመመለስና ለመበቀል የተዘጋጀ ነው።

**"ክርክር"** በሌሎች ተዛማጅ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ላይ **"ጠብ"** ወይም **"ንትርክ"** ተብሎ ተተርጉሞ እናገኘዋለን። የግሪኩ ምንባብ *ኤሪስ* የሚለውን ቃል የተጠቀመ ሲሆን ቃሉ የተወሰደው የጥንታዊት የግሪክ አማልዕክት አንዷ ከሆነችው የጠብ፣ የንትርክና ያለመስማማት ወይም ያለመግባባት ምንጭ ተብላ ከምትታወቀው ሴት አምላክ ነው። በእንግሊዝኛው ትርጉሞች strife, discord, contention ወይም quarreling ተብሎ ተተርጉሟል። ክርክር፣ ንትርክ ወይም ጠብ በሰዎች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የአሳብ ልዩነቶችን በተገቢው መንገድ ካለማስተናገድ የተነሳ የሚፈጠርና ሕብረትን የሚያጠለሽ ተግባር ነው (ሮሜ. 13፥13፣ 1ቆሮ. 1፥11፣ 3፥3፣ 2ቆሮ. 12፥20፣ ፊሊጵ. 1፥15፣ 1ጢሞ. 6፥4)።

**"ቅናት"** ወይም **"ቅንዓት"** *ዚሎስ* የሚለው የግሪክ ቃል ወይም jealousy የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የአማርኛ ፍቺ ሆኖ አንድን ነገር ከልክ ባለፈ ስሜት የመመኘትን አሳብ ያመለክታል። ቀጥተኛ ትርጉሙ ውስጣዊ የስሜት "መፍላት" ወይም "መንተክተክ" ሲሆን ከቃሉ ትርጉምና አጠቃቀም እንደምንመለከተው ቅናት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ እግዚአብሔር ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ያለው ቅናት በበጎ ጎኑ የተጠቀሰ ሆኖ እናገኘዋለን (ኢሳ. 26፥11፣ ሕዝ. 16፥42፣ ዕብ. 10፥27)። እንዲሁም በምላሹ ሕዝቡ ለእርሱና የእርሱ ለሆነው ነገር ቅናት እንዲኖራቸው ይፈልጋል (ዮሐ. 2፥17፣ ሮሜ 10፥2፣ 2ቆሮ. 7፥7፣ 11፣ 9፥2)። በዚህ መሠረት ሰዎች የተሻለ ነገርን ለማግኘት ሰዋዊና አዎንታዊ ቅናት ሊኖራቸው ይችላል። ይህ ስሜት ግን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሲያድግና በተለይ አንድ ሰው በሌሎች ላይ ክፉ ስሜት እንዲያዳብር የሚያደርግ

ጎጂ በሚሆንበት ጊዜ ቅናት በግለኝነት ላይ ያተኮረ ኀጢአተኛ ባህሪይ ይሆናል። ሰዎች በሌሎች ደስታና መሳካት ከመደሰት ይልቅ ሌሎቹ ያገኙትን መልካም ነገር ተገቢ ባልሆነ ስሜት መመኘትን ይፈጥራል (ሮሜ. 13፥13፣ 1ቆር. 3፥3፣ 2ቆር. 12፥20፣ ያዕ. 3፥14፣ 16)። ይህን ትንታኔ መሠረት በማድረግ ቅንዓትን በሦስት መልኩ ልንመለከተው እንችላለን።

***የእግዚአብሔር ቅንዓት*** - በዘጸ. 34፥12-14 መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ እንዳስቀመጠው እግዚአብሔር ለክብሩ እና ለማንነቱ ቅንዓት ስላለው ክብሩን ለማንም አያካፍልም ለዚህ ነው በዚሁ ክፍል "...ስሙ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር ቅንዓት ያለው አምላክ ነውና ለሌላ አምላክ አትስገድ…" ያለው።

***የሰው መንፈሳዊ ቅንዓት (አዎንታዊ)*** - ይህ ቅንዓት ለእግዚአብሔር ወገንተኝነትን ለማሳየት መልካም ነገርን በማሰብ ለመሥራት ወይም ለማድረግ ከውስጥ የሆነ ከፍተኛ ፍላጎት የማሳደር መግለጫ መንገድ በመሆኑ መዝሙረኛው እንዲህ በማለት ለእግዚአብሔር ያለውን ጥልቅ የቅናት ስሜት ይገልጣል፦ "የቤትህ ቅናት በልታኛለች እና የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ወድቋልና" (መዝ. 69:9)።

*የሥጋ ሥራ ቅንዓት (አሉታዊ)* - በገላ. 5፥20 በዋነኛነት ሐዋርያው ለማሳየት የፈለገውና ትኩረት ያደረገው በግልጥ እንደተቀመጠው የሥጋ ሥራን ነው። ይህ የሥጋ ሥራ በባህሪው ጥላቻ ያዘለ ማንነትን ከማንጸባረቁ ባሻገር ቅናት ክፉ ነገርን ለማድረግ የውስጥ ትኩሳት ሆኖ ያገለግላል። "ቅናት ለሰው የቍጣ ትኩሳት ነው በበቀል ቀን አይራራም" (ምሳ. 6፥34)። ቅናት እያደገ ሲሄድ የሰውን ባህሪይ በመቀየር ጨካኝና ርህራሄ ቢስ ያደርጋል። "ቅናት እንደ ሲኦል የጨከነች ናት" (መኃ. 8፥6)። ስለዚህ ቅዱሳን ይህን የሥጋ ሥራ በመዋጋት መንፈሳዊ ደህንነታቸውን መንከባከብ ይኖርባቸዋል።

**"ቍጣ"፦** በዚህ ክፍል ላይ የምናነበው **"ቍጣ"** የሚለው የአማርኛ ቃል በቀዳሚው የግሪክ ቃል *ቱሞይ* የሚል ሲሆን በብዙ ቁጥር (plural) የተጠቀሰ በመሆኑ በእንግሊዝኛው "fits of rage" ወይም "outbursts of anger" ተብሎ ተተርጉሟል። የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም የጦፈ ውስጣዊ የንዴት ስሜቶች ወደ ውጪ በሚገነፍሉበት ጊዜ የሚኖረውን ሁኔታ ያመለክታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ቍጣ በተለያዩ *ሥፍራዎች* የተጠቀሰ ቢሆንም ይህ ክፍል የሚናገረው ስለ ሰዎች ቍጣ እንደሆነ እናስተውላለን። ቍጣ እንደ ቅናት ሁሉ ከሰዎች ስሜት ጋር የተገናኘ ነው። ከ*ሥጋ ሥራዎች* አንዱ በመሆኑም ከቁጥጥር ውጪ ገንፍሎ በሚወጣበት ጊዜ ማኅበራዊ ግንኙነቶችንና ሕብረቶችን የመጉዳት አቅም አለው። ስለሆነም ሊወገዱ ከሚገባቸው ኀጢአትኛ ባህሪያት ወይም የ*ሥጋ ሥራዎች* አንዱ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል አበክሮ ያስተምረናል (ሉቃ. 4፥28፣ ሐዋ. 19፥28፣ 2ቆሮ. 12፥20፣ ኤፌ. 4፥3፣ ቆላ. 3፥8፣ ያዕ. 1፥19)። **ቍጣን እንደ** እግዚአብሔር ቃል ሳይመሽ ወይም ሳይቆይ ማስተካከል አለብን (ኤፌ 4:30)።

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች (በአንድ ቀን ካላለቀ የሁለት ሳምንት ጥናት ማድረግ እንችላለን)**</u>

1. ሉቃ. 23፥12 እና ሮሜ 8፥7 ስለ ጥል ይናገራሉ። የሁለቱ ጥሎች ልዩነት ምንድን? ስለ ጥል ምንነትና ዓይነት ምን ያስረዱናል?
2. በያዕ. 4፥4-5 ላይ የምናነበው የተጠቀሰው በነማን መካከል የተፈጠረ ጥል ነው? ምክንያቱስ ምንድን ነው? ለጥሉ ለኳሾች የተቀመጠው የመጠሪያ ስም ስለ ጥሉ ምን ይነግረናል? ከያዕ. 3፥14-16 ስለ ቅናት ምንነትና ውጤት ምን እናስተውላለን?
3. ኤፌ. 2፥16 መሰረት ጥልን በተመለከተ የተገለጸው እንዴት ነው? (በያዕ. 4፥4-5) ላይ ከሚታየው ጥል ጋር እንዴት ሊገናዘብ ይገባል ትላላችሁ?
4. በቲቶ 3፥9 ላይ "የማይጠቅሙና ከንቱዎች" የተባሉት ምን ምን ናቸው? ተወያዩበት። በ1ጢሞ. 6፥4-5 ክርክርን የሚወዱ እንዴት ባለ አገላለጽ ተጠቅሰዋል?

እንደነዚህ ካሉት ጋር የሚኖረን ግንኙነት ምን ሊሆን እንደሚገባ ከክፍሉ ምን እንማራለን?

5. በ1ቆሮ. 1፥11-13 መሰረት በቆሮንቶስ አማኞች መካከል የነበረው "ክርክር" ቅናትን ጨምሮ በ1ቆሮ.3፥3 የተጠቀሰው የምን ባህሪ መታወቂያ ሆኖ ነው የቀረበው?
6. በሮሜ 1፥28-29 እና 13፥13 መሰረት የክርክርን ኀጢአት አቅልለን እንዳናይ ምን ልንማር እንችላለን?
7. የሐ. 2፥17፣ 2ቆሮ. 11፥2፣ ፊልጵ. 3፥6፣ ሐሥ. 5፥17፣ ሐሥ. 13፥45 እና ሮሜ 10፥2 በማገናዘብ፤ ስለቀኑት ሰዎች ማንነት፣ ስለ ቅናታቸው ተግባርና ውጤት እንዲሁም ስለ ቅናታቸው ዓይነት የተረዳነውን እናካፍል።
8. በሉቃ. 4፥28 እና ሐዋ. ሥራ 19፥28 የምናየው ቍጣ እንዴት ይመሳሰላል? በምንስ ይለያያል?
9. በኤፌ. 4፥31 እና ቆላ. 3፥8 ላይ የምናነበው ትእዛዝ ምንድን ነው? በያዕ. 1፥19-20 ያለው ክፍልስ ቍጣን በተመለከተ ምን ያስተምረናል?
10. ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓትና፣ ቍጣን በተመለከተ የእኛ ሕይወትና ኑሮ ምን ይመስላል? የጌታ መንፈስ እንዲመረምረን በመፍቀድ የሚረዳንን ጸጋ ለመቀበል በጸሎት እንቅረብ።

***<u>መደምደሚያ</u>***

"በቀን እንደምንመላለስ በአግባብ እንመላለስ። በጭፈራና በስካር አይሁን፤ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፤ ***<u>በክርክርና በቅናትም አይሁን</u>***' ሮሜ 13፥13 (አ.መ.ት.)

"መራርነትን ሁሉ ቍጣና ንዴትን፣ ጭቅጭቅንና ስድብን ከማንኛውም ክፋት ጋራ ***<u>ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ</u>***።" ኤፌ. 4፥31 (አ.መ.ት.) "አሁን ግን ቍጣን፣ ንዴትን፣ ስድብን፣ ሐሜትንና አሳፋሪ ንግግርን የመሳሰሉትንም ሁሉ ***<u>አስወግዱ</u>***።" ቆላ. 3፥8 (አ.መ.ት.)

# ጥናት አራት

## **የንባብ ክፍል፡-** *ገላትያ* 5፥20

## **ርዕስ፡-** *አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት*

***ዓላማ፡-*** *አድመኛነት፣ መለያየትና መናፍቅነት የመንፈስን አንድነትና የቅዱሳንን ህብረት የሚጎዱ የሥጋ ሥራዎች መሆናቸውን ለማሳሰብ*

***መግቢያ፡-*** *ሰዎች ማኅበራዊ ፍጥረቶች እንደመሆናቸው እርስ በርሳቸው አብሮነትን የመፈለግ ዝንባሌ አላቸው። በተለይም ደግሞ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም አማካኝነት የተፈጠረች ሰማያዊ ማኅበረሰብ እንደመሆኗ የቅዱሳን ሕብረትና አንድነት እጅግ የሚበረታታ ብቻ ሳይሆን የሕልውናዋ ነጸብራቅ መሆኑ እሙን ነው። ነገር ግን ይህንን ሕብረት ሊጠፉ ከሚችሉ ሥጋዊ ባህሪያት መካከል አድመኛነት፣ መለያየትና መናፍቅነት ይጠቀሳሉ። በዚህ ጥናት እነዚህን የሥጋ ሥራዎች በዝርዝር እንመለከታለን።*

**<u>አጭር ትንታኔ</u>**

*ከዚህ ቀደም እንደተመለከትነው የሥጋ ሥራዎች መልካም ያልሆኑ ባህሪያት በመሆናቸው ሁልጊዜ መልካሙን ነገር የማበላሸትና ሙሉ በሙሉ የማጥፋት አቅም አላቸው። በገላ. 5፥20 ላይም አድመኛነት፣ መለያየትና መናፍቅነት ተብለው የተጠቀሱት እነዚህ ሦስት ባህሪያት መልካም የሆነውን ሕብረትና የመንፈስ አንድነትን የሚያጠቁ የሥጋ ሥራዎች ስለሆኑ የሚወገዙና ሙሉ በሙሉ ሊወገዱ የሚገባቸው ባህሪያት ናቸው። እነዚህ ተግባራት ሆን ተብለውም ሆነ ባለማስተዋል ሊደረጉ ይችላሉ። እንዲሁም በግለሰብ ደረጃ ወይም በቡድን ትብብር የሚደረጉ የከፋት ድርጊቶች ሆነውም ሊቀርቡ ይችላሉ። በተለይም ደግሞ በገላ. 5፥15 ላይ "ነገር ግን እርስ በርሳችሁ የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፉፉ ተጠንቀቁ" ብሎ አንባቢያኑን*

እንደሚያስጠነቅቃቸው እነዚህ የሥጋ ሥራዎች ጳውሎስ በገላትያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበሩ ከሚላቸው ችግሮች ጋር በቀጥታ የተያያዙ ለመሆናቸው ፍንጭ እናገኛለን።

**"አድመኛነት"** ለሚለው የግሪክ አቻው *ኢሪቴኢይ* የሚለው ቃል ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙም በሰዎች መካከል አለመስማማትን፣ ግጭትን ወይም ጠብን በመዝራት የተከፋፈሉና እርስ በርሳቸው የሚጠቃቁ ቡድኖችን መፍጠር ነው። የቃሉ ፍቺ በሌላ መልኩ እንደሚያሳየውም ራስ ወዳድነት ወይም የራሴ ወገን ለሚሉት ብቻ እንጂ ለሌሎች አለማሰብ ለዚህ ባህሪይ ዋነኛው መንስዔ ነው (ፊሊጵ. 1፥17)። ይህ ኀጢአተኛ ባህሪይ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን በአላስፈላጊ ፉክክርና አንዱን በሌላው ላይ አላግባብ በማነሳሳት የሚያውክ ጠንቀኛ የሕብረትና የመንፈስ አንድነት ጠር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው እንዲህ ዓይነቱ የሥጋ ሥራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቁጣንና መቅሰፍትን የሚያመጣ በክርስቲያኖች መካከል ፈጽሞ ሊኖር የማይገባው እኩይ ምግባር ነው (ሮሜ. 2፥8፣ 2ቆሮ. 12፥20፣ ያዕ. 3፥14 ይመለከቱ)።

**"መለያየት"** የሚለው የሥጋ ሥራም ከአድመኛነት ጋር በተመሳሳይ የሚታይ ቃል ነው። ቀጥተኛ የግሪክ ቃሉ *ዳይኮታሲኢይ* የሚል ሲሆን ትርጉሙም ሰዎችን በማባበልና በማታለል በመካከላቸው መለያየት ወይም አላስፈላጊ ክፍፍልን መፍጠርን ነው። በተለይም ደግሞ በቤተክርስቲያን ሕብረት መካከል ሊኖሩ የሚችሉ የአሳብ ልዩነቶችን በማጉላትና እንደምክንያት በመጠቀም መለያየትን የሚፈጥሩ ሰዎችን ክፉ ምግባር ያመለክታል። ይህም መለያየት በአጓጉል ክርክሮች፣ ሐሜታዎችና አንዱን በሌላው ላይ በማነሳሳት የሚፈጠር የቅዱሳን ሕብረት እንቅፋት ነው። ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች በም. 16፥17 ላይ በቤተክርስቲያኒቱ መካከል መለያየትን ከሚፈጥሩ ሰዎች ፈቀቅ እንዲሉ የመከራቸውን ምክር ለዚህ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

**"መናፍቅነት":-** አድመኛነትና መለያየት በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ **"መናፍቅነት"** የሚለው አሳብ ግን ከሁለቱ በተለየ መልኩ በሥርዓት የተደራጀና በተለይ በአስተምህሮ ላይ የተመሠረተ መከፋፈልን በክርስቲያኖች ሕብረት መካከል

የመፍጠር ሂደት ነው። በክፍሉ በኩረ ምንባብ ላይ የተጠቀሰው የግሪክ ቃል ሄይርሲስ ሲሆን (የእንግሊዝኛው heresy የመጣው ከዚህ ቃል እንደሆነ ልብ ይሏል)። ትርጉሙም ከመሠረታዊ የሃይማኖት አስተምህሮ ጋር የተጣረሰ፣ ባለማወቅ ሳይሆን ሆን ተብሎ የሚስፋፋ የትምህርት ስህተት ወይም ግድፈት ነው። “መናፍቅ” የሚለው የአማርኛ ቃል የመጣው “መንፈቅ” ከሚለው ቃል ነው፤ “መለየት” ወይም “መክፈል” ተብሎም ይተረጎማል። ስለሆነም መናፍቅነት የተከፈለ እውነት ያለው ነገር ግን በሐሰት የተሞላ አስተምህሮን ማራመድ ነው። ይህም በዚህ ክፍል ከሥጋ ሥራዎች እንደ አንዱ የተጠቀሰና የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን በተሳሳተ አስተምህሮ የሚያምስ ሥጋዊ ምግባር ነው።

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች**</u>

1. ከላይ በተሰጠው አጭር ትንታኔ መሠረት መናፍቅነት/መናፍቅ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ገላ. 5፥20ን ከያዕ. 3፥14-16 ጋር በማንበብ ስለ አድመኛነት ምን እንረዳለን?
3. በሮሜ. 16፡17 ጳውሎስ በሮም ለነበሩት አማኞች በመልእክቱ መዝጊያ ላይ ያሳሰባቸው ምን እንዲያደርጉ ነበር? ለእንዲህ አይነቱ ትእዛዝ አማኞች በጋራ ተገቢውን ምላሽ ባይሰጡ የሚያስከትለው ችግር ምድንነው?
4. በ1ቆሮ. 3፥3-9 መሠረት በቆሮንቶስ አማኞች መካከል የነበረው መለያየት ስለ እነርሱ ምንን ያሳያል? በተለይ ከቁጥር 5-9 ያለውን አሳብ መገንዘብ ቢችሉ ከነበሩበት መለያየት እንዴት ያተርፋቸው ነበር?
5. በሐሥ. 15፥1 የተነሳው መናፍቅነት ምን ነበር? ያስከተለው ተጽዕኖና ቤተክርስቲያን የወሰደችው እርምጃ ምን ነበር? (15:1-3፣ 6፣ 22-27)
6. 1ጢሞ. 1፥20 እና 2ጢሞ. 2፥17-18 በሄሜኔዎስና በእስክንድሮስ ላይ የደረሰው ቅጣት ምንና ከምን የተነሳ እንደነበር በመመልከት ቤተክርስቲያን በመናፍቃን ላይ መውሰድ ስለሚገባት እርምጃ ተወያዩ።
7. በሐሥ. 24፥5፣ 14 መሠረት በሐዋርያው ጳውሎስ ላይ ቀርቦ የነበረው ክስ ምንድን ነበር? ክሱ ተገቢ ነበር? ለምን?

8. በ2ጴጥ. 2፥1 ላይ ሐሰተኛ ነቢያትንና ሐሰተኛ አስተማሪዎችን "ሐሰተኛ" ያስባላቸው ምንድን ነበር? ሐሰታቸው የሚያስከትለው ጥፋትና መዘዝ በንባቡ ውስጥ እንዴት ባለ መልኩ ተገልጿል?
9. በዛሬው ጥናት መሠረት አድመኝነትን መለያየትን መናፍቅነትን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ልናበረታታባቸው መንገዶች በዝርዝር ተነጋገ።

***<u>መደምደሚያ</u>***

"ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም። ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው፤ ከእርሱም የተነሣ፣ አካል ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ፣ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል።" ኤፌሶን 4:14-16 (አ.መ.ት.)

"ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ አትመኩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ። ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፤ ነገር ግን የምድር ነው፤ የሥጋም ነው፤ የአጋንንትም ነው፤ ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ ሁሉ አሉና።" ያዕቆብ 3:14-16 (አ.መ.ት.)

## ጥናት አምስት

**የንባብ ክፍል፦** ገላትያ 5፥21

**ርዕስ፦** ምቀኝነት፣ መግደል

***ዓላማ፦*** ምቀኝነትና መግደል ከሥጋ ሥራዎች ዝርዝር ውስጥ የሚጠቀሱ ጠንቀኛ ባህሪያት እንደሆኑ ለማሳሰብ

***መግቢያ፦*** የሌሎችን ሕይወትና የእነርሱ የሆነውን ማንኛውንም ነገር በአክብሮት መያዝ መጽሐፍ ቅዱስ "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" የሚለውን መለኮታዊ ትእዛዝ መተግበር ነው። በገላ. 5፥21 ላይ የተጠቀሱት ምቀኝነትና መግደል የዚህ ዓይነቱ አኗኗር ተቃራኒ የሆኑና የሌሎችን መልካም ነገር ሳይሆን ጉዳታቸውን ወይም ጥፋታቸውን የሚፈልጉ ሥጋዊ ባህሪያት ናቸው። በዚህ ጥናት ውስጥ ስለ እነዚህ የሥጋ ሥራዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን በመተንተን ክርስቲያኖች ከድርጊቶቹ ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው እንመለከታለን።

**<u>አጭር ትንታኔ</u>**

ከዚህ ቀደም በሌሎቹ ጥናቶች እንደተመለከትነው የሥጋ ሥራዎች ተብለው በገላትያ 5፥19-21 የተጠቀሱት ባህሪያት ሁሉ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሰዎች ከሌሎች ጋር የሚኖራቸውን መልካም ግንኙነት የሚያበላሹ ናቸው። በዚህ ጥናት የምንመለከታቸው ምቀኝነትና መግደልም በተጓዳኝ ሊታዩ የሚችሉ ሁለት ሥጋዊ ባህሪያት ናቸው። እነዚህ እኩይ ምግባራት ሰዎች በሌሎች ሕይወትና ስኬት ላይ ቀና አመለካከት እንዳይኖራቸው ብቻ ሳይሆን የሌሎችን ሕልውና እስከ ማጥፋት ድረስ እንዲሄዱ የሚያደርጉ የሥጋ ሥራዎች ናቸው።

**“ምቀኝነት”**

**“ምቀኝነት”** ለሚለው የግሪኩ ጥሬ ቃል *ፍቶኖስ* (ገላ. 5፥21፣ ቲቶ 3፥3፣ ማቴ. 27፥18፣ ማር፣ 15፥10፣ ሮሜ 1፥29፣ ፊልጵ. 1፥15፣ 1ጢሞ. 6፥4፣ ያዕ. 4፥5 እና 1ጴጥ. 2፥1) የሚል ሲሆን ትርጉሙም ሌሎች መልካም ነገር በማግኘታቸው ቅር መሰኘት ወይም ደስተኛ አለመሆንን፤ ከዚያም አልፎ ሌሎች መልካምን ነገር እንዳያገኙ መንገድ መዝጋትን ወይም ማደናቀፍን ያካትታል። በተቃራኒው ምቀኝነት የሞላበት ሰው ሌሎች የሚያገኙትን ያንኑ ነገር ለራሱ ለማግኘት ይቋምጣል ወይም ይመኛል። ስለዚህም ምቀኝነት የሌሎችን ነገር አላስፈላጊ በሆነ የራስ ወዳድነት ስሜት መመኘትንም ያጠቃልላል። ይህ የምኞት ስሜት በአሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ “የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ” (ዘጸ. 20፥17) ከሚለው መለኮታዊ ትእዛዝ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ የሥጋ ሥራ ነው። ነገር ግን ምቀኝነት የሌላውን ከመመኘት ባሻገር ሌሎች ያላቸውን ነገር እንዲያጡ መፈለግን ጭምር የሚያመለክት በመሆኑ ከምኞት ከፍ ይላል። በ1ሳሙ. 18፥6-9 የእስራኤል ሴቶች “ሳኦል ሺህ ዳዊትም እልፍ ገደለ” ብለው ዳዊትን በማሞገሳቸው ምክንያት “ከዚያም ቀን ጀምሮ ሳኦል ዳዊትን ተመቅኝቶ ተመለከተው” ይላል። ሳኦል በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ዳዊትን እንዲያሳድደው ያደረገው ይህ የምቀኝነት ባህሪይ ነበር። የሳኦልና የዳዊት የአሳዳጅና የተሳዳጅነት ታሪክ ምቀኝነት ከፉ መርዝ ያለበት መልካሙን ነገር የሚያጠፋ ለመሆኑ ጥሩ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

**“መግደል”**

**“መግደል”** ተብሎ የተጠቀሰው የሥጋ ሥራም በአሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ “አትግደል” (ዘጸ. 20፥13) ተብሎ የተጠቀሰውን ግልጽ ትእዛዝ መሠረት ያደረገ እንደሆነ ይታመናል። መግደል የሌላን ሰው ሕይወት አላግባብ በሆነ መልኩ መቅጠፍ ወይም ማጥፋት ማለት ነው። የግሪኩ ጥሬ ቃል *ፎኖስ* ወይም *ፍኦኖስ* የሚል ሲሆን *ፍቶኖስ* (ምቀኝነት) ከሚለው ቃል ጋር የድምጸት ምስስል እንዳላቸው እንመለከታለን። ሆኖም ከቃላት መመሳሰል ባለፈ ምቀኝነትና መግደል የተለየ ቁርኝት ያላቸው ድርጊቶች እንደሆኑ መረዳት አስፈላጊ

ይሆናል። ለዚህም በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን ግድያ ዋቢ ማድረግ ይቻላል። ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ የተነሳበትና ሕይወቱን ያጠፋበት ዋነኛው ምክንያት ምቀኝነት እንደሆነ ዘፍ. 4፥3-8 ያለው ታሪክ በግልጽ ያሳየናል። ቃየን እጅግ የተናደደውና ፊቱ የጠቆረው የአቤል መሥዋዕት ከእርሱ ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ ነበር። ይህም በወንድሙ መልካም ስኬት ምክንያት ያደረበት የምቀኝነት ስሜት የገዛ ወንድሙን ሕይወት አላግባብ በግፍ እንዲቀጥፍ አስገድዶታል።

የሰውን ሕይወት ማጥፋት ወይም ደምን ማፍሰስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ የተኮነነ ተግባር ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ ኢየሱስ መግደልን በተመለከተ የሰጠው አዲስ ብያኔ ወይም ማብራሪያ በተለየ ሁኔታ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ ነው። በማቴ. 5፥21-26 እንደምንመለከተው ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ዘጸ. 20፥13 ላይ የተጠቀሰውን “አትግደል” የሚለውን ትእዛዝ ሠፋ በማድረግ በእግዚአብሔር እይታ በሌሎች ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጥላቻ፣ ፍትሃዊ ያልሆነ ቁጣ ወይም የቃላት ስድብ ከመግደል እንደማይተናነስ አጽንቶ መናገሩን እናስተውላለን። በዚህ መሠረት በገላ. 5፥21 ከሥጋ ሥራዎች እንደ አንዱ የተጠቀሰው “መግደል” የሰዎችን ሕይወት አካላዊ ደምን በማፍሰስ ማጥፋት ብቻ ሳይሆን ሌሎችን መጥላትና በክፉ መመልከት ከመግደል ያልተናነሰ ኀጢአታዊ ድርጊት መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ይሆናል።

## ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. ከላይ በተገለጠው አጭር ትንታኔ መሠረት “ምቀኝነት” የሚለው ቃል ከገላትያና ከቲቶ መልዕክቶች በስተቀር በሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ቃሉ ምን ተብሎ ነው የተተረጎመው? ገላ. 5፡20 ታሳቢ በማድረግ ምቀኝነት ምን ማለት ነው? ከቅንዓት ጋርስ ምን ዓይነት ተዛምዶ እንዳለው ተወያዩ
2. በቲቶ 3፥3 መሰረት ከተዘረዘሩት የሥጋ ሥራዎች መካከል “ምቀኝነት” አንዱ ነው። ባጠቃላይ እስከ አሁን በተመለከትናቸው ጥናቶች ምቀኝነት በተመለከተ የጨበጥነው ቁም ነገር ምንድ ነው?

3. በ1ሳሙ. 18፥6-9 ላይ በሳኦል ልብ ምቀኝነት የነገሰው እንዴት ነበር? ስለ ምቀኝነት ከታሪኩ ምን እንማራለን?
4. ዘፍ. 37፥3-11 በምናገኘው ታሪክ ውስጥ ምቀኝነትን የምናየው እንዴት ነው? በታሪኩ ውስጥ የምቀኝነት መነሻ የሆነው ጉዳይ ምን ነበር?
5. በዘጸ. 20፥1-17 ከተዘረዘሩት አስርቱ ትዕዛዛት መካከል "አትግደል" የሚለው አንዱ ነው። በማቴ. 5፥21-22 ጌታ ይህንን ትእዛዝ ተመርኩዞ ያስተማረው ምን ነበር?
6. በ1ዮሐ. 3፥15 "መግደል" የሚለው አሳብ ምን ዓይነት ፍቺ ተሰጥቶታል? ጥቅሱን ከማቴ. 5፥21-22 ጋር በማዛመድ እንወያይበት።
7. በማቴ. 15፥19-20 እና በማር. 7፥21-23 "መግደል" ከተጠቀሰበት ከዐውዱ ምን እንማራለን?
8. ዘጸ. 17፥13፣ ዘኍ. 21፥24፣ እና ዘዳ. 13፥15፣ 20፥13 የምናነበውን አሳብ "አትግደል" ከሚለው ትእዛዝ አንጻር እንዴት ልንረዳው ይገባናል? ሰዎች በዚህ አሳብ ቢሞግቱን ምላሻችን ምን መሆን አለበት?
9. ወደ ምቀኝነት የሚያድግ መጥፎ ቅንዓት፣ የሌላውን ሰው ኑሮ የእኛ እንዲሆን መመኘት/መቋመጥ በልባችን ይኖር ይሆን? እንደ ነፍስ ማጥፋት የሆነው ጥላቻስ ይገኝብን ይሆን? ራሳችንን እንፈትሽ፤ ንስሃ እንግባ።

***<u>መደምደሚያ</u>***

"ቀደም ሲል እኛ ራሳችን ማስተዋል የጐደለን፣ የማንታዘዝ፣ የተታለልን፣ ለተለያየ ምኞትና ምቾት ባሪያ ሆነን የተገዛን ነበርን፤ እየተጣላንና እርስ በርስ እየተጠላላን በክፋትና ***<u>በምቀኝነት እንኖር</u>*** ነበር። ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤ ይህንም መንፈስ እግዚአብሔር

በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ላይ አትረፍርፎ አፈሰሰው፤ ይኸውም በጸጋው ጸድቀን የዘላለምን ሕይወት ተስፋ ይዘን ወራሾች እንድንሆን ነው። ይህም የታመነ ቃል ነው። ***<u>በእግዚአብሔር ያመኑቱ መልካሙን ነገር ለማድረግ ራሳቸውን አሳልፈው ይሰጡ</u> ዘንድ*** እነዚህን ነገሮች አስረግጠህ እንድትናገር እፈልጋለሁ። ይህ መልካምና ለማንኛውም ሰው የሚጠቅም ነው።" ቲቶ 3፥3-8 (አ.መ.ት.)

"ወንድሞቻችንን ስለምንወድድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ፍቅር የሌለው ሁሉ በሞት ይኖራል። ***ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይወት እንደሌለው ታውቃላችሁ።*** " 1ዮሐ. 3፥14-15 (አ.መ.ት.)

## ጥናት ስድስት

**የንባብ ክፍል፡-** ገላትያ 5፥21

**ርዕስ፡-** ስካር፣ ዘፋኝነት

**ዓላማ፡-** ስካርና ዘፋኝነት በመንፈሳዊ ሕይወትና ልምምድ ውስጥ ያላቸውን አሉታዊ ተጽዕኖ በተገቢው መንገድ
ለመረዳት

**መግቢያ፡-** ክርስቶስን የሚከተሉ አማኞች በሁሉም መስክ ልከኝነትንና ራስን መግዛትን የሕይወታቸው መርህ አድርገው እንዲኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ይህም ከተለያዩ ውስጣዊውንም ሆነ ውጫዊውን ሰውነት ሊጎዱ ከሚችሉ ልቅ የሆኑና ቅጥ ያጡ ድርጊቶችና ልምምዶች ራስን በመጠበቅ ወይም በመታቀብ በአግባብ መመላለስን ያካትታል። በገላ. 5፥21 ከተዘረዘሩት የሥጋ ሥራዎች ውስጥ ስካርና ዘፋኝነት ከእንዲህ ዓይነቱ የልከኝነት የሕይወት መርህ ጋር የሚጣረሱ አግባብ የሌላቸው የአኗኗር ዘይቤዎች ናቸው። እነዚህ የሥጋ ሥራዎች ማንነትን የሚያዋርዱ፤ ክብርን የሚያቃልሉ፤ አምልኮተ-እግዚአብሔርን የሚጎዱ ከመሆናቸውም ባሻገር መንፈሳዊ ድክመትን በማምጣት የህይወት መስመር የሚያስቱ ናቸው (ምሳ. 23፥31-35፣ ዘጸ. 32፥6)። በዚህ ጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስካርና ዘፋኝነት ምንነት እንዲሁም በእውነተኛ መንፈሳዊነት ላይ ስለሚኖራቸው አሉታዊ ተጽዕኖ በዝርዝር እንመለከታለን።

### <u>አጭር ትንታኔ</u>

**ስካርና ዘፋኝነት** በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአብዛኛው አብረው የሚጠቀሱ ልከኝነት የጎደላቸው፣ የብኩንነት መገለጫና ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ጠንቅ የሆኑ የአኗኗር ዘይቤዎች ናቸው። ስካርም ሆነ ዘፋኝነት ጳውሎስ ይህንን መልእክት በሚጽፍበት ወቅት በነበሩት አረማዊያን የባዕድ አምልኮም ሆነ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በስፋት የሚታወቁ እኩይ ልምምዶች ናቸው። እነዚህ ልምምዶች በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን

በአጽንዖት ከሚወገዙና በክርስቶስ የቅድስናን ኑሮ ለመኖር የተጠሩ አማኞች እንዲያስወግዷቸው ከሚጠበቅባቸው *ሥጋዊ* ድርጊቶች ውስጥ ይመደባሉ።

**"ስካር"**

**"ስካር"**ወይም በግሪኩ *ሜታይ* እንዲሁም በተለያዩ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች drunkenness ተብሎ የተተረጎመው ቃል የሚያሰክር ወይም አልኮል ያለበትን መጠጥ ያለ ልክ ወደ ሰውነት ውስጥ በማስገባት (በመጠጣት)፡ራስን ከቁጥጥር ውጪ የማድረግ ጎጂ ልምምድ ነው። ስካር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁልጊዜም የተወገዘ ነው (ምሳ. 20፥1፣ ሉቃ. 21፥34፣ ሮሜ 13፥13)። በአልኮል ሰውነቱ የተመረዘ ሰው ራሱን መቆጣጠር አይችልም። ስለሆነም ስካር ራስን በመግዛት ሊቃኝ የሚገባው የእውነተኛ መንፈሳዊ አኗኗር ዘይቤ ፈጽሞ ተቃራኒ ነው (ዘፍጥ9:20-24)። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ. 5፥18 ላይ "መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይህ ማባከን ነውና" በማለት በስካር የተሞላ ሕይወትን በመንፈስ ከተሞላ ሕይወት ጋር የተቃረነ ስለ መሆኑ የጻፈው። "ስካር አዕምሮን ያጠፋል" (ሆሴ.4፥11) እንደሚል ስካር አዕምሮን አስጥሎ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መናጋትን ይፈጥራል። ስካር የሰውነት ጤንነታችንንም እንደሚያቃውስ የተረጋገጠ ነው። በተጨማሪም "ስካርን ለመከተል በጠዋት ለሚማልዱ የወይን ጠጅ እስኪያቃጥላቸው እስከ ሌሊት ድረስ ለሚዘገዩ ወዮላቸው" (ኢሳ. 5፥11) እንደሚል ስካር ፍርድን ያመጣል። እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን የሥጋ ሥራ በቸልተኝነት መለማመድ ወይም በድርጊቱ መቀጠል የሚያመጣው መንፈሳዊ አደጋ ብርቱ መሆኑን በመረዳት አማኝ ይህን ድርጊት ከመሞከርና በልምምዱ ከመቀጠል ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል።

**"ዘፋኝነት"**

**"ዘፋኝነት"***ኮሞስ* ለሚለው የግሪክ ቃል የተሰጠ የአማርኛ ትርጉም ሲሆን በተለያዩ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳት ትርጉሞች orgies, carousing, reveling

ተብሎ ተተርጉሟል። *ኮምስ* በሚለው ቃል ውስጥ ዜማ ከማንጎራጎር ያለፈ ሠፋ ያለ አሳብ ስላለ እንደየቃላቱ አፈታት ዘፋኝነት የብዙ እኩይ ልምምዶች ጥርቅም ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። የግሪኩ በኩረ ቃል የሚያመለክተው በወቅቱ በአሕዛብ መካከል የነበረውን የባዕድ አምልኮ ልምምድ ሲሆን በውስጡ ዳንኪራን፣ ሙዚቃን፣ ለጣዖት መሠዋትን፣ ያለ ልክ መብላትና መጠጣትን ወይም መስከርን እንዲሁም ግልሙትናንና የተለያዩ ርኵሰቶችን ያካተተ ምግባር ነው። ቃሉን በአግባቡ ለመተርጎም በ2005 የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከ "ዘፋኝነት" ይልቅ "ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ" ብሎ ተርጉሞታል። ይህም "ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ" የሚለው ሀረግ በ1ጴጥ. 4፥3 ላይ "የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት . . . ያለፈው ዘመን ይበቃልና" ብሎ የጠቀሳቸውን ድርጊቶች ሁሉ የተካተቱበትን እኩይ ምግባር ያመለክታል።

## ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ዘፍ. 9፥20-24 ላይ የሚገኘውን ታሪክ ስናነብ ስካር ስለሚያስከትለው ጥፋት ምን እንረዳለን?
2. በምሳሌ 20፥1 ላይ የሚያሰክር መጠጥ ከመጠጣት ጋር ተያይዞ የምናገኘው ምክር ምንድን ነው?
3. ኢሳ. 28፥7 ላይ የምናያቸው አገልጋዮች ሁኔታ ምን ይመስላል? ለመሳታቸው ምክንያት የሆነውስ ምንድን ነበር?
4. ሉቃ. 21፥34 ስካር ስለሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ ምን ያስተምረናል?
5. በሮሜ 13፥13 "በአገባብ እንመላለስ" የሚለው አባባል በገላ. 5፥21 ከተጠቀሱት ስካርና ዘፋኝነት አንጻር ምን ማለት ነው?
6. በ1ጴጥ. 4፥3 ዘፈን የተጠቀሰበትን ዐውድ በማስተዋል በ1ዮሐ. 2፥15-16 ካለው የንባብ ክፍል ጋር አዛምደን የተረዳነውን እናካፍል።

7. 1ቆሮ. 10፥7 ላይ በምናነበው ጥቅስ ውስጥ “ሊዘፍኑም ተነሡ” የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው እንዴት ያለውን ዘፈን ነው? ተግባራቸውን አስጸያፊ ያደረገውስ ምንድን ነበር? ከዚህ ምን እንረዳለን?
8. በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ መጠጥ መጠጣትና ዘፋኝነት እንደ ነጻነት ሲቆጠር ይሰማል። ምን አልባት እንዲህ ያለው አመለካከት በእኛም ዘንድ ቢኖር ራሳችንን እንመርምር። በእነዚህ ነገሮች ምክንያት ምስክርነታችን እንዳይበላሽ ሕይወታችንም እንዳይጎዳ ጌታ ይረዳን ዘንድ በንስሃ ፊቱን እንፈልግ።

***<u>መደምደሚያ</u>***

“እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ። ቀኖቹ ክፉ ናቸውና ዘመኑን በሚገባ ዋጁ። ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ። ***<u>በመንፈስ ተሞሉ</u>*** እንጂ ***<u>በወይን ጠጅ አትስከሩ</u>***፤ ይህ ብክነት ነውና። ***<u>በመዝሙርና በውዳሴ</u>***፣ በመንፈሳዊም ዝማሬ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ በልባችሁ ለጌታ ተቀኙ፤ አዚሙም። በዚህም እግዚአብሔር አብን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ሁሉ ነገር ሁልጊዜ አመስግኑ። ለክርስቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሀት የተነሣ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ።” ኤፌ. 5፥15-20 (አ.መ.ት.)

## ክፍል ሁለት፡-

## የመንፈስ ፍሬዎች

## ጥናት ሰባት

**የንባብ ክፍል፡-** ገላትያ 5፥22

**ርዕስ፡-** ፍቅር

**ዓላማ፡-** ፍቅር የእውነተኛ መንፈሳዊነት መገለጫና በቀዳሚነት የሚጠቀስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ መሆኑን ለማሳየት

***መግቢያ፡-*** *መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ማንነት ለመግለጥ ከተጠቀማቸው አገላለጾች አንዱ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" የሚል ነው (1ዮሐ. 4፥9፣ 16)። ፍቅር የሚለው ቃል የእግዚአብሔር የራሱ መገለጫ መሆኑ ምን ያህል የላቀ ዋጋ ያለው መሆኑንና በዋነኛነት የሚነሳ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ በሕይወታቸው ሊያሳዩትና ሊያዳብሩት የሚገባ የመንፈስ ፍሬ መሆኑን ያመለከታል። በዚህ ጥናታችን ውስጥ ከገላ. 5፥22 በመነሳት እንደ መንፈሳዊ ፍሬነቱ ስለ ፍቅር መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምራቸውን አንዳንድ መሠረታዊ እውነቶች እንመለከታለን።*

**<u>አጭር ትንታኔ</u>**

በገላ. 5፥22-23 ውስጥ የመንፈስ ፍሬ ተብለው በቅደም ተከተል ከተጠቀሱት ዘጠኝ መዘርዝሮች ውስጥ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ፍቅር ነው። ይህም ፍቅር በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ቀዳሚነቱንና በቀጣይ ለተዘረዘሩት ሌሎች የመንፈስ ፍሬዎች መሠረት መሆኑን ያመለክታል። ይህንንም ጳውሎስ በዚሁ የገላትያ መልእክቱ ላይ እንዲህ ብሎ ይገልጸዋል፡- "ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ። ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፥ እርሱም፡- ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው" (ገላ. 5፥13-14)። እንዲሁም ጳውሎስ በሮሜ 13፥8-11 "ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው" በማለት ከሌሎች ሕግጋት ሁሉ የላቀ መሆኑን ሲያሳይ በ1ቆሮ. 12፥31 እና 13፥13 ደግሞ "የሚበልጠው መንገድ" በማለት ፍቅርን እንደገለጸው እንመለከታለን። እነዚህ ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ከመሆኑም በላይ ከሁሉም የላቀ በመሆኑ

በዚህ መዘርዝር ውስጥ ጳውሎስ በቀዳሚነት ሲያስቀምጠው ይህንን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም።

**“ፍቅር”**

“ፍቅር” የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ በተለያዩ ቃላቶች የተጠቀሰ ቃል ነው (ለምሳሌ፡- *ኤሮስ* [የታዊ ፍቅር]፣ *ፊሊያ* [የወዳጅነት/የጓደኛ ፍቅር] እና *ስቶርጌ* [ቤተሰባዊ ፍቅር])። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በክርስቶስ ኢየሱስ የገለጠው ዘለዓለማዊ የአባትነት ፍቅር እንዲሁም የክርስቶስ ተከታይ የሆኑ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጣቸው የፈሰሰውና እንዲያጎለብቱት ከሚፈለገው ባህሪይ ጋር የተያያዘው ፍቅር ***አጋፔ*** በመባል የሚታወቀው የፍቅር ዓይነት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከ120 ጊዜ በላይ የተጠቀሰው *አጋፔ* ከፍቅሮች ሁሉ በላይ ከፍተኛውን ደረጃ የሚይዝ ምንም ዓይነት መተኪያ የሌለው መለኮታዊውን ፍቅር የሚገልጽ ቃል ነው።

*አጋፔ* ፍቅር እግዚአብሔር ኀጢአተኛ የሆኑትን የሰው ልጆች ለማዳን አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመስቀል ሞት አሳልፎ በመስጠት የገለጠው ፍቅር ነው (ዮሐ. 3፥16፣ ሮሜ 5፥8)። በራስ ወዳድነት ላይ ያልተመሠረተና ያለ ምንም ግላዊ ጥቅም ራስን ለሌሎች በመስጠት ላይ የተመሠረተ ፍቅር ነው። አማኝ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ለፈሰሰው ገደብ የሌለው መለኮታዊ ፍቅር ምላሽ የሚሰጥበትና ሌሎችንም እንዲወድበት የታዘዘው በ*አጋፔ* ፍቅር ሲሆን በገላ. 5፥22 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ባስቀመጠው መዘርዝር ውስጥ የሚገኘው ይህ ዓይነቱ ፍቅር ነው። ይህ ፍቅር የመንፈስ ፍሬ እንደመሆኑ መጠን በሰዎች የግል ባህሪይ ወይም ብቃትና ችሎታ የሚገኝ ሳይሆን አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ባደገ መጠን የሚያድግና የሚጎለብት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው (ሮሜ 5፥5)።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ገላ 5:22 እንደሚያስረዳን "ፍቅር" እግዚአብሔር እኛን የወደደበት የፍቅር ዓይነት ነው። ገላ. 5፥22፣ ሮሜ 5:5፣ 1ዮሐ. 3፥1 1ዮሐ. 4፥7-16 መሰረት አማኝ እንዲህ ዓይነቱን ፍቅር ለሌሎች ለመስጠት የሚችልበትን አቅም እንዴትና ከየት እንደሚያገኝ ተወያዩ። 1ዮሐ. 4፥9 እና 4፥16
2. በ1ቆሮ. 13፥1-3 ላይ ፍቅር አልባ ማንነት እንዴት ነው የተገለጸው? ከገለጻው ምን እንማራለን? በ1ቆሮ. 13፥4 ላይ ከፍቅር ጋር ተያይዘው ወይም ተዛምደው የተዘረዘሩት ምን ምን ናችው? ዝርዝሮቹ የፍቅር ትርጉም ወይስ የፍቅር መገለጫ ናቸው? እንዴት?
3. በ1ቆር. 13፥4 ላይ "ፍቅር … ቸርነትንም ያደርጋል" የሚለውን አባባል በ1ቆሮ. 13፥3 ላይ "ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል … ምንም አይጠቅመኝም" ከሚለው ጋር በማዛመድ ምን እንረዳለን?
4. በ1ቆሮ. 13፥5-7 ያሉትን ጥቅሶች በማንበብ ፍቅር የሚሆናቸውን ወይም የሚያደርጋቸውን እንዲሁም የማይሆናቸውን ወይም የማያደርጋቸውን ነገሮች በየፈርጁ በመተንተን ተወያዩበት።
5. በሮሜ 14፥15 መሠረት አማኝ በፍቅር "አልተመላለሰም" የሚባለው መቼ/እንዴት ነው?
6. በሮሜ 13፥10 "ፍቅር የሕግ ፍጻሜ" ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ነው የሕግ ፍጻሜ የሚሆነው?
7. ሮሜ 12፥9 "ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን" ይላል። የጥቅሱን ሙሉ አሳብ በመመልከት ግብዝነት ያለው ፍቅር ምን ዓይነት ፍቅር ሊሆን ይችላል?
8. በዮሐ. 15፥9-13 ላይ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ፍቅር ያዘዛቸው ወይም ያስተማራቸው ምንድን ነበር?

9. ጌታ ስለ መጨረሻው ዘመን ሲያስተምር ስለ ፍቅር በማቴ. 24፥12 የተናገረው ምን ነበር? ከንግግሩስ ምን እንማራለን?

10. ከዛሬ ጥናት ምን እንደተረዳን በማስረዳት ስለራሳችን የፍቅር ሕይወት እየመረመርን እንጸልያለን።***<u>መደምደሚያ</u>***“የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ***<u>ፍቅር</u>*** ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ ልጆቹ ነን። ….ከመጀመሪያ የሰማችኋት፣ እርስ በርሳችን ***<u>ልንዋደድ ይገባናል</u>*** የምትለዋ መልእክት ይህች ናትና፤ የክፉው ወገን ሆኖ ወንድሙን እንደ ገደለው እንደ ቃየን አትሁኑ፤ ለምን ገደለው? ምክንያቱም የእርሱ ሥራ ክፉ፣ የወንድሙ ግን ጽድቅ ስለ ነበረ ነው። ወንድሞች ሆይ፤ ዓለም ቢጠላችሁ አትደነቁ። ወንድሞቻችንን ***<u>ስለምንወድድ</u>*** ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ***<u>ፍቅር</u>*** የሌለው ሁሉ በሞት ይኖራል። ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይወት እንደሌለው ታውቃላችሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ ስለ ሰጠ፣ ***<u>ፍቅር</u>*** ምን እንደ ሆነ በዚህ እናውቃለን፤ እኛም ሕይወታችንን ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል።” 1ዮሐ. 3፥1፣ 15-16 (አ.መ.ት.)

**ጥናት ስምንት**

**የንባብ ክፍል፡-** ገላትያ 5፥22

**ርዕስ፡-** ደስታ፣ ሰላም

**ዓላማ፡-** ደስታና ሰላም በመንፈሳዊው የሕይውት ልምምድ ውስጥ እጅግ ወሳኝ ግብዓቶች መሆናቸውን ለማሳየት

**መግቢያ፡-** የሰው ልጆችን ሁሉ ከሚያመሳስሏቸው ፍላጎቶች መካከል በሕይወት ውስጥ ደስታንና ሰላምን ማግኘት ሊጠቀሱ የሚችሉ ነገሮች ናቸው። እውነተኛ የሆነ ውስጣዊ ደስታና የማይናወጥ ልባዊ ሰላም ለሕይወት ምሉእነት እጅግ ያስፈልጋሉ። ደስታም ሆነ ሰላም የራሳቸው የሆነ ለየት ያለ መገለጫ ቢኖራቸውም ውስጣዊ መሆናቸውና በውጫዊ

ሁኔታ የሚመዘኑ አለመሆናቸው ተመሳሳይ ገጽታ ይሰጣቸዋል። በዚህ ጥናታችን አማኞች ሊያፈሩት ከሚገባቸው የመንፈስ ፍሬዎች መካከል እነዚህን ሁለት ባህሪያት ወይም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ገላ. 5፥22ን መሠረት በማድረግ እንመለከታለን።

## **<u>አጭር ትንታኔ</u>**

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነተኛ መንፈሳዊነትንና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ተገቢ አኗኗር አስመልክቶ በጥምረት ከሚጠቀሱ አሳቦች መካከል **<u>ደስታና ሰላም</u>** ጎላ ብለው የሚታዩ ባህሪያት ናቸው። በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመጡ አማኞች ሁሉ ይህንን የእግዚአብሔር ደስታና ሰላም በሕይወታቸው ሊለማመዱት እንደሚያስፈልግ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይጠቁማሉ። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ. 14፥17 ላይ እንደሚያስረዳው ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ ከጽድቅ ጋር የእግዚአብሔር መንግሥት መሠረታዊ መለያዎቹ እንደሆኑ እንመለከታለን። እንዲሁም “የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ” (ሮሜ. 14፥13) በማለት ደስታና ሰላም በእግዚአብሔር ከማመን ብቻ የተነሳ የሚገኙ እሴቶች መሆናቸውን ይጠቁማል። በዚህም የተነሳ ነው በገላ. 5፥22 ላይ ከተዘረዘሩት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል ደስታና ሰላም የሚጠቀሱት።

### **“ደስታ”**

**“ደስታ”** (joy ወይም በግሪኩ ካራ) በአዲስ ኪዳን ውስጥ በስፋት የሚገኝ ቃል ሲሆን ጥሬ ቃሉ ብቻውን ሲተረጎም መልካም ነገርን ከማግኘት ወይም ከማሰብ የተነሳ የሚገኝ የስሜት መፈንደቅ ወይም እርካታ ነው። ነገር ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ደስታ ከውጫዊው መልካም ስሜት ያለፈ ጥልቅ የሆነና በሚረብሹ እንዲሁም ደስ በማያሰኙ ሁኔታዎች መካከል የሚቀጥል አዕምሮአዊ እረፍትን ያመለክታል። ይህ እውነተኛ ደስታ ከምንም የሚገኝ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ፍቅር ከመረዳትና ከመለማመድ የተነሳ በመፈንስ ቅዱስ አማካኝነት በውስጣችን የሚፈጠር በማይመቹና ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች እንኳን የማይቆም ጥልቅ የእረፍት ስሜት ነው (2ቆሮ. 7፥4፣

1ተሰ. 1፥6)። ይህ ደስታ በራሳችን ጥረት ወይም በሁኔታዎች መመቻቸት የሚገኝ ሳይሆን ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ በመሆኑ አማኞች  በመንፈስ በመመላለስ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት የሚፈጠርን፣ የሚበዛና የሚያድግ ነው።

**"ሰላም"**

**"ሰላም"** (peace ወይም በግሪኩ *ኤሬኔ*) በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሠረት አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ የሚፈጠር ጥልቅ የሆነ ውስጣዊ መረጋጋትና እረፍት ነው። ሰላም በዋነኝነት ከኃጢአት የተነሳ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ተፈጥሮ የነበረው ጠላትነት በክርስቶስ የማስታረቅ ሥራ አማካኝነት ሲወገድ የሚገኝ የህሊና እረፍት ነው (ሮሜ 5፥1፣ ኤፌ. 2፥17)። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ የሚገኝ የህሊና እረፍት ሰዎች በውስጣቸው ከራሳቸው ጋር፣ በውጪ ከሌሎች (አማኞች ወይም ከማያምኑ) ጋር እንዲሁም ከተፈጥሮ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር የሚገለጥ ሁከት፣ ጭንቀትና ስጋት የሌለበት የተረጋጋ ሕይወት ነው። ሰላም የመንፈስ ፍሬ በመሆኑ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር በሚያዳብረው ግንኙነት መጠን የሚያድግና የሚጎለብት ሲሆን በተለይም ደግሞ በጌታ የተጠሩ ቅዱሳን የመንፈስ ሕብረታቸውንና አንድነታቸውን የሚጠብቁበት ዋነኛው ማሠሪያ ነው (ኤፌ. 4፥2)።

**<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

1. በማቴ. 13 ቁ. 20 እና ቁ. 44 መካከል ደስታን በተመለከተ የምናየው ልዩነት ምንድን ነው?
2. በማቴ. 25፥20-23 በሚነበበው ታሪክ ውስጥ "ወደ ጌታህ ደስታ ግባ" የሚለው ሀረግ ምን ማለት ነው? ይህ ደስታ በገላ. 5፥22 ከተጠቀሰው የሚለይ ነውን? በታሪኩ መሠረት ወደ ጌታቸው ደስታ የገቡትና የሚገቡት እነማን ናቸው?
3. በዮሐ. 17:13 ላይ "በእነርሱም ዘንድ ደስታዬ የተፈጸመ እንዲሆንላቸው" የሚለው አገላለጽ ምን ማለት ነው? እንዴትስ ነው የእርሱ ደስታ በአማኞች የሚፈጸመው?
4. በሐዋ. 8፥4-8 መሠረት በሰማርያ ከተማ ታላቅ ደስታ የሆነው ከምን የተነሳ ነበር?
5. ፊልጵ. 4፥4 እና 1ተሰ. 5፥16ን በማገናዘብ/በማነጻጸር የተረዳነውን እንነጋገር።

6. ኤፌ. 2፥14-18 ስለ ሰላም ምን ያስረዳናል? በኤፌ. 4፥3 መሠረትስ ለአማኞች ሰላም ምንድን ነው?
7. ገላ. 5፥22፣ ሮሜ 8፥6 እና ሮሜ 14፥17 በማነጻጸር ስለ ሰላም ምን ልንረዳ እንችላለን?
8. ፊልጵ. 4፥7 እና ቆላ. 3፥15ን በማንበብ ከጥቅሶቹ የተረዳነውን አሳብ እንወያይ።
9. ከዛሬው ጥናት ስለ ደስታና ሰላም የተረዳችሁትን አብራሩ። ለየዕለት ሕይወታችን ምን ይጠቅማል?

***<u>መደምደሚያ</u>***

“ምንጊዜም በጌታ ***<u>ደስ</u>*** ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ ***<u>ደስ</u>*** ይበላችሁ።” ፊልጵ. 4፥4 (አ.መ.ት.)

“ነገር ግን ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ ***<u>ደስታችሁ</u>*** ታላቅ እንዲሆን የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ።” 1ጴጥ. 4፥13 (አ.መ.ት.) “በ***<u>ሰላም</u>*** ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።” ኤፌ. 4፥3 (አ.መ.ት.)

“በተረፈ ወንድሞች ሆይ ደኅና ሁኑ። ፍጹማን ሆኑ ምክሬን ስሙ፤ አንድ ሐሳብ ይኑራችሁ፤ ***<u>በሰላምም ኑሩ</u>***። የፍቅርና የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።” 2ቆሮ. 13፥11 (አ.መ.ት.)

# ጥናት ዘጠኝ

**የንባብ ክፍል፡-** ገላትያ 5፥22

**ርዕስ፡-** ትዕግሥት፣ ቸርነት

***ዓላማ፡-*** በትዕግሥትና በቸርነት የታነጸ ሕይወት የመንፈስ ፍሬ የሞላበት መሆኑን ለማሳሰብ

***መግቢያ፡-*** አማኞች በግለሰባዊ ሕይወታቸውም ሆነ እርስበርስ ወይም በውጭ ካሉት ጋር በሚኖራቸው ማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ ሊያዳብሩት ከሚገባቸው መልካም ባህሪያት ውስጥ ትዕግሥትና ቸርነት ይጠቀሳሉ። እግዚአብሔር ታጋሽና ለፍጥረቱ ሁሉ ቸርነትን አድራጊ አምላክ ነው፤ በመሆኑም ትዕግሥትና ቸርነት የእግዚአብሔር የራሱ የባህሪይ መገለጫዎች ናቸው (ሮሜ 2፥4)። ትዕግሥትና ቸርነት ጳውሎስ በገላ. 5፥22-23 ላይ ከዘረዘራቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል ሁለቱ ሲሆኑ ይህ ጥናታችን እነዚህን ባህሪያት የምንመለከትበት ይሆናል።

**<u>አጭር ትንታኔ</u>**

ትዕግሥትና ቸርነት እንደ መንፈስ ፍሬነታቸው በክርስትና እምነትና የሕይወት ልምምድ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ መንፈሳዊ ባህሪያት ናቸው። ትዕግሥትም ሆነ ቸርነት የእግዚአብሔር ባህሪይ መገለጫ እንደመሆናቸው የባህሪዩ ተካፋዮች እንዲሆኑ የተጠሩ ሁሉ በሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሊያዳብሯቸው የሚገቡ ሰናይ ምግባራት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንድንከተላቸው በሚያቀርብልን ታሪኮችም ሆነ በቀጥታ በሚሰጠን ምክርና ትእዛዝ ትዕግስተኛንነትና ቸር አድራጊነትን የተላበሰ ሕይወት እንዲኖረን በተለያዩ ክፍሎች ያስተምረናል።

**"ትዕግሥት"**

**"ትዕግሥት"** (patience ወይም በግሪኩ *ማክሮቱሚያ*) የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደስ የማያሰኙ፣ የማይመቹ ወይም በቀላሉ ሊያስቆጡ፣ ሊያበሳጩና

ሊያሳዝኑ የሚችሉ ነገሮችን ችሎ የማለፍ ውስጣዊ ብቃት ነው። ትዕግሥት የተሞላ ሰው በሕይወቱ ውስጥ በሚገጥመው መከራና ስቃይ ወይም የመልካም ነገሮች መዘግየት ምክንያት ውስጣዊ ማንነቱ ሳይናወጥ በጽናት የሚቆም ሰው ነው። ትዕግሥት የእግዚአብሔር የራሱ የማንነቱ መገለጫ ባህሪይ ስለሆነ የኀጢአት ብዛት ሳይገድበው ሁሉን በትዕግሥት የሚችል አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ሥፍራዎች ላይ ያስተምረናል (ሮሜ 9፥22፣ 1ጢሞ. 1፥16፣ 1ጴጥ. 3፥20፣ 2ጴጥ. 3፥15)። ስለሆነም እርሱን የምንከተል ሁላችን ልናፈራው የሚገባና ልንላበሰው የሚያስፈልግ በጎ ባህሪይ ነው (2ቆሮ. 6፥6፣ ቆላ. 3፥12፣ 2ጢሞ. 3፥10፣ ያዕ. 5፥10)። ፍቅር የመንፈስ ፍሬዎች ሁሉ መሠረት እንደመሆኑ ትዕግሥትም ከፍቅር የሚመነጭ መሆኑን ኤፌ. 4፥2 "እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ" በማለት በግልጽ ያሳየናል። ስለሆነም የትዕግሥት ፍሬን በማፍራት የተጠራንበትን የሕይወት ጥሪ ከፍቅር በሚወጣ ትዕግሥት ልንፈጽመው ይገባናል።

**"ቸርነት"**

**"ቸርነት"** (kindness ወይም በግሪኩ *ክሬስቶቴስ*) ዐበይት ከሆኑት የመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ነው። የቃሉ ጥሬ ትርጉም እንደሚያመለክተው ለሌሎች የሚደረግ ከራስ ወዳድነት የጸዳ ርህራሄና ደግነት ነው። ቸርነት በተለይ ሌሎች ላደረጉልን በጎ ነገር የሚሰጥ ምላሽ ሳይሆን ለሚጠሉንና ክፉ ለሚያስቡብን ወይም ለሚያደርጉብን በመልካም የምንመልስበት በጎ ምግባር ነው። ቸርነትም እንደ ትዕግሥት ከእግዚአብሔር የሚመነጭ የራሱ ባህሪይ ሲሆን ዐመጸኛና ጠላት ለሆነው የገዛ ፍጥረቱ የሚያሳየው በጎ ምላሽ ነው (መዝ. 31፥19፣ 68፥10፣ 119፥68፣ ሮሜ 11፥22፣ ኤፌ. 2፥7፣ ቲቶ 3፥4)። ይህ የእግዚአብሔር ቸርነት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችን ስለፈሰሰ ክርስቶስን የምንከተል አማኞች ሁሉ በሕይወታችን ልንለማመደው የሚገባ፤ ለወዳጆቻን ብቻ ሳይሆን ለሚጠሉን ሁሉ በመልካምነት ምላሽ መስጠት እንድንችል የሚያደርገን የሕይወት መርህ ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሮሜ 2፥4፣ 9፥22 እና 2ጴጥ. 3፥15 ትዕግሥት ከእግዚአብሔር አንጻር እንዴት ተገልጿል?
2. በ2ቆሮ. 6፥3-13 ካሉት ዝርዝሮች መካከል ትዕግሥትና ቸርነት በቁ. 6 ተጠቅሰዋል። አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ የትዕግሥትና የቸርነት ሚና ምንድነው?
3. በኤፌ. 4፥1-2 መሠረት ትዕግሥት ምንን ማሳያ ነው? በቆላ. 3፥12-13 ትዕግሥትና ቸርነትን በተመለከተ የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው? ምንስ ማለት ነው?
4. ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ጢሞ. 3፥10 ላይ ለጢሞቴዎስ ከሚሰጠው አደራ ስለ ትዕግሥት ምን እንረዳለን?
5. ሮሜ 5፥3-4 እና ያዕ. 1፥2-3 በማንበብ በመከራና በትዕግሥት መካከል ስላለው ግንኙነት የተረዳነውን እናካፍል። በነዚህ ክፍሎች ውስጥ ትዕግሥት የተገለጠው እንዴት ነው?
6. በዕብ. 6፥12 የተስፋውን ቃል ለመውረስ የሚያስፈልገው ምንድን ነው? ያዕ. 5፥10-11 "ነቢያትን ተመልከቱ" የሚለው ለምድን ነው?
7. ኤፌ. 4፥32 አማኞች ምን እንደናደርግ ያዘናል? ከሉቃ 6፥35 ጋር በማስተያየት የምንረዳውን እንከፋፈል።
8. በቲቶ 3፥4 የእግዚአብሔር ቸርነት በተገለጠ ጊዜ የሆነውን በመወያየት እንደ አማኝ ከእግዚአብሔር የምንካፈለው ይህ የቸርነት ባህሪይ በእኛም ኑሮ ሲገለጥ በዙሪያችን ባሉት ላይ ሊፈጠር የሚችለው አዎንታዊ ተጽዕኖ ምን ሊሆን እንደሚችል እንወያይ።
9. **** በዛሬ ጥናት መሰረት ትዕግስት እና ቸርነት እንዴት በዕለት ተ ዕለት ህይወታችን ልተገብረውና ልንለማመደው እንደምንችል የተረዳነው አካፍለን በጸሎት እንደምድመው።

***<u>መደምደሚያ</u>***

“ወንድሞቼ ሆይ፤ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፤ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ***<u>ትዕግሥትን</u>*** እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ። ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉኣን እንድትሆኑ ***<u>ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም</u>***።” ያዕ. 1፥2-4 (አ.መ.ት.)

“በእምነትና ***<u>በትዕግሥት</u>*** የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንድትሆኑ አንፈልግም።” ዕብ. 6፥12 (አ.መ.ት.)

“እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ ***<u>ቸሮችና</u>*** ርኅሩኆች ሁኑ።” ኤፌ. 4:32 (አ.መ.ት.)

## ጥናት አሥር

**የንባብ ክፍል፦** ገላትያ 5፥22

**ርዕስ፦** በጎነት፣ እምነት/ታማኝነት

***ዓላማ***፦ ክርስቲያኖች የተጠሩት በጎነትንና እምነትን (ታማኝነትን) በሕይወታቸው በሙላት እንዲያንጸባርቁ መሆኑን ለማስታወስ

***መግቢያ***፦ የእግዚአብሔር ቃል ስለ እውነተኛ መንፈሳዊነት ከሚያስተምራቸው በርካታ አሳቦች መካከል በጎነትና እምነት/ታማኝነት የሚጠቀሱ ናቸው። ክርስቲያኖች መልካምነትንና ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ያላቸውን ታማኝነት በሁሉም የሕይወት አቅጣጫዎቻቸው እንዲያሳዩ ተጠርተዋል። ስለዚህም ነው በጎነትና እምነት ሐዋርያው ጳውሎስ በገላ. 5፥22 ላይ የመንፈስ ፍሬ ብሎ ባስቀመጣቸው መዘርዝር ውስጥ የሚገኙት። በዚህ ጥናታችን እነዚህን ሁለት የመንፈስ ፍሬዎች እንመለከታለን።

**<u>አጭር ትንታኔ</u>**

ከዚህ ቀደም እንደተመለከትነው በገላ. 5፥22-23 ላይ የመንፈስ ፍሬ ተብለው የተዘረዘሩት መልካም ባህሪያት የእግዚአብሔር የማንነቱ መገለጫዎች ናቸው። በጎነትና እምነት/ታማኝነትም በእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ ከምናያቸው ባህሪያት መካከል ይጠቀሳሉ። ስለ እግዚአብሔር በጎነትና ታማኝነት መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ሥፍራዎች ላይ በግልጽ ይመሠክራል። ከዚህም በተጨማሪ በጎነትና እምነት/ታማኝነት የእግዚአብሔር ባህሪይ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን አምነው የሚከተሉ ሁሉ እንደ መንፈስ ፍሬ በሕይወታቸው ሊያንጸባርቋቸው የሚገቡ ሰናይ ምግባራት እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። እነዚህ ባህሪያት በገላ. 5፥22 አብረው እንደተጠቀሱ ሁሉ በ2ተሰ. 1፥11 ላይም "የበጎነትንም ፈቃድ ሁሉ የእምነትንም ሥራ በኃይል ይፈጽም ዘንድ ስለ እናንተ ሁልጊዜ እንጸልያለን" በሚል በጥምረት እንደተጠቀሱ እንመለከታለን። በተጨማሪ ማቴ. 25፥21 "አንተ በጎ፣ ታማኝም ባሪያ" ከሚለው ጥቅስ አሁንም በጎነትና ታማኝነት በዚህ ሁኔታ በጥምረት እንደተጻፉ እናነባለን።

**"በጎነት"**

**"በጎነት"** (goodness ወይም በግሪኩ *አጋቶሱኔ*) በተለያየ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱሳችን የሚገኝ ቃል ሲሆን ደግነትን፣ መልካምነትን ወይም ጥሩ መሆንን ያመለክታል። ምንም እንኳን ቃሉን ለመተርጎም "በጎነት" በሚለው የአማርኛ ቃል የተጠቀሱ ጥቅሶች ጥቂት ቢሆኑም ከእግዚአብሔር መልካምነት እንዲሁም ከሚያደርጋቸው መልካም ነገሮች በመነሳት እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ መልካም ስለ መሆን የሚያስተምራቸውን አሳቦች በመመልከት የቃሉን አሳብ በዚህ መልኩ ለመረዳት እንችላለን። ጳውሎስ በሮሜ 15፥14 ላይ "በበጎነት ራሳችሁ እንደ ተሞላችሁ . . . ስለ እናንተ ተረድቼአለሁ በማለት በጎነት በክርስትና ሕይወት ውስጥ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራል። እንዲሁም በኤፌ. 5፥8-9 ላይ "የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና" በማለት የበጎነት ሕይወት ከጨለማ ወደ ጌታ ብርሃን የመመለስ አንዱ ምልክት እንደሆነ ያሳያል። ስለዚህ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን በጎነት መላበስ ወይም የበጎነትን ፍሬ ማፍራት እንደሚኖርብን ቃሉ ያሳስበናል።

**"እምነት"** ወይም **"ታማኝነት"**

**"እምነት"** ወይም **"ታማኝነት"** (faith, faithfulness በግሪኩ *ፒስቲስ*) በገላ. 5፥22-23 ከተዘረዘሩት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ውስጥ ለትርጉም አሻሚ የሆነ ቃል ነው። ለዚህም ምክንያቱ በአዲስ ኪዳን ውስጥ *ፒስቲስ* የሚለው የግሪኩ በኩረ-ቃል አንድም "እምነት" አልያም "ታማኝነት" ተብሎ በሁለቱም መንገድ ሊተረጎም የሚችል ከመሆኑ የተነሳ ነው። እምነት በአንድ ነገር፣ ሰው ወይም አምላክ ማመንን የሚያመለክት ቃል ሲሆን ታማኝነት ደግሞ በሌላ ወገን የታመነ ሆኖ መገኘትን ወይም ለሌላው ታማኝ መሆንን ያሳያል። ስለሆነም ቃሉ የትኛውን ፍቺ እንደሚያመለክት ለመረዳት የምንችለው ከዐውዱ በምናገኘው ፍንጭ መሠረት ብቻ ይሆናል። በገላትያ ውስጥ እምነት (በእግዚአብሔር ማመን) እንደ መለኮታዊ ስጦታ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር የሚገናኝ መሆኑን በተለያዩ ክፍሎች የተጠቀሰ በመሆኑና (ገላ. 3-2-5፣ 5፥5) ጳውሎስ በበርካታ

ሥፍራዎች ላይ ይህንን ቃል ከዚህ አንጻር የተጠቀመው በመሆኑ በዚህ ጥቅስ ላይም ቃሉ የሚያመለክተው እምነትን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የክፍሉ ዐውድ እንደሚጠቁመው ከተዘረዘሩት የመንፈስ ፍሬዎች አንጻር ቃሉ ታማኝነት (ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ታማኝ ሆኖ መገኘት) በሚለው ቢተረጎም የተሻለ ስሜት ይሰጣል። ለዚህም ነው አዲሱ መደበኛ ትርጉም ቃሉን ከእምነት ይልቅ ታማኝነት በሚል የተረጎመው።

ታማኝነት ለእግዚአብሔር ወይም ለሌሎች ታምኖ መገኘትን ያመለክታል። እግዚአብሔር በቃሉና በሥራው ታማኝ እንደሆነ ክርስቲያኖችም ለእግዚአብሔር እንዲሁም ለሌሎች ሰዎች በቃላቸውና በሥራቸው ታማኝ ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል። ታማኝነት እንደ መንፈስ ፍሬነቱ በራሳችን አቅምና ችሎታ የምናመጣው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የምናፈራውና የምናዳብረው መልካም ሥነ-ምግባር ነው። ታማኝነት ለእግዚአብሔር በተሰጠ ሁኔታ መኖርን፣ ለሌሎች የገባነውን ቃል ጠብቆ መገኘትን፣ ኃላፊነትን በተገቢው ሁኔታ መወጣትን እና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ምግባር ነው። ጳውሎስ በ2ጢሞ. 4፥7 ላይ “መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ ሩጫውን ጨርሼአለሁ ሃይማኖትን [እምነት/ታማኝነት] ጠብቄአለሁ” በማለት ይህንኑ የግሪክ ቃል በመጠቀም እስከ መጨረሻው ታማኝ ስለ መሆን ያስተምራል። እንዲሁም በማቴ. 25፥21 እንደምንመለከተው “ጌታውም፡-መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው” እንደሚል ክርስቲያኖች የታማኝነት ሕይወትን እንድንኖር ይጠበቅብናል።

**_የመወያያ ጥያቄዎች_**

1. በሮሜ 15፥14 ጳውሎስ ስለ በጎነት የሰጠው ምስክርነት ምን ነበር? በሮም ስለሚገኙት ቅዱሳን የሰጠው መልካም ምስክርነት የምን ውጤት እነሆነ የተረዳነውን እናካፍል? (ሮሜ 15፡ 1=13 ይነበብ)
2. በኤፌ. 5፥9 መሠረት በጎነት የምን መገለጫ ነው?
3. በ2ተሰ. 1፥11 መሠረት በጎነትና ታማኝነት ውጤታማ ወይም ፍሬያማ የሚሆነው ምን ሲሆን ነው? ከክፍሉ ምን እንማራለን?

4. በ2ጴጥ. 1፥5-6 መሠረት በእምነት ላይ በጎነትን እንዲሁም በበጎነት ላይ እውቀትን መጨመር ምን ማለት ነው? በምዕራፉ ቁጥር 2 እና 3 መሠረት የመጨመር ትጋት መነሻ መሠረቱ ምንድን ነው?
5. በኤፌ. 6፥21 እና በቆላ. 4፥9 የምናገኘው ተመሳሳይ አሳብ ምንድን ነው? ደግሞም በ1ቆሮ. 4፥1-2 ከታማኝነት ጋር የቀረበውን አሳብ በማብራራት ተወያዩበት።
6. 1ጢሞ. 6፥12-13 ላይ ስለ ተገለጸው ታማኝነት በማብራራት እንወያይ። በተጨማሪም በ2ጢሞ. 2፥1-2 ላይ ታማኝነትና አደራ እንዴት ተገልጸዋል?
7. በ1ጢሞ. 1፥12 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ራሱ ከሚሰጠው ምስክርነት ምን እንማራለን?
8. በዛሬው ጥናት ከበጎነትና ከታማኝነት አንጻር ሕይወታችን ሲመዘን እንዴት ነን? ጸጋውን እዲሰጠን፣ በበጎነትና በታማኝነት መመላለስ እንችል ዘንድ እንዲረዳን በንስሃ የጌታን ፊት እንሻለን።

***<u>መደምደሚያ</u>***

“በገዛ ክብሩና ***<u>በበጎነቱ</u>*** የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኀይል ሰጥቶናል። ከክፉ ምኞት የተነሣ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ፣ ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል። በዚህም ምክንያት በሙሉ ትጋት ***<u>በእምነታችሁ ላይ በጎነትን</u>*** ለመጨመር ***<u>ጣሩ፤ በበጎነት ላይ</u>*** ዕውቀትን በሙሉ ትጋት በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ለመጨመር ጣሩ፤ በበጎነት ላይ ዕውቀትን፣…” 2ጴጥ. 1፥3-5 (አ.መ.ት.)

## ጥናት አስራ አንድ

## የንባብ ክፍል፡- ገላትያ 5፥23

## ርዕስ፡- የውሃት/የዋህነት፣ ራስን መግዛት

**ዓላማ፡-** ክርስቲያኖች በሚመሩት ሕይወታቸው የዋህነትን እንዲሁም ራስን መግዛትን እንዲያዳብሩ ለማሳሰብ

**መግቢያ፡-** በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊው መሥፈርት የዋህነትና ራስን መግዛት የልከኝነት መገለጫና ለራስም ሆነ ለሌሎች የሚጠቅሙ መልካም ባህሪያት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈሳዊው ሕይወት ውስጥ የየዋህነትንና ራስን የመግዛትን አስፈላጊነት በተመለከተ በርካታ አሳቦችን ያስተምረናል። ከዚህ ቀደም እንዳየናቸው የመንፈስ ፍሬዎች ሁሉ የዋህነትና ራስን መግዛት ከእግዚአብሔር ማንነት ጋር የተያያዙና ከራሱ ብቻ የሚገኙ እውነተኛ መንፈሳዊ ባህሪያት ናቸው። በዚህ ጥናታችን ገላ. 5፥23ን መሠረት በማድረግ የመንፈስ ፍሬ ተብለው ስለተጠቀሱት ሁለቱ ባህሪያት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን እንመለከታለን።

### <u>አጭር ትንታኔ</u>

በገላትያ 5፥22-23 ላይ የመንፈስ ፍሬ ተብለው ከተዘረዘሩት ዘጠኝ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ውስጥ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የዋህነትና ራስን መግዛት ናቸው። የዋህነትና ራስን መግዛት ሰው ከአምላኩ፣ ከራሱም ሆነ ከሌሎች ጋር በሚኖረው መስተጋብር ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እንደ ክርስቲያን ሁሌም ልንከተላቸው የሚገቡ ሰናይ ምግባራት ናቸው። ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 11፥29 ላይ "ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና" ብሎ ባስተማረው ትምህርት መሠረት የዋህነት የራሱ የእግዚአብሔር ባህሪይ መሆኑንና ከእርሱ ብቻ ልንማረው ወይም ልናገኘው እንደምንችል እንረዳለን። እንዲሁም ጳውሎስ በ2ጢሞ. 1፥7 ላይ "እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና" ማለቱ ራስን የመግዛት ዋነኛው ምንጭ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያስተምረናል።

**“የውሃት/የዋህነት”**

**“የውሃት/የዋህነት”** (gentleness ወይም *ፕራውቴስ*) ተብሎ በዚህ ክፍል ላይ የተተረጎመው የግሪክ ቃል በአንዳንድ የአማርኛ ቅጂዎች ላይ “ገርነት” ተብሎ የተተረጎመ ሲሆን በሌሎች ክፍለ-ምንባቦች ላይ ደግሞ “ትሕትና” የሚለው ትርጉም ተሰጥቶት እንመለከታለን። የግሪኩን ቃል በትክክል ሊገልጽ የሚችል አቻ ባለመኖሩ እነዚህ ቃላቶች የተመረጡ ቢሆኑም የቃሉ ትክክለኛ ትርጉም እንዲሁ በልማድ የዋህ ወይም ገራ ገር ብለን ከምንረዳው ባህሪይ በላይ ከውስጥ የመነጨ አሳቢነት (ማስተዋል)፣ ቅንነት (ቀናነት) እና ትሕትና (ገርነት) የተቀላቀለበት የአእምሮ ወይም የልብ ሁኔታን የሚያሳይ ነው። በተለምዶ እንደሚታሰበው የዋህነት የደካማነት ወይም የሽንፈት ምልክት አይደለም፤ ነገር ግን ከእምነትና ለእግዚአብሔር ከመገዛት የሚገኝ የመንፈስ ጥንካሬ የታከለበት ግሩም ባህሪይ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የየዋህነትን ባህሪይ እጅግ ያበረታታል። ጳውሎስ የዋህነትን ልንከተለው የሚገባ ባህሪይ እንደሆነ በተለያዩ ሥፍራዎች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እንደገለጸ እናነባለን፦ ኤፌ. 4፥2 “በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ”፤ ቆላ. 3፥12 “የዋህነትን ልበሱ”፤ 1ተሰ. 2፥7-8 “ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትንከባከብ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን”፤ 1ጢሞ. 6፥11 “የዋህነትን ተከታተል”፤ ቲቶ 3፥2 “ለሰው ሁሉ የዋህነትን ሁሉ የሚያሳዩ እንዲሆኑ አሳስባቸው”። እንዲሁም ጴጥሮስ “የዋህና ዝግተኛ መንፈስ” “በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ” መሆኑን ያሳስበናል (1ጴጥ. 3፥4)። ያዕቆብም “. . . በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ” (ያዕ. 1፥21)፤ እንዲሁም “ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አንዋዋሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ” (ያዕ. 3፥13) በማለት የዋህነት በክርስትና ውስጥ ያለውን ትልቅ ዋጋ ያሳስበናል። (ተጨማሪ ጥቅሶች፦ 2ቆሮ. 10፥1፣ ገላ. 6፥1፣ ቆላ. 3፥12፣ 2ጢሞ. 2፥26)

**"ራስን መግዛት"**

**"ራስን መግዛት"** ( (self-control ወይም በግሪኩ *ኢንክራቴያ*) ቃሉ ራሱ በግልጥ እንደሚያመለክተው የራስን ስሜት፣ ድርጊትና ፍላጎት መቆጣጠር ወይም በራስ ቁጥጥር ሥር ማድረግ ነው። ራስን መግዛት ከአስተሳሰብ፣ ከአነጋገር ወይም ከድርጊት ልቅነት መታቀብ የመቻል አቅም ሲሆን በተለይ ደግሞ እንደ መንፈሳዊ ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የተጣመረና የተጣጣመ ሕይወትን መምራት ማለት ነው። ራስን መግዛት የልቅነትና ቅጥ ያጣ አኗኗር ፍጹም ተቃራኒ ነው። ምናልባት ጳውሎስ "ራስን መግዛትን" በገላትያ የመንፈስ ፍሬ መዘርዝር ውስጥ በመጨረሻ ያስቀመጠው በሥጋ ሥራዎች መዘርዝር ላይ በመጨረሻ ካስቀመጣቸው የልቅነትና ቅጥ የማጣት ሕይወት ምልክት ከሆኑት "ስካርና ዘፋኝነት" ጋር በማነጻጸር ሊሆን ይችላል። በዚህ መልኩ ታስቦ የተደረገ ባይሆን እንኳን ይህ ንጽጽር በግልጽ የሚታይ ነገር ነው፤ ራስን መግዛት ሁለንተናን ከልቅነት በማቀብ በአግባቡ ተገቢውን ነገር ብቻ ለማድረግ ራስን መስመር ውስጥ የማስገባትና በሥርዓት የመመራት ጥበብ ነውና።

ራስን ስለ መግዛት አስፈላጊነት የእግዚአብሔር ቃል አበክሮ ያስተምረናል። ጠቢቡ ሰሎሞን በምሳሌዎቹ "ታጋሽ ሰው ከጦረኛ፣ ስሜቱን የሚገዛም ከተማን በጕልበቱ ከሚይዝ ሰው ይበልጣል (ምሳ. 16፥32)፤ እንዲሁም "ራሱን የማይቆጣጠር ሰው፣ ቅጥሯ እንደ ፈረሰ ከተማ ነው" (ምሳ. 25፥28) በማለት ራስን መግዛት ወይም መቆጣጠር ከተማን በጦር ኃይል ከመቆጣጠር እንደሚበልጥና ራስን አለመግዛት ደግሞ ሥርዓት ያጣ የተበተነ ከተማን መምሰል ነው በማለት በሕይወት ውስጥ ራስን መግዛት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው አሳይቶናል። ጌታ ኢየሱስ በራሱ ሕይወት ምሳሌነት እንዲሁም በትምህርቶቹ ራስን ስለ መግዛት አስፈላጊነት እንዳስተማረን በሕይወታችን ራስን መግዛትን ልንለማመድ ያስፈልገናል። ጳውሎስ በአገረ ገዡ ፊሊክስ ፊት ስለ ወንጌል ሲሰብክ ከተናገራቸው ዋና ነገሮች ውስጥ ጽድቅና ኵነኔን ጨምሮ ራስን መግዛት መካተቱ ምን ያህል ዋጋ ሊሰጠው እንደሚገባ ያመለክታል

(ሐዋ. 24፥25)። ራስን የመግዛት ምንጩ እግዚአብሔር ራሱ በመሆኑ ሐዋርያው ጳውሎስ በቲቶ 2፥13 ላይ እንደጻፈው በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠን ጸጋ "ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል"። (ተጨማሪ ጥቅሶች፦ 2ጢሞ. 1፥7፣ ቲቶ 1፥8 "ራሱን የሚገዛ ይሁን"፣ ቲቶ 2፥5፣6)

## የመወያያ ጥያቄዎች፥

1. በ1ቆሮ. 7፥9 መሠረት ራስን መግዛት ማለት ምን ማለት ነው? ደግሞስ በ2ጴጥ. 1፥6 ላይ ራስን ስለ መግዛት የምናየው አሳብ ምንድን ነው?
2. በገላ. 5፥23 እና በ1ቆሮ. 4፥21 ተመልክተን በመግቢያው ላይ በተሰጠን አጭር ትንታኔም በመመርኮዝ የውሃት ወይም የየውሃት መንፈስ ምን ማለት ነው? በገላ. 6፥1 ላይ የውሃት/የዋህንት የተጠቀሰበትን አሳብ በማብራራት እንወያይ።
3. በኤፌ. 4፥1-2 ተያይዘው ከቀረቡት ባህሪያት ጋር በማነጻጸር በክፍሉ ዐውድ መሠረት ስለ የዋህነት/የውሃት እንወያይ።
4. በቆላ. 3፥12 እና በ1ጢሞ. 6፥11 ላይ ስለ የዋህነት የተሰጡት ትእዛዛት ምን ምን ናቸው? ከትእዛዝ ቃላቶቹ ምን እንማራለን?
5. 1ጴጥ. 3፥15 እንዴት እንረዳዋለን? በማብራራት እንወያይ።
6. ምሳ. 16፥32 እና ምሳ. 5፥28ን በማንበብ ራስን ስለ መግዛት የተገነዘብነውን እናካፍል። *(ማስታወሻ፥ በአሮጌው ትርጉም "መንፈስ" የሚለውን ቃል አዲሱ ትርጉም "ስሜት" ይለዋል። ስሜትን መግዛት/ራስ መግዛት ነው)*
7. ቲቶ 2፥11-13ን በማንበብ ራስን ለመግዛት ጸጋ የሚኖረውን ድርሻ በምንባቡ መሠረት ተወያዩበት።
8. 2ጢሞ. 1፥7 ራስን ስለ መግዛት የሚያስረዳን ምንድን ነው?
9. ከጥናታችን አንጻር በየዋህነት ስለመመላለስና እንዴት ልተገብረው እንደምንችል የተማራችሁትን አስረዱ። ራስን መግዛትና የዋህነትን እንዲያስተምረን በጌታ ፊት በጸሎት እንሁን።

***መደምደሚያ***

“ክርስቶስን ጌታ አድርጋችሁ በልባችሁ ቀድሱት። እናንተ ስላላችሁ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሁልጊዜ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን ይህን ሁሉ በትሕትናና በአክብሮት አድርጉት፤ በክርስቶስ ያላችሁን መልካም ጠባይ አክፋፍተው የሚናገሩ ሰዎች በሐሜታቸው እንዲያፍሩ በጎ ኅሊና ይኑራችሁ።” 1 ጴጥ. 3፥15 (አ.መ.ት.)

**ክፍል ሦስት፡-** *መንፈሳዊ ውጊያ*
*ጥናት አስራ ሁለት*
**የንባብ ክፍል፡-** ኤፌሶን 6:10

**ርዕስ**፡- የውስጥ ጥንካሬ

**ንዑስ ርዕስ አንድ**፡- በጌታ መበርታት

**ዓላማ፡-**የውስጥ ብርታት ሊሰጠን ሁል ጊዜ አብሮን ያለውን ጌታ እንድንደገፍ ለማሳሰብ።

***መግቢያ፡-***መንፈሳዊ ውጊያ ለመዋጋት፥ የመዋጊያ መሳሪያ መሸከም ብቻ አይጠቅምም። ከመሳሪያው በተጨማሪ የውስጥ ጥንካሬ ያስፈልጋል። አንድ ሰው ለመንፈሳዊ ውጊያ የሚያስፈልገው የመጀመሪያው ነገር የራሱ የውስጥ ጥንካራ እንደሆነ እናያለን። እንደአማኞች በውስጥ ሰውነታችን ለመጠንከር የምንችለው በጌታ በራሱ መሆኑን በዚህ ጥናት እናያለን።

***ማብራሪያ፡***

1. “በቀረውስ” (በአዲሱ መደበኛ “በተረፈ”) የሚለው ቃል ጳውሎስ መንፈሳዊ ውጊያን በስተመጨረሻ ማድረጉን ያሳያል።ማለትም እስካሁን ካስተማረውና ካዘዘው ትዕዛዛት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያሳያል። ይህ ማለት በዋነኝነት አማኞች ሊያደርጉት የሚገባው በኤፌሶን 1፡1-6፡9 የተጻፉትን ነው። መንፈሳዊ ውጊያ እነዚህን ነገሮች ሊተካ አይገባውም። በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ መንፈሳዊ ውጊያ ቦታ የለውም። በሌሎች ዘንድ ደግሞ ሁሉም ነገር መንፈሳዊ ውጊያ ብቻ ነው። መንፈሳዊ

ውጊያ ቦታ አለው፥ ቦታው ግን ማድረግ ያለብንን ሁሉ እያደረግን ነው መዋጋት ያለብን።

2. የበረታቹ ሁኑ፡- አንድ ሰው ውጊያ ለመዋጋት የውጊያ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የውስጥ ብርታትም እንደሚያስፈልገው ያሳያል። የጦርነት ስልጠና መሳርያ አጠቃቀም ብቻ ሳይሆን፥ የውስጥና የአካል ጥንካሬ ላይም ያተኮረ ነው። አብዛኛው ስልጠና ጥንካሬ ላይ እንጂ መሳሪይ አጠቃቀም ላይ አይደለም። በኢያሱ ምዕራፍ አንድ እግዚአብሔርም ህዝቡም ኢያሱን "አትፍራ፥ በርታ" ያሉበት ምክንያት፥ኢያሱ ውስጡ ካልበረታ ከፊቱ ያለውን ውጊያ መዋጋትም ማዋጋትም ስለማይችል ነው።

3. በጌታ መበርታት፤- በኤፌሶን ውስጥ 'ጌታ' ብሎ የሚጠራው ኢየሱስን ነው። ጌታ ማን እንደሆነ በጥልጽ የተጠቀሱበት ቦታዎች፡ ኤፌ 1፡2፣3፣15፣17 ናቸው።በእነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይናገራል። በጌታ መበረታትን ለመረዳት የሚከተሉትን ሁለት ጥቅሶች ማየት በቂ ነው፤

    - 2ኛ ጢሞ 4፡16-17 ". . . ሁሉም ተዉኝ እንጂ። ይህንም አይቍጠርባቸው፤ ዳሩ ግን የስብከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም አሕዛብ ሁሉ እንዲሰሙት፥ ጌታ አጠገቤ ቆሞ አበረታኝ፥ ከአንበሳ አፍም ዳንሁ።"
    - 1ኛ ሳሙ 30፡6 "ዳዊት ልቡን በአምላኩ በእግዚአብሔር አበረታ። "

4. በብሉይ ኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር የህዝቡ ጉልበት እንደሆነ እናያለን። ለምሳሌ መዝ 18፡1 እና 28፡7-8። በኤሶ 4፡5 ደግሞ አንድ ጌታ ብቻ እንዳለ ይነግረናል። ስለዚህ "በጌታ የበረታቹ ሁኑ" ሲል በኢየሱስ ክርስቶስ የበረቱ እንዲሆኑ ነው የሚያዛቸው።ነገር ግን ኢየሱስ ራሱ የብሉይ ኪዳኑ እግዚአብሔር እንደሆነም ማየት እንችላለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡**

1. በኤፌ. 6:10 ጳውሎስ አማኝ **በማህበራዊ መስተጋብር** ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ሚናና ኃላፊነቶች ዘርዝሮ እንደጨረሰ፡ የትኩረቱን አቅጣጫ ወዴት ነው ያዞረው? **"በቀረውስ"** የሚለውስ አባባል ምን ያመለክታል?
2. በኤፌ. 6:10 መሰረት ለአማኝ ከሚታየው አኗኗርና ህይወት በዘለለ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው አስፈላጊ ጉዳይ ምንድን ነው? ተወያዩበት።
3. በኤፌ 6፡10 መሰረት "በጌታና በኃይሉ ችሎት" የሚለውን አሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ? ይህስ በውስጥ ሰውነት መጠንከር ለመንፈሳዊ ውጊያ የሚኖረው አስተዋጾ ምንድን ነው?
4. በኤፌ 6፡10 መሰረት "የበረታችሁ ሁኑ" የሚለውን አሳብ በማብራራት ተወያዩበት? ይህስ ለመንፈሳዊ ውጊያ የሚኖረው ሚና ምንድን ነው?
5. በኤፌ 3፡16-17 መሰረት ጳውሎስ ለአማኞች የሰጠውን ምክርና አስፈላጊነቱን በተመለከተ በማብራራት ተወያዩበት
6. በ2ኛ ጢሞ 4፡16-17 መሰረት ጳውሎስ ሚያልፍበትን መከራ በድል ለማለፍ የአቅምና የብርታቱ ምንጩ ምንድን ነበር? ከዚህ ምስክርነቱ ምን እንማራለን?
7. በ1ኛ ሳሙ 30፡6 መሰረት ዳዊት ልቡን በእግዚአብሔር አበረታ የሚለውን አሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ?
8. በኢሳ 40፡29-31 መሰረት ከብላቴናዎች ድካም ጎበዛዝት መዛል ጋር ተያይዞ የቀረበውን ተስፋ በተመለከተ በዝርዝር ተነጋገሩበት?
9. ከዛሬው ጥናት በጌታና በሃይሉም ችሎት በውስጡ ሰውነታችን ስለ መበረታት ምን ተማርን? በጌታ ለመበርታት እኛ ማድረግ ያለብን ምንድን ነው?

**መደምደምያ፡-**

በችግራችን ሰዓት ሰዎች ከጎናችን ሲሆኑ ችግራችንን እንኳ እንረሳለን። ስዎቹ ሲርቁን ግን ችግራችንን እናስታውሳለን። ጌታ ግን ሁል ጊዜ፥ በመንፈሳዊ ጦርነት ጊዜ አብሮን ስላለ፥ አይናችንን እርሱ ላይ ካደረግን፥ በችግራችን ከማዘን፣በጦርነቱ ከመፍራት ይልቅ በእርሱ እየተደሰትን ልንበረታ ይገባል።

## ጥናት አስራ ሦስት

**የንባብ ክፍል፡-**ኤፌሶን 6:10

**ርዕስ**፡-የውስጥ ጥንካሬ

**ንዑስ ርዕስ ሁለት፡-** በኃይሉ ችሎት መበርታት

**ዓላማ፡-** መንፈስ ቅዱስ የውስጥ ሰውነታችንን ለማጠንከር ኃይል እንደሚሰጠን አምነን፥ የእርሱን ኃይል ሁል ጊዜ በጸሎት እንድፈልግና ለመንፈስ ቅዱስም እየተገዛን እንድንኖር ለማበረታት።

**መግቢያ፡-**በባለፈው ጥናት እንዳየነው መንፈሳዊ ውጊያ ለመዋጋት፥ የመዋጊያ መሳሪያ መሸከም ብቻ አይጠቅምም። ከመሳሪያው በተጨማሪ የውስጥ ጥንካሬ ያስፈልጋል። አንድ ሰው ለመንፈሳዊ ውጊያ የሚያስፈልገው የመጀመሪያው ነገር የራሱ የውስጥ ጥንካራ እንደሆነ ባለፈው ጥናት አይተናል።በዛሬው ጥናት የውስጥ ጥንካሬ ለማግኘው ጌታ በውስጣችን ባሳደረው በመንፈሱ በኩል ኃይል እንደሚሰጠን እናያለን።

**ማብራሪያ፡**

በኤፌ 1፡18-22 ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ከሚጸልይላቸው ጉዳዮች አንዱ "ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው።" ይህ የሚያሳየን ለቅዱሳን የተሰጠ ኃይል አለ። ኃይል ሁሉ ብርቱ አይደለም። ሁሉም ሰው ኃይል አለው። ነገር ግን የሁሉም ሰው ኃይል እኩል አይደለም። የአንዳንዱ ሰው ኃይል ውስን ነው። የጌታ ኃይል ግን ብርቱ ነው። ብርቱ ማለት ቻይ ማለት ነው። የጌታ ኃይል ያሰበውን፥ የወደደውን ሁሉ ማድረግ የሚችል ብርቱ ኃይል መሆኑን ለማሳየት ነው።

በኤፌ 1፡19 "የኃይሉ ታላቅነት"፡ ይህ የእርሱ ኃይል ከሌሎች ኃይላት ጋር ሲነጻጸር እንደሚበልጥ ያሳያል።

ኤፌ 1፡20-21 “የብርታቱ ጉልበት”፡ (አዲሱ መደበኛ፡ ቁ 19 ይህም ኃይል እንደእርሱ ታላቅ ብርታት)፡ ታላቅ የሆውነ ኃይሉ ብቻ ሳይሆን፥ ብርታቱም (የኃይሉ አቅም) ታላቅ ነው። የብርታቱ አቅም/ትልቅነት ምን ያህል እንደሆነ የታየው ይህ ኃይል በክርስቶስ የሰራውን በመናገር ነው፡-“ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል።”

በኤፌሶን 1፡18 የተሰጣቸውን ኃይል እንዲያውቁ ብቻ ሳይሆን፥ በዚያ ኃይል እንዲበረቱ ደግሞ በኤፌ 3፡16 ይጸልያል፡ “በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ።” በውስጣቸው በኃይሉ የሚያጠነክራቸው በውስጣቸው ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው።

በመጨረሻም በኤፌ 6፡10 “በኃይሉ ችሎት የበረታቹ ሁኑ” ሲል ራሳቸው በውስጣቸው ላለው ለመንፈስ ቅዱስ ስራ እንዲሰጡ እያዘዛቸው ነው። ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳው፥ እኛንም ከሞት ያስነሳን፥ ውስጣችንን ለውጊያ ብቃት የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱ ኃይል ይሰጠናል።የእኛ ኃይል ሲያልቅብን፥ ሲደክመን፥ እግዚአብሔርም የደከመው እንዳይመስለን። ይልቁን የእርሱን ኃይል በጸሎት ልንፈልግ እንደሚገባን ያሳየናል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በኤፌ 1፡18-22 ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ”የኃይሉ ታላቅነት “ለምናምን” ነው ሲል ስለእምነት አስፈላጊነት ምን ይነግረናል?
2. በኤፌ 1፡20-22 ለቅዱሳን የተሰጠውን ኃይል በክርስቶስ ከሰራው ኃይል ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ ኃይል በክርስቶስ የሰራውን ሥራ በዝርዝር ተነጋገሩ።

3. በዚሁ በኢፌ. 1:20-22 መሰረት ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳው ኃይል በእኛ ውስጥ መኖሩ፥ በውስጣችን ምን ሊፈጥር ይገባል? ይህን እውነት መረዳት የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው?
4. ኤፌ 3፡16-19 በመመልከት በውስጥ ሰውነት መንጠንከር ምን እንደሚመስል ተነጋገሩ።
5. በኤፌ 3፡20 "እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥" የሚለው ስለእግዚአብሔር ኃይል ምን ያስተምረናል?
6. በኤፌ 6፡10 ደግሞ በኃይሉ የበረታቹ ሁኑ ሲል ምን እንዲሆኑና እንዲያደርጉ ነው የሚያዛቸው? እስከ አሁን ባየነው፥ በኃይሉ መበርታት ምን ይመስላል?
7. በኤፌ 4:7 መሠረት ስናምን ኃይል የምናገኘው ከየት ነው? በማብራራት ተወያዩበት።
8. ከዛሬው ጥናት በውስጡ ሰውነታችን ጥንካሬ ምንጭና አስፈላጊነት በተመለከተ ዋናው ነገር ምንድ ነው?

***መደምደምያ***

በዕየለቱ በውስጥ ሰውነታችን እንድንበረታ፥ መንፈስ ቅዱሱ እንዲያበረታን ልንጸልይና ለመንፈስ ቅዱስ አመራርን ግዛት ራሳችንን ልናስለምድ ይገባል።

## ጥናት አስራ አራት

**የንባብ ክፍል፡-** ኤፌሶን 6፡11-12

**ርዕስ፡-** “ዋናው ጠላት”

***ዓላማ፡-*** ዋናው ጠላታችን ማን መሆኑን አሳታውሰን፥ ውጊያችንን ከእርሱ ጋር እንድናደርግ ለማሳሰብ።

***መግቢያ፡-*** ባለፉት ሁለት ጥናቶች የእኛ ጦር መሪ በሆነው በጌታና እርሱ በሚሰጠን ኃይል እንዴት ልንበረታ እንደሚገባን አይተናል። በዛሬው ጥናት ደግሞ የምንዋጋው ጦርነት ከማን ጋር እንደሆነና ጠላትም እንዴት እንደሚዋጋን እንማራለን። ጠላቱን የማያውቅ ተዋጊ ሽንፈት ብቻ ነው እድሉ። ጠላቱን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ደግሞ የጠላቱን ስልት የማያውቅ ተዋጊም እድሉ ሽንፈት ብቻ ነው። ስለዚህ ጠላታችን ማን እንደሆን፥ የሚሰራባቸው ሰራዊቶቹ ማን እንደሆኑና የሚዋጋበት ስልቱ ምን እንደሆነ እናያለን።

***ማብራሪያ፡-***

1. በቁጥር (ኤፌ 6፡11-12 መሠረት ጦርነቱን ከማን ጋር እንደሆነ ይነግረናል። የጦሩ ዋናው መሪ ዲያቢሎስ እንደሆነ እናያለን። ዲያቢሎስ የሚለው የሰይጣን ሌላኛው ስም ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዲያቢሎስ ስለሚሰራቸው ስራዎች በዝርዝር ተጽፎ እናገኛለን። ለምሳሌ፡ ሐዋ 13፡10 የጽድቅ ጠላት፥ የቀናውን መንገድ ከማጣመም የማያርፍ ነው። እንዲሁም በማቴ 4፡1 እና በ1ኛ ዮሐ 3፡8 ኃጢአትን የሚያደርግ፥ እኛንም ኃጢአት ማስደረግ የሚፈልግ **ነው**። ኃጢአት እንድናደርግ ይፈትነናል። ለዚህ ውጊያው ደግሞ እኛ እምቢ በማለት እንደምንዋጋው ይነግረናል። እምቢ ስንለው ከእኛ ይሸሻል።

   በኤፌ 4፡27 መሠረት ትንሽ ቀዳዳ ካገኘ አስፍቶ ይጠቀምበታል። ስለዚህም ምንም እድል/የእግሩ መረገጫ እንዳንሰጠው ታዘናል። ራዕ 12፡9-11ን ደግሞ ስናይ ኃጢያት ስናደርግ ይከሰናል። ተጸጽተን ከጌታ እንድንርቅ ሊያደርግ ይታገላል።

   1ኛ ጴጥ 5፡8 ደግሞ “የሚውጠውን ፍለጋ በአለም ሁሉ ይዞራል” ይላል። ይህ ክፍል እንደሚነግረን በአንድ ጊዜ በሁሉ ቦታ መሆን ስለማይችል ይዞራል። አንዱ

ፈተናውን እምቢ ሲል ይሸሻል። ከዚያም ወደሌላው ይዞራል። በመዞር ሂደት ውስጥ ፈቃዱን የሰጠውን ሰው ያጠቃል።

2. "**ዲያቢሎስ ዋና አዛዥ ነው" ስንል የሚታዘዙት** አሉት ማለት ነው። እንዲሁም በቁጥር 12 ላይ እንደምናየው በዲያቢሎስ ትዕዛዝ ስር ያሉ ሠራዊቶች አሉ። እነዚህም ኃይላት፣ስልጣናት እና ርኩሳት መናፍት ናቸው። እነዚህን በተለያየ ስፍራ አሰማርቶ፥ የዚህን ዓለም ኃያላንና ስልጣናትን እንዲሁም የተለያዩ ሰዎችን በመጠቀም የሚሰራባቸው ሠራዊቶች ናቸው። ዲያቢሎስ ሠራዊቶች እንዳሉት፥ ጌታም ሰራዊቶች አሉት። በዚህ ክፍል መሠረት፥ የጌታ ሠራዊቶች አማኞች ነን። ጌታ ዋናው የሠራዊቱ አለቃ ነው። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የጌታ አካሉ ናት። መንፈሳዊ ውጊያን በግል ብቻ ሳይሆን፥ ከቅዱሳን ጋር በአንድነት ልንዋጋ እንደሚያስፈልግ ከዚህ ልንማር እንችላለን።
3. ሽንገላ ('ተንኰል') **ሰይጣን** ክርስትያኖችን የሚያጠቃበት ዋነኛ መሳሪያ ነው። በኤፌ 4፡14 ሽንገላ (ተንኮል) የስህተት አስተማሪዎች የሚያደርጉት፥ ሰዎችን ከእውነት፣ ከጽድቅና ከጌታ መንገድ የሚያወጣ ነው። ይህም የተጠና የማታለል ዘዴ ነው። ድያብሎስ ተንኮሉ የሰውን ድካም አጥንቶ ሰዎችን ለማታለል እጅግ መጣር ነው። ይህም በእግዚአብሔር ቃል ካልታጠቀን ይጥለናል።
4. ኤፌሶን 2፡1-3 እንደምናየው፥ ሰይጣን በዚህ አለም ውስጥ እንዲሰራ አቅም የሰጠው የሰዎች አለመታዘዝ ነው። አለመታዘዝ ሰዎችን ለሰይጣን እንዲገዙ ያደርጋቸዋል።
5. መጋደላችን ከሰው ጋር አይደለም ማለት ሰው እኛን ለመጉዳት ምንም አያደርግም ማለት አይደለም። በመንፈሳዊ ውጊያ ዋናው ዓላማ የሚደረገው ዲያቢሎስ ቢሆንም፥ ሰውን ግን ሊጠቀም እንደሚችል መዘንጋት የለብንም። ዲያቢሎስ ሰውን ይጠቀማል።
6. የኢየሱስን ህይወትና አገልግሎት ስናጠና ዲያቢሎስ ራሱ ኢየሱስን ብቻውን አግኝቶ ፈትኖታል (ማቴ 4፡1-11)።ፈተናውን እምቢ በማለት ሲቃወመው፥ ከእርሱ ሸሽቶ ሄደ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሚቀርበው፥ ከሌሎቹ ሁሉ መንፈሳዊ ብስለት በነበረው በጴጥሮስም በኩል ፈትኖታል(ማቴ 16፡15-23)። ስለዚህ ውጊያችን ከሰው ጋር

አይደለም ሲል፥ ሰይጣን ሰውን አይጠቀምም ማለት ሳይሆን፥ ሰውን እየተጠቀመበት ያለውን ዋናውን ሰይጣንን እራሱን እንድንዋጋ ለማድረግ ነው። ዋናው ሰው ነው ብለን ከሰው ጋር መጋደል መፍትሔ አያመጣም። አንድን ሰው ብንጋደል፥ በሌላም በኩል መምጣቱ አይቀርም። ዋናውን ከሰው ጀርባ ከተዋጋነው ግን ይሸሻል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኤፌ. 6:11-12 መሰረት መንፈሳዊ ጦርነቱ ከማን ጋር ነው? በተጨማሪም በኤፌ 4፡27 መሰረት ለዲያብሎስ ዕድል ፈንታ መስጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩ።
2. በማቴ 4፡1-11 ዲያቢሎስ ኢየሱስን ለመፈተን የተጠቀመው አጋጣሚ/እድል ፈንታ ምን ነበር?
3. ኤፌ 6፡11 ላይ የዲያቢሎስ የመዋጊያ ስልት "ሽንገላ" ('ተንኰል') መሆኑን ስናይና ኤፌ 4፡14 ደግሞ "ሽንገላ" (ተንኮል) የስህተት አስተማሪዎች የሚያደርጉት እንደሆነ ስንመለከት ስለዲያቢሎስ የውጊያው ስልትና እኛ ሊኖረን ስለሚገባ ምላሽ ተወያዩ።
4. በኤፌ 6፡12 እንደምናየው በዲያቢሎስ ትዕዛዝ ስር ሆነው እኛን የሚዋጉንን ጠላቶቻችን ምን ተብለው እንደተቀሱ ተነጋገሩ። ምን እንረዳለን።
5. በኤፌሶን 2፡1-3 መሠረት ጠላት በአለም እንዲሰራ የሚያስችለው ነገር ምንድን ነው? ከዚህስ ስለጠላት መጠቀሚያ መሳሪያና አቅም ምን መማር እንችላለን?
6. በኤፌ. 6:12 መሰረት "መጋደላችን ከደም እና ከሥጋ ጋር አይደለም" ማለት ምን ማለት? ሰውን አይጠቀምም ማለት ነው? ከማቴ 16፡15-23 ጋር በማነጻጸር በስፋት ተነጋገሩ።
7. በሉቃ 23፡34 መሰረት በመስቀል የሰቀሉትንና እንዲሰቀል ያደረጉትን ሰዎች "የሚያደርጉትን አያውቁምና" ማለት ምን ማለት ነው? ሰይጣን ተጠቀመባቸው የምንላቸውን ሰዎች፥ይቅር ማለትስ የሚከብደን ለምንድን ነው?

8. 1ዮሐ. 3:8 እና ራዕይ. 12:9-11ን እንደ ምሳሌ ብንወስድ የኢየሱስ ክርስቶስ ውጊያው ከማን ጋር ነበር? የኢየሱስ ደቀ መዝሙር እንደመሆናችን፥ የኢየሱስን አርአያ እየተከተልን ነው? እንዴት?
9. በ2ኛ ቆሮ 2፡11 ላይ "በሰይጣን እንዳንታለል፥ የእርሱን ሃሳቡን አንስተውምና" ሲል፥ በዚህ ክፍል ሰዎችን የሚያታልልበት የሰይጣን ሃሳብ ምንድ ነው?

***መደምደምያ***

ዲያቢሎስ በተለያዩ ሰራዊቶች፥ ሰዎችንም በመጠቀምና በተለያየ የሽንገላ መንግድ እንደሚዋጋን አውቀን፥ የዕለት ተለት ውጊያችንን ከሰዎች ጀርባ ሆኖ የሚሰራውን እርሱን እንጂ ሰዎችን መጋደል እናቁም።

ጥናት አስራ አምስት

**የንባብ ክፍል፡-** ኤፌሶን 6፡13

**ርዕስ**፡- "የውጊያ ቀን"

**ዓላማ፡-** *መንፈሳዊ ውጊያ ክፉው በእያንዳንዱ ቀን እኛን እንደግለሰብም ሆነ እንደ ቤተክርስቲያን ለማጥቃት የሚሰራበት ጊዜ መሆኑን አውቀን፥ ለእያንዳንዱ ቀን ውጊያ የተዘጋጀን እንድንሆን ለማሳሰብ*

***መግቢያ፡-*** ባለፈው ጥናት ዋናው ጠላታችን ማን እንደሆና እንዴት እንደሚሰራ አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ ጠላታችን ዲያብሎስ እኛን ስለሚዋጋባቸው ቀኖች እናያለን። እያንዳንዱ ቀን ክፉው የሚሰራበት ቀን እንደሆነ፥ ነገር ግን በእያንዳንዱ ቀን እንደማይዋጋን ግልጽ ነው። ከእነዚህ ክፉ ከሆኑ ቀኖች ውስጥ አንዱን ቀን ለአንዱ፥ ሌላን ቀን ለሌላው እንደ አመቺነቱ እያየ እንደሚዋጋንም እንመለከታለን። ሁል ጊዜ ውጊያ አለመኖሩ ሳያዘናጋን፥ ለሚመጣው ክፉ ቀን የተዘጋጀን መሆን እንዳለብንም እንመለከታለን።

***ማብራሪያ፡***

1. በኤፌ 5፡16 መሰረት "ቀኖች ክፉ ናቸው" የሚለውን አሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ? ዘመኑንመንፈሳዊ ውጊያ ምን
2. በኤፌ 6፡13 እና ኤፌ 5፡16 መሰረት በክፉ ቀንና በክፉ ቀኖችና መኃል ያለው አንድነትና ልዩነት በተመለከተ ተወያዩበት።
3. ሦስት አይነት ክፉ ቀን በኢየሱስ ህይወት እናያለን። በእግዚአብሔር እውቀትና ፈቃድ ከእነዚህ አንዱ ወይም ሁሉም በህይወታችን የሆነ ጊዜ ሊመጣ/ጡ ስለሚችሉ ልናውቃቸውና ተገቢውን ዝግጅት ልናደርግ ይገባል።
   - የመጀመሪያው የክፉ ቀን በማቴ 4፡1-11 ተጽፏል። ከዚህ ክፍል እንደምናየው ሰይጣን ራሱ ቀርቦ እየሱስን የፈተነበት ቀን ነው።

- ሁለተኛው የከፉ ቀን በማቴ 16፡21-26 ይገኛል። ከዚህ ክፍል ስለሁለተኛው አይነት የከፉ ቀን ማለትም በሽማግሌዎች፣ በካህናትና በአለቆች መከራን መቀበልና መገደል ነው።
- በኢየሱስ ህይወት የምናየው ሦስተኛው ክፉ ቀን በይሁዳ አሳልፉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በመስቀል እስከተሰቀለበት ድረስ ያለው ነው (ለምሳሌ ሉቃ 22-23 መመልከት ይቻላል። በተለይ ሉቃ 22፡3 ይመልከቱ)።

4. በማቴ 6፡34 "ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል" ሲል ስለሚመጣው የከፉ ቀን ስናስብ ማድረግ የሌለብን ነገር ይነግረናል። ይህም በጌታ መደገፍና አለመጨነቅ ነው።
5. በ2 ቆሮ 6፡2 "በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፤ እነሆ፥ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ፥ የመዳን ቀን አሁን ነው።" ከዚህ ክፍ "የመዳንን ቀንና" ከከፉ ቀን ጋር አነጻጽረን ማየት እንችላለን።
6. ምሳሌ 27፡12 "ብልህ ሰው ክፉን አይቶ ይሸሸጋል፤ አላዋቂዎች ግን አልፈው ይጐዳሉ።" ይላል። በዚህ ክፍል መሠረት ብልህና አላዋቂ የሚያመሳስላቸውና የሚያለያያቸው ነገር ግልጽ ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኤፌ 5፡16 መሰረት "ከፉ ቀን" መቼ ነው? (ሁሌም ወይስ እያንዳንዱ ቀን)። "ቀኖች ከፉ ናቸውና" ማለት ምን ማለት ነው?
2. ኤፌሶን 6፡13 "ከፉ ቀን" ሲል በከፉ ቀንና "ከፉ ቀኖች" መኃል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
3. የማቴ. 4:1-11 በማንበብ በዚህ ጥናት በተሰጠው አጭር ማብራሪያ መሠረት በጌታ ህይወት ከሆነው የመጀመሪይው "ከፉ ቀን" ምንድ ነው? የጥናቱን ማብራሪያ ተመልከቱ።

4. ለማቴ 16፥21-26 በዚህ ጥናት በተሰጠው አጭር ማብራሪያ መሠረት በጌታ ህይወት ሁለተኛው “ከፉ ቀን” ምንድን ነው? በመጀመሪያውና በሁለተኛው ቀን ያለው ልዩነትና አንድነት ተንጋገሩ።
5. እንዲሁም በሉቃ. 22:3 እና 22:23 መሰረት ሦስተኛው “ከፉ ቀን” ምን ነበር? ከሁለቱ ቀናት ጋር ያለው ግንኙነትና ልዩነት ተነጋገሩ።
6. በማቴ 6፥34 “ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል” ሲል ስለሚመጣው የከፉ ቀን ስናስብ ማድረግ የሌለብን ምንድን ነው? ማድረግ ያለብንስ?
7. በ2 ቆሮ 6፥2 መሰረት “የመዳንን ቀን” “ከከፉ ቀን” ጋር በማነጻጸር ተወያዩ። “የመዳን ቀን” አሁን መሆኑ ምን ተስፋና ምክር ሊሰጠን ይችላል?
8. ምሳሌ 27፥12 “ብልህ ሰው ከፉን አይቶ ይሸሸጋል፤ አላዋቂዎች ግን አልፈው ይጐዳሉ” ይላል። ከዚህ ክፍል ስለ ከፉ ቀን ምን መረዳትና ማድረግ ይጠበቅብናል?
9. ባጠቃላይ ከዛሬው ጥናት ምን እንማራለን።

***መደምደምያ***

“ከፉው ቀን” በህይወታችን የሚመጣበት ጊዜ አለ። ነገር ግን አሁን የመዳን ቀን/ሰዓት መሆኑን አውቀን፥ የሚመጣውን የከፋት ቀን እያሰበን ከመጨነቅ ይልቅ፥ ሊያድነን አሁን አብሮን ላለው ጌታ ራሳችንና ህይወታችንን ልንሰጥ፥እርዳታውን ልንጠይቅ ይገባናል።

## ጥናት አስራ ስድስት

**የንባብ ክፍል፦** ኤፌሶን 6፡11-13

**ርዕስ**፦ የእግዚአብሔር እቃ ጦር

**ዓላማ፦**የጠላትን የመዋጊያ መንገዶች ሁሉ የምናሸንፍበት እግዚአብሔር የሰጠን ብዙ ዓይነት መሣሪያዎች እንዳሉን እንድናውቅና ዓላማቸውንም ምን እንደሆነ እንድንረዳ ይሆናል።

**መግቢያ፦** የባለፉት ሁለት ጥናቶች ስለዋነኛው ጠላታችንና ስለውጊያው ቀን አጥንተናል። ከዛሬ ጀምሮ ደግሞ በሚቀጥሉት ጥናቶች ሁሉ የምናየው **ጠላትን የምንዋጋበትን መሣሪያዎች** ነው። የዛሬው ጥናት ለሚቀጥሉት ጥናቶች ሁሉ መሠረት ነው። በዚህ ጥናት የጦር መሣሪያዎቹ ከየት እንደመጡ፥ ለምን ዓላማ እንደተጡን እናያለን። ኢየሱስ ጠላትን ያሸነፈበትን የጦር መሣሪያ ሁሉ አንስተን ልንዋጋ እንደሚገባን እናያለን።

**ማብራሪያ፡**

1. የምንዋጋባቸው መሣሪያዎች "የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር" የተባሉትበት ምክንያት ሁለት ነው።
1. አንደኛ፡ እግዚአብሔር (ኢየሱስ) ራሱ ለውጊያ የሚጠቀምባቸው ስለሆኑ ነው።
2. ሁለተኛ፡ ከእግዚአብሔር የምንቀበላቸው እንጂ፥ እኛ እራሳችን ሰርተን የምናገኛቸው መሣሪያዎች ስላይደሉ ነው።
2. "የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ" ሲል የጦር መሣሪያዎቹ ብዙ መሆናቸው ያሳያል። ብዙ መሆን ያስፈለገበት ምክንያት መረዳት ያስፈልጋል። የጠላት የመዋጊያው ስልቱ ብዙ ስለሆነ የእኛም የመዋጊያ መንገድ ብዙ መሆን አለበት።ጠላትን በአንድ መሳርያ ብቻ ማሸነፍ አይቻልም።በአንድ ወይም በተወሰነ መሳሪያ ላይ ብቻ ስናተኩር፥ ጠላት በድካማችን/በጉድለታችን ሊያገኘን ይችላል።የጠላት ስልቱ አንዱ ማታለል ነው። በአንድ ወቅት ስንዋጋ የሰራልን አንድ መሳርያ ብቻ ካለ ሁሌ ያንን ብቻ እየተጠቀምን

እንድናሸነፍ ይፍልጋል፤ምክንያቱም የውጊያ መንገዱን ቀይሩ በመምጣት ሊያሸንፈን ስለሚፈልግ ነው።

3. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ግዙ ወይም ስሩ ሳይሆን **“ልበሱ”** (ቁ. 11) እና “አንሱ” (ቁ. 13) ነው የተባልነው። “አንሱ” የሚለውን አዲሱ መደበኛ “ልበሱ” ነው የሚለው። ነገር ግን ከክፍሉ እንደምናየው አንዳንዱ የጦር መሳርያ የለበስ አንዳንዱ ደግሞ የሚነሳ ነው። የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ግዙ ወይም ስሩ ሳይሆን “ልበሱ” እና “አንሱ” መባሉ፥ መሣሪያዎቹ እኛ የምንሰራቸው፥ የምንገዛቸው ሳይሆኑ፥ ከእግዚአብሔር የተሰጡን መሆናቸውንና ከእኛ የሚጠቀው መቀበልና መልበስ ወይም ማንሳት ብቻ ነው።

4. የጦር መሣሪያዎቹ የምንለብስበትና የምናነሳበት ሁለት ዓላማዎች አሉ።
    - በቁጥር 11 ላይ የተገለጠው የመጀመሪያው ዓላማ “መቃወም” ወይም “መቋቋም” ነው። ይህን ትዕዛዝ በልምድ የጌታን ስም እየጠራን ከመገሥጽ ጋር እናያይዘዋለን። በዚህ ክፍል መሠረት “መቃወም” ወይም “መቋቋም” በአንደበታችን “በኢየሱስ ስም ሂድ” ማለት ብቻ እንደይደለ የሚያሳየን እውነት ነው። “በኢየሱስ ስም ሂድ” ማለት ካልሆነ ምን ማድረግ ያለብን? ከኢየሱስ ህይወት ግን የምንማረው፥ ኢየሱስ ራሱ የተቃወመው ፈተናውን እንደ እግዚአብሔር ቃል እምቢ በማለት ነው።የኢየሱስን ስም መጥራት ዋጋ አለው። ነገር ግን ስሙን ከመጥራት በተጨማሪ፥ ትክክለኛውን የመዋጊያ መንገድ ካልተጠቀምን፥ ለጠላት ሽንገላ ልንወድቅ እንችላለን።
    - ሁለተኛው የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር መልበስና ማንሳት የሚያስፈልገበት ዓላማ በቁጥር 13 መሠረት “መቆም” ነው። በዚህ አውድ መሠረት መቆም ማለት “ክርስቶስን በማመን መቀጠል፥ ለጠላት ሽንገላ እሺ አለማለት፥ ፈተናው አልፎ በአሸናፊነት ኑሮን መቀጠል ማለት ነው።

5. “ሁሉን ፈጽማችሁ መቆም” ሁሉን ፈጽማችሁ፡ ሁሉን የሚለው የጠላትን ልዩ ልዩ የሆኑ የሽንገላ መንገዶችን ሲሆን ‘ፈጽማችሁ’ ሲል ለእያንዳንዱ ተገቢውን ምላሽ ሰጥተን ማለት ነው።
6. በቁጥር 11-13 መሠረት የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ የምንለብሰውና የምናነሳው በክፉ ቀን እንዲረዳን ቢሆንም፥ ክፉ ቀን ሲመጣ ግን አይደለም። አስቀድመን መልበስና ማንሳት አለብን።

**የመወያያ ጥያቄዎች (ጥናቄዎቹን ለመመለስ የጥናቱን ማብራሪያ ማንበብ በጣም አስፈላጊ ይሆናል)**

1. በኤፌ. 6:11-13 የምንዋጋባቸውን የጦር መሣሪያዎች “የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር” ይላቸዋል።ለምን የእግዚአብሔር ተባሉ?
2. በኤፌ. 6:11-13 መሰረት ለምን ከአንድ በላይ መሣርያ አስፈለገ? በአንድ መሣሪያ ብቻ ውጊያውን ማሸነፍ ያልተቻለው ለምንድን ነው? ከጥናቱ ማብራሪያ መመልከት ጥሩ ይሆናል።
3. በኤፌ. 6:11 “ልበሱ” ሲል ነገር ግን በኤፌ. 6:13 “አንሱ” ይላል። በመልበስና በማንሳት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? “ልበሱ” እና “አንሱ” መባሉ ምን ሊያስተምረን ይገባል?
4. ኤፌ 6:11ን አስመልክቶ በተጻፈው ማብራሪያ መሰረት መቃወም ማለት ምን ማለት ነው? በማብራሪያው መሠረት “በኢየሱስ ስም ሂድ” ማለት ካልሆነ ምን ማድረግ ነው? እስካሁን ባጠናነው ጥናት መሠረት እና ከጌታችን ከኢየሱስ ከራሱ ዲያቢሎስን ስለ መቃወም ወይም መቋቋም ምን ተረዳን?
5. በኤፌ. 6፥13 በዚህ አውድ መሠረት “ሁሉን ከፈጸሙ በኋላ መቆም” ማለት ምን ማለት ነው? ከዚህ በመነሳት ጠላት እኛን የሚዋጋበት አንዱ ግቡ ምንድን ነው ማለት ይቻላል?

6. በቁጥር 13 ላይ "ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ" ሲል "ሁሉን" እና "ፈጽማችሁ" ሲልስ ምን ማለቱ ነው? ተነጋገሩ።
7. ኤፌ 6፡11-13 መሠረት **የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር** ሁሉ አስቀድመን መልበስና ማንሳት እንዳለብን ማወቃችን ለምን ይጠቅመናል?

በዛሬው ጥናታችን መሠረት እኛ እንደ አማኞች ምን ኃላፊነት አለብን? ምንስ ማድረግ አለብን? ተነጋገሩ።**መደምደምያ፡-**

**አማኞች** ዲያቢሎስን የምንዋጋው መሣሪያዎች ሰው ሰራሽ አይደሉም። እኛም ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ ልንዋጋው አንችልም። ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱ ያዘጋጀልንን መሣሪያ ለብሰንና አንስተን ጠላትን ለመዋጋት ዝግጁ ልንሆን ይገባል።

## ጥናት አስራ ሰባት

**የንባብ ክፍል፡-** ኤፌሶን 6፡14

**ርዕስ**፡- እቃ ጦር አንድ፡ "እውነት"

**ዓላማ፡-** እውነት በአዕምሮ የሚታወቅ እውነታ እና በኑሮ የሚገለጥ እውነተኛነት መሆኑን ለማስገንዘብ

**መግቢያ፡-**ከዚህ ጥናት ጀምሮ ለሚቀጥሉት አምስት ጥናቶች፥ እያንዳንዱን የእግዚአብሔር የጦር ዕቃዎች በዝርዝር እናያለን። በዚህ ጥናት የምናየው "እውነት"ን ነው። እውነት ሁለት ገጽታ እንዳለው እናያለን። እውነትን አንደ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች አድርገን መረዳት አለብን። የመጀመሪያው ገጽታ እውነታ (fact) ነው። ይህ በአዕምሮአችን ልናውቀው የሚገባ ነው። ሁለተኛው ገጽታ እውነተኛነት (truthfulness) ነው። ይህ በባህሪያችን ልንኖረው የሚገባን ነገር ነው። ሁለቱም ጥብቅ ግንኙት አላቸው። እውነተኝነት እውነትን ከማወቅ የሚመጣ ነው።

**ማብራሪያ**

1. በኤፌ 6፡14-15 የተዘረዘሩትን የጦር ዕቃዎች ታጥቀው እንዲቆሙ ያዛቸዋል። በዚህ አውድ "መቆም" ማለት ዝግጁ፣ የጸና መሆን ማለት ነው። ታጥቆ መቆም የተዘጋጀ እና ጽኑ የሆነን ሰው ያሳያል።
2. በኤፌ 1፡13 "የእውነትን ቃል" በማለት የሰሙትን ቃል ይገልጻል።ይህ የሰሙትን እውነተኛ ወንጌል ያመለክታል። በዚህ ቁጥር "እውነት" ማለት ከእግዚአብሔር የሆነ፥ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ማለት ነው። እግዚአብሔር ስለእራሱ፥ ስለልጁ፥ ስለሰው፥ ስለኃጢያት ወዘተ የተናገረውን፥ የገለጠውን እውነታ የሚያመለክት መለኮታው እውቀት ነው።
3. በኤፌ 4፡21 ላይ "በእርግጥ ሰምታችሁታልና፥ እውነትም በኢየሱስ እንዳለ በእርሱ ተምራችኋል" ይላል። እውነት በኢየሱስ መሆኑን ማወቃቸው፥ አይናቸውን በኢየሱስ ላይ እንዲያደርጉ ያደርጋቸዋል። እውነት የተገለጠው በኢየሱስ ነው።

ሌሎች ከኢየሱስ ተቀብለው ለእኛ አስተላለፉልን። በኤፌ 4፡17-15 መሠረት እውነትና እውነተኛነት ከኢየሱስ የምናገኛቸው ነገሮች ናቸው።

4. ከኤፌ 4፡25 አንጻር እውነትን እርስ በእርስ መነጋገር ያስፈልጋል። የአንድ አካል ብልቶች ስለሆንን፥ አንዱ ብልት ከሌላው ብልት ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ እርስ በእርሳችን እውነትን ማውራት አለብን። ሰዎች እውነታችንን ሲያውቁ ያወሩብናል ብለው ብዙዎች እውነትን መናገር ይፈራሉ። ሲያወሩብን እውነታውን ሌሎች ያውቃሉ። ይህ ደግሞ እኛ ራሱ ማድረግ ያለብን ነገር ነው። መናገር የማይፈልጉ ሰዎች እውነትን መነጋገር የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን፥ ትዕዛዝ መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል። እውነትን ከአማኞች መደበቅ ከራስ እንደመደበቅ መሆኑን መረዳት አለብን።
5. በኤፌ 4፡24 "ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" ሲል፥ እውነትን ከጽድቅና ከቅድስና ጋር አያይዘን እንድንለብስ ያዘናል። እውነትን በዚህ ክፍል የምናውቀው እውነታ ሳይሆን፥ የምንኖረው እውነተኛነት ነው። በእግዚአብሔር እና በዲያቢሎስ መካከል ያለው ልዩነት እግዚአብሔር እውነተኛ፥ ዲያቢሎስ ደግሞ የሃሰት አባት ነው።እግዚአብሔር ለመምሰል እንደተፈጠሩ ሰዎች፥ እውነትን መነጋገር ይኖርብናል።
6. እንዲሁም ደግሞ በኤፌ 5፡9-10 "የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፥ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤" ይላል። ብርሃን የተደበቀውን ይገልጣል። ስለዚህም እውነትን ያፈራል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በኤፌ 6፡14-15 መሠረት አማኞች ምን እንዲያደርጉ ነው የታዘዙት? በዚህ አውድ "መቆም" ማለት ምን ማለት ነው? እውነት ከትጥቅ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
2. በኤፌ 1፡13 "የእውነትን ቃል" በማለት የሰሙትን ቃል መግለጡ ለምንድን ያስፈለገው? በዚህ ቁጥር ስለ "እውነት" ምን እንማራለን?

3. ኤፌ 4፡21 “በእርግጥ ሰምታችሁታልና፥ እውነትም በኢየሱስ እንዳለ በእርሱ ተምራችኋል” ይላል። እውነት በኢየሱስ መሆኑን መማራቸው ምን ይጠቅማቸዋል? በኤፌ 4፡17-15 ባለው አውድ በማየት ጥቅሙን ተነጋገሩ።
4. ኤፌ 4፡24 እውነትን ከጽድቅና ከቅድስና ጋር ተይይዞ እንድንለብስ ያዘናል። እውነትን በዚህ ክፍል እንዴት መልበስና መረዳት እንችላለን?
5. ከኤፌ 4፡25 አንጻር እውነትን እርስ በእርስ መነጋገር ለምን ያስፈልጋል? ይህ ከአማኝ ማንነት ጋር ምን ግንኙነት አለው?
6. ኤፌ 5፡9-10 “የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ **በእውነትም** ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፥ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤” ሲል፥ የብርሃን ጥቅምና ውጤቱ ምንድ ነው?
7. በኢሳ 11፡5 ታማኝነት የመሲሁ፥ የኢየሱስ የጎን መታጠቂያ መሆኑን ይነግረናል። ኢየሱስ የታጠቀውን መታጠቅያ አድርጉ መባላችን ምን ሊያስተምረን ይገባል? ለእኛስ ምን ይጠቅማል?
8. ካዛሬው ጥናት ስለ እቃ ጦር ማለትም ስለ “እውነትን” አስፈላጊነቱ ምን ተረዳችሁ?

**መደምደምያ፡-**

እንደ እግዚአብሔር ልጆች በክርስቶስ አስቀድመን የሰማነውን የእውነት ቃል አጥብቀን ልንይዝ፥ ይህም የእውነት ቃል ከእኛ የሚጠብቅብንን እውነተኛነት ልንለማመድ ይገባል።

## ጥናት አስራ ስምንት

**የንባብ ክፍል፡-** ኤፌሶን 6፡14

**ርዕስ**፡- እቃ ጦር ሁለት፡ "ጽድቅ"

**ዓላማ፡** ጽድቅ እግዚአብሔር የሚቆጥርልን እኛም የምንለማመደው መሆኑን ለማስገንዘብ

**መግቢያ፡-** በዚህ ጥናት ሁለተኛ የሆነውን የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር "ጽድቅን" እናያለን። ባለፈው ጥናት እውነት ሁለት ገጽታ እንዳለው አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ የ"ጽድቅ" ሁለት ገጽታ እናያለን። የመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ከእምነት የተነሳ የሚቆጠርልን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የተለማመድነው፥ የምንኖረው ጽድቅ ነው። ጽድቅን ልበሱ ስንባል፥ እነዚህን ሁለት የጽድቅን ገጽታዎች ማሰብ አለብን።

**ማብራሪያ፡-**

1. በኤፌ 6፡14-15 **"የጽድቅን ጥሩር"** እንድንለብስ ያዘናል። ይህ "ጽድቅ" ሁለት ገጽታ አለው። የመጀመሪያው በሮሜ 3፡20-25 ይገኛል፡፡ እንዲህ ይላል "20-21 ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፥ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም። 22 ስለዚህ ደግሞ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። 23 ነገር ግን። ተቈጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም፥ ስለ እኛም ነው እንጂ፤ 24-25 ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው። " በዚህ ክፍል መሠረት፥ "ጽድቅ" በእምነት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው፥ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያት የሌለብን ሆነን መቆጠር ነው። ከክስና ከፍርድ ነጻ መሆን ነው!
2. ሁለተኛው የጽድቅ ገጽታ በ1ኛ ዮሐ 2፡29 እን 3፡7 እንዲሁም 3፡10 ይገኛል። እነዚህን ክፍሎች ስናነብ የምንማራው ሁለተኛው የጽድቅ ገጽታ ከኑሮ ወይም ከድርጊት ጋር የተያያዘ ነው። ይህም ማለት ጽድቅ እግዚአብሔር የሚቆጥርልን ግን

እኛ የማንኖረው ብቻ ሳይሆን፥ ፍጹምም ባንሆን በተወሰነ መልኩ በዚሁ ምድር መለማመድ የምንጀምረው ነው። ይህ ግን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ለመቆጠር ሳይሆን፥ ጻድቅ ሆነን ስለተቆጠርን በሌሎች ዘንድ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ የምንመሰክርበት ነው።

- በኤፌ 4፡24 ጽድቅ እውነተኛ ነው (በድሮው 'ለእውነት ነው') ይላል። ይህ ማለት ያልሆነውን እንደሆንን የምናሳይበት፥ ሳይሆን በእርግጥ የሆነውን ሆነን የምንገኝበት ነው። አንዳንድ ሰዎች "እውነተኛ" በመሆን ሰበብ፥ ኃጢያትን በግልጥ በማድረግ ራሳቸውን ከጸጸትና ከክስ ነጻ ሊያወጡ ይፈልጋሉ። ነገር ግን፥ የታዘዝነው። ጽድቅን እንድንኖረው፣ሳናስመስል እንድናሳይ እንጂ፥ ኃጢያትን በግልጥ እንድንለማመድ አይደለም።
- ኤፌ 4፡24 ጽድቅና ቅድስና እግዚአብሔርን ለመመሰል ይረዱናል። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው። የሚሰራው ሁሉ እርሱ በቃሉ ከተናገረን ጋር የሚሄድ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ማለትም ከአለም የተለየ ማለት ነው።ወንዲሁም ከማንኛውም ኃጢያት የተለየ ነው። እኛም እግዚአብሔር ለመምሰል ከፈለግን ልንመስለው የሚገባውም የምንችለውም ጽድቁንና ቅድስናውን ነው። እንደቃሉ ስንሄድ፥ ከአለም ስንለይ እግዚአብሔርን በመምሰል እያደግን መሄድ እንችላለን።
- ኤፌ 5፡9 ጽድቅ የብርሃን ፍሬ ነው። በጨለማ ውስጥ ሰው ሳይሰናከል መራመድ አይችልም። በእግዚአብሔር ፈቃድ በመኖር፥ ጽድቅን የምናደርገው ከእግዚአብሔር ብርሃን የተነሳ ብቻ ነው። የቃሉን ብርሃን በእየለቱ ስንቀበል፥ ከእግዚብሔር ጋር በጸሎት፥ ከቅዱሳን ጋር በህብረት ስንመላለስ፥ ጽድቅን መለማመድ እንችላለን።
- ኤፌ 5፡9 የብርሃን ፍሬ የሆኑትን ሲዘረዝር ጽድቅን ከበጎነትና ከእውነት ጋር ያያይዛል። በጎነት ለሌሎች የሚጠቅም ነገር ማድረግ ነው። ባለፈው እንዳየነው እውነተ ደግሞ በሌሎች ፊት እውነተኛ መሆን ነው። "ጽድቅ" የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ነው። ስለዚህ የምናደርገው በጎነት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ

የሆነውን እንጂ ሰዎችን ለማስደሰት ብለን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚቃረንን ነገር አይደለም። እውነተኛም እንሁን ሲባል የሥጋችንን ፍላጎት እሺ እያልን፥ ኃጢያትን በግልጥ መለማመድ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ጽድቅ/ፈቃድ ሳናስመስል መኖር ነው።

- በኢሳ 11፡5 ላይ ጽድቅ የመሲሁ የጎን መታጠቂያ ሲሆን በዚህ ክፍል ደግሞ ጥሩር ይለዋል። ይህ የሚያሳየን ዋና መልዕክቱ ስዕላዊው መግለጫው ሳይሆን “ጽድቅ” ነው። የኢሳ 11፡5 ዋና መልዕክት መሲሁ ጻድቅ መሆኑን ነው። መሲሁ ኢየሱስ ጻድቅ እንደሆነ እኛም ጻድቅ እንድንሆን ታዘናል። እርሱ ባሸነፈበት መሳርያ እንድንዋጋ የሚያዘን፥ እንደእርሱ በድል እንደምናሸንፍ ስለሚያውቅ ነው።

**የመወያያ ጥያቄዎች (እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ማብራሪያውን ማንበብ ጥሩ ይሆናል)**

1. ኤፌ 6፡14-15፣ ሮሜ 4፡20-25፣ 10፡10፣ በማንበብ ጽድቅ ስንት ገጽታዎች እንዳሉት ተነጋገሩ። ጽድቅን ልበሱት የሚለውን አሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ?
2. በ1ኛ ዮሐ 2፡29 እና በ1ኛ ዮሐ 3፡7 እንዲሁም በ1ኛ ዮሐ 3፡10 መሰረት ስለሁለተኛው የጽድቅ ገጽታ ምንነት ተነጋገሩ። ምን እንማራለን?
3. በኤፌ 4፡24 ጽድቅ እውነተኛ ነው (በድሮው ‘ለእውነት ነው’) ማለት ምን ማለት ነው? ባለፈው ጥናት እንዳየነው ጽድቅ ከእውነተኛነት ጋር ምን ያገናኘዋል?
4. ኤፌ 4፡24 ጽድቅና ቅድስና ትርጉማቸውንና ግንኙነታቸው ተነጋገሩ። ጽድቅና ቅድስና እግዚአብሔርን ለመምሰል እንዴት ይረዱናል?
5. ኤፌ 5፡9 ጽድቅ “የብርሃን ፍሬ” የተባለው ለምንድ ነው? ብርሃን እንዴት ነው ጽድቅን የሚያፈራው?
6. ኤፌ 5፡9 “የብርሃን ፍሬ” የሆኑትን ሲዘረዝር ጽድቅን ከበጎነት እና ከእውነት ጋር ማያያዙ ምን መልዕክት አለው?

7. በኢሳ 11፡5 ላይ ጽድቅ የመሲሁ "የጎን መታጠቂያ" ሲሆን በኤፌ 6:14 ደግሞ የአማኙ "ጥሩር" ይላል። ሁለቱ መሲሁ የለበሰውን እንድንለብስ መታዘዛችን ምን ትርጉም ሊሰጠን ይገባል?
8. ከዛሬው ጥናት አሳብ ስለ ጽድቅ ገጽታዎችና ጽድቅን ስለ መልበስ ምን ተማርን? የብርሃን ፍሬ እንድናፈራም እንጸልያለን።

**መደምደምያ፡-**

ክርስቶስን በማመን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቀናል። ይህን ሁል ጊዜ ልናምን፥ አጥብቀን ልንይዝ ይገባል። ነገር ግን በዚህ እውነት ላይ ቆመን፥ የጽድቅን ህይወት ልንኖር ደግሞ ይገባል።

## ጥናት አስራ ዘጠኝ

**የንባብ ክፍል፡-** ኤፌሶን 6፡15

**ርዕስ**፡- እቃ ጦር ሦስት "ወንጌል"

**ዓላማ፡-**ያመንነውና የዳንበት ወንጌል ምን እንደሆነ ለማስታወስና አጥብቀን ይዘን ሌሌሎችም ለመናገር ዝግጁ እንድንሆን ለማሳሰብ

**መግቢያ፡** "ወንጌል" ሦስተኛው የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር ነው። ክርስቶስ ራሱ ወንጌልን እንደሰበከ እና የሰበከውም ወንጌል ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሳይሆን ከሰውም ጋር እንዳስታረቀ እናያለን።ስለዚህ እንደሌሎቹ የጦር ዕቃዎች ወንጌልም ሁለት ገጽታ ያለው የጦር ዕቃ ነው።

**ማብራሪያ፡**

1. በኤፌ 1፡13 እነርሱ የሰሙትን ወንጌል "የመዳን ወንጌል" ይለዋል።በዚህ ክፍል (ኤፌ 1፡3-14) መዳን የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፥ የበደልን ስርየት ማግኘት ወዘተ ያካትታል። በወንጌሉ እንዲድኑ ከእነርሱ የሚጠበቀው ወንጌሉን አምኖ መቀበል

ነው። አምነው ሲቀበሉ፥ የመዳናቸው ማረጋገጫ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ይታተማሉ።

2. በኤፌ 2፡14-18 ኢየሱስ የሰበከውን የሰላም ወንጌል ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ደግሞም ሰውን ከሰው ጋር የሚያስታርቅ የሰላም ወንጌል ነው። በመካከላቸው የነበረውን ግድግዳ በክርስቶስ ሞት መፍረሱን የሚያበስር ወንጌል ነው።
3. በኤፌ 6፡15 ይህንን ወንጌል ደግሞ የሰላም ወንጌል በማለቱ ያረጋግጣል።
4. ኢሳ 52:7 "የምስራች የሚናገር፥ ሰላምንም የሚያወራ፥ የመልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገር፥ መድኃኒትንም የሚያወራ፥ ጽዮንንም አምላክሽ ነግሦአል የሚል ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው።" በዚህ ክፍል መሰረት "እግር" የምስራች ነጋሪ፥ የመልክተኛ ምልክት ነው።
5. በኤፌ 6፡15 እግርን በሰላም ወንጌል መጫማት የሰላምን ወንጌል ለመናገር ዝግጁ መሆን ነው። መጫማታችንን የምናውቀው አሁን ወንጌልን ለመስበክ እድል ብናገኝ የምንሰብከውን ወንጌል ማወቅ አለማወቃችን ነው። ሁላችንም አንድ የማያምን ሰው አሁን ብንገኝ ምን ብለን እንደምንሰብክ ልናውቅ ይገባል።
6. ኤፌ 3፡6 ወንጌል አህዛብን ከአይሁድ ጋር ወራሽ፥ አንድ አካል፥ የተስፋ ተካፋይ ያደረገ ሚስጢር እንደሆነ ይናገራል። ይህ ሚስጢር ግን ሰዎች እያዩት የማይረዱት እንጂ የተሰወረ አይደለም። ኤፌ 6፡19 ወንጌል ሚስጥር እንደሆነ፥ ይህን ሚስጢር ለመግለጥ (ለማወጅ) ጳውሎስ እንደተጠራ፥ ለመናገርም የተዘጋጀ እንደሆነ ይናገራል። ሚስጢር መገለጥ ወንጌልን በመስበክ፥ በመመስከር የሚፈጸም ነው።
7. ከላይ ባጠናነው መሠረት "ወንጌል" የእግዚአብሔር የእቃ ጦር ነው የተባለው ጠላት ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያለያይ፥ እርስ በእርስ ሊያጣላ ሲል፥ ወንጌል የጠላትን ሥራ በመቃወም ሰላምን ስለሚሰብክ ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኤፌ 1፥13 እነርሱ ስለሰሙት ወንጌል ምንነት፥ ውጤቱና ወንጌሉ ከእነርሱ የሚጠብቀው ምን እንደሆነ ተነጋገሩ።
2. በኤፌ 2፥14-18 ኢየሱስ የሰበከውን የሰላም ወንጌል እንዴት ይገልጠዋል?
3. በኤፌ 6፥15 ወንጌሉን የሰላም ወንጌል ማለቱ ምን እንድናስብና እንድናደርግ ያስተምረናል?
4. ኢሳ 52:7 በመግቢያው በተብራራው መሰረት እግር የምን ምልክት ነው? ለእኛስ ምን ያስተምረናል?
5. በኤፌ 6፥15 እግርን "በሰላም ወንጌል" መጫማት ምን ማለት እንደሆነ ከቃሉና ከጥናቱ ማብራሪያ በመመልከት ተነጋገሩ።
6. ኤፌ 3፥6 እና 6፥19 ስለወንጌል ምን እንማራለን? ሐዋ ጳውሎስ የወንጌል ሚስጥር የሚለው ምኑን ነው?
7. ኤፌ 2:11-18 በማንበብ ይህ ሰላም እንዴት እንደመጣ ተነጋገሩ።
8. በዚህ ጥናት መሠረት ባጠቃላይ "ወንጌል" የእግዚአብሔር የእቃ ጦር ነው የተባለው ለምንድ ነው?

**መደምደምያ፡** ወንጌል ከእግዚአብሔር ጋር የተታረቅነበት ብቻ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቁት ሁሉ ጋር የታረቅንበትና አንድ ቤተሰብ፥ አንድ አካል፥ አንድ ቤተ መቅደስ የሆነበት የክርስቶስ ሥራ ነው።

## ጥናት ሀያ

**የንባብ ክፍል፡-** ኤፌሶን 6፡16

**ርዕስ**፡-አራተኛው የእግዚአብሔር የእቃ ጦር "እምነት"

**ዓላማ፡-**እምነት በእግዚአብሔር ላይ ያለን መደግፍና ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሃይማኖትም (ትምህርት) መሆኑን ለማስገንዘብ።

***መግቢያ፡-***በዚህ ጥናት አራተኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር እናያለን። ይህም እምነት ነው። እምነት በዋነኝነት በክርስትስ ላይ፥ እርሱ ብቻ ሰርቶ በጨረሰው ሥራ ላይ ያለንን መደገፍ የሚያሳይ ነው። ጌታን ስንቀበል የምናደርገው ብቻ ሳይሆን፥ ሁል ጊዜ የምንኖርበት የህይወት ውሳኔ እንደሆነ እናያለን። እንደሌሎቹ የእግዚአብሔር ዕቃ ጦሮች ሁሉ ሁለት ገጽታ አለው። የመጀመሪያው ገጽታ እግዚአብሔር ላይ ያለን መታመን/መደገፍ ሲሆን ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሃይማኖት (ትምህርት) ነው። ማለትም በየቀኑ እንድንኖር የታዘዝንበት የህይወት ፍሬ ነው።

***ማብራሪያ፡*** ኤፌ 1፡15 "በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለ ማመን . . . ሰምቼ" ሲል በጌታ ኢየሱስ ማመን ጌታ ኢየሱስን ለመከተል መወሰን ነው። ሌሎች አማልክትን ትቶ እርሱን እውነተኛ አምላክና አዳን አድርጎ መቀበል ነው። ባለፈው ጥናት ስለወንጌል አይተናል። ወንጌል ክርስቶስን አምላክ እንደሆነና አምላክ የሆነው እርሱ ሰው ሆኖ መጥቶ ለእኛ ኃጢያት እንደሞተና ከሙታን እንደተነሳ ይነግረናል። ስለዚህ እምነት ይህን የወንጌልን ምስራች መቀበል ነው።

1. በኤፌ 2፡8 መሠረት የምንድነው በጸጋ ነው። ጸጋ ደግሞ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ እና እኛ ምንም አስተዋፅዖ ያላደረግንበት ነገር ነው። ነገር ግን ደህንነትን የምናገኘው ይህን ጸጋ በእምነት ስንቀበል ነው። እምነት እግዚአብሔር የሰጠንን ነጻ ስጦታ እጅን ዘርግቶ መቀበል ነው።
2. በኤፌ 3፡12 እምነት ወደ እግዚአብሔር መገኘት የምንገባበት፥ እግዚአብሔርን ለማምለክም ሆነ ለጸሎት ፊቱ የምንቀርብበት መንገድ ነው። እምነት እግዚአብሔር

እኛን በክርስቶስ ሥራ እንደተቀበለን ማመን ስለሆነ፥ በኃጢአት ተከስን እንዳንፈራ ድፍረት ይሰጠናል። ድፍረታችን በሥራችን ሳይሆን፥ ባለቀው የክርስቶስ ሥራ ነው። እምነት ድፍረት አይደለም፥ ነገር ግን ድፍረትን ይወልዳል።

3. ኤፌ 3፡17 "ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር" ሲል "እንዲኖር" የሚለው ክርስቶስን በልባችን መኖርን እንዲቀጥል እንጂ ገና እንዲገባ አይደለም። ስናምን ክርስቶስን በልባችን ገብቶአል። ክርስቶስ ወደ ልባችን እንዲገባ እንዳመነው፥ እንዲሁ ደግሞ በልባችን መኖርን እንዲቀጥል እምነታችንን አጥብቀን ልንይዝ ይገባል። እምነት መጀመሪያችንም መጨረሻችንም ነው።
4. ኤፌ 4፡5 "አንድ ጌታ፥ አንድ እምነት፥ አንድ ጥምቀት" ይላል። በዚህ ክፍል "እምነት" ከጌታና ከሐዋርያቱ የተቀበልነው ትምህርት ወይም ሃይማኖት ነው። ይሁዳ ቁ. 3 "ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ ተሰጠው እምነት" (አዲሱ መደብኛ) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።
5. በኤፌ 4፡13 እንደተገለጠው ሁላችንም የሚኖረን እምነት አንዱ ክርስቶስ ላይ መሆን እንዳለበትና በዚህም አንድ ወደ መሆን ልንደርስ እንደሚገባን ይነግረናል።እምነታችን በምናውቀው ልክ ስለሚወሰን፥ ክርስቶስን እንደቃሉ ሁላችንም እኩል አውቀን፥ እኩል ወደምናምንበት እንድንደርስ ይነግረናል።
6. ኤፌ 6፡16 "የጠላት ፍላጻ" የሚለው ጠላት ወደ ሰው አይምሮ የሚወረውረውን ፍርሃትን፥ ጥርጣሬን ለማምጣት የሚወረውረውን ሃሳብ ነው። እምነት የጠላትን ፍላጻ የሚያጠፋው ፍርሃትን በድፍረት፥ ጥርጣሬን በሙሉ ልብ ወዘተ እየቀረ ነው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ኤፌ 1፡15 "በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለ ማመን . . . ሰምቼ" ሲል "በጌታ ኢየሱስ ማመን" ማለት ምን ማለት ነው? ከባለፈው ጥናት ጋር በማያያዝ ይህን ጥያቄ በዝርዝር ተነጋገሩበት።
2. በኤፌ 2፡8 መሠረት ለደህንነት <u>**የእምነትና የጸጋ**</u> ድርሻ ምንድነው? ልዩነታቸውና ግንኙነታቸውን ተነጋገሩ።

3. በኤፌ 3፥12 የተገለጠውን “የእምነት” ጥቅም ምንድን ነው? እምነት እና ድፍረት እንዴት እንደሚገናኙና እንደሚለያዩ አስረዱ።
4. ኤፌ 3፥17 “ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር” ሲል “እንዲኖር” ማለት ምን ማለት ነው? ክርስቶስ ወደ ልባችን እንዲገባ ያመነው እምነት፥ በልባችን እንዲኖር ከሚያደርገው እምነት ጋር ያለውን ግንኙነት ተነጋገሩ።
5. በኤፌ 4፥5 እና ይሁዳ ቁ.3ን በመመልከት ለቅዱሳን የተሰጠው እምነት ምን ዓይነት እንደሆነ አብራሩ።
6. በኤፌ 4፥13 የተገለጠውን የእምነት አንድነት ከክፍሉ በመነሳት አብራሩ።
7. ኤፌ 6፥16 የጠላት ፍላጻ ምንድን ነው? እምነት እንዴት ነው የጠላትን ፍላጻ የሚያጠፋው?
8. ከዛሬው ጥናት አሳብ እምነት ከመዳናችን ጀምሮ በየቀኑ ለምንኖረው ኑሮ ስለሚኖረው አስተዋጾ ምን ያስተምረናል?

***መደምደምያ፡-***

“ጻዲቅ በእምነት በህይወት ይኖራል” ተብሎ እንደተጻፈ፥ እምነት በክርስትና ህይወት መጀመሪያ ብቻ ሳይሆን፥ከመጀሪያው እስከመጨረሻ ሊኖረን የሚገባ የህይወት ውሳኔ ነው።ስለዚህ እምነታችንን አጥበቀን ልንይዝ፥ ደግሞም ልናሳድገው ይገባል።

**ጥናት ሃያ አንድ**

**የንባብ ክፍል፦** ኤፌሶን 6፡17

**ርዕስ፦** እቃ ጦር አምስት፡ "የእግዚአብሔር ቃል"

**ዓላማ፡- በመንፈሳዊ** ውጊያ ሰዓት ጠላትን የምናሸንፍበት አንዱ መንፈሳዊ መሳሪያ "የእግዚአብሔር ቃል" ማለትም እግዚአብሔር እንደሚስጠን ለማስገንዘብ

**መግቢያ፡-** ይህ ጥናት ከእግዚአብሔር ጦር ዕቃዎች መካከል በመጨረሻ የተጠቀሰውን "የእግዚአብሔርን ቃል" እናያለን። በተጨማሪም ይህ የጦር ዕቃ በውጊያ ሰዓት ለመከላከያም ለማጥቂያም እንደሚጠቅም እናጠናለን።እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል በውጊያ ቀን ጠላትን ሸንገላውን የምናሸንፍበት መሣሪያ መሆኑን እናያለን።

**ማብራሪያ፡-**

1. "የመዳን ራስ ቁር"፡- የእግዚአብሔር ቃል "የመዳን ራስ ቁር" ነው ማለት መጀመሪያም ደህንነትን ያገኘንበት፥ አሁንም የምንድንበት ነው ማለት ነው። መዳን አንዱ ትርጉሙ ከጠላት መንግሥት መውጣት ነው። እግዚአብሔር ከዲያቢሎስ መንግሥት እኛን ያወጣን በቃሉ ነው።
2. የእግዚአብሔር ቃል "የመንፈስ ሰይፍ" ነው ሲል ስይፍነቱ በዋነኝነት በዲያቢሎስና በሰራዊቱ ላይ ነው። የመንፈስ ስይፍ የተባለበት መንፈስ ቅዱስ ራሱ የሚሰጠን ስለሆነ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የመንፈስ ቅዱስ ቃል ነው። ሰይፍ ሲባል ግን ዲያቢሎስ በሰይፍ ይሞታል ሳይሆን ስራው ይከሽፋል ማለት ነው። ዲያቢሎስ መንፈስ ስለሆነ አይሞትም። ነገር ግን በሰይፍ ይሸነፋል፥ ስራው ከንቱ ይሆናል።
3. በዕብ 4፡12 "የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤" ይላል። ይህም፥ የእግዚአብሔር ቃል ሰይፍነቱ በዲያቢሎስ ላይ ብቻ ሳይሆን በእኛም ላይ መሆኑን ያሳያል። ሰይፉ በእኛ የሚያደርገውና በዲያቢሎስ የሚያደርገው ግን ይለያያል። በእኛ ህይወት ሲሰራ ውስጣችንን ገልጦ ያሳየናል፣ወደ ንስሃ ይመራናል። ይህም ሲሆን፥ ጠላት በእኛ ዘንድ እንድል ፈንታ እንዳይኖረው ያደርጋል።

4. በዚህ ክፍል “የእግዚአብሔር ቃል” የሚለው በግሪኩ “ሬማ (Rhema)” ነው። በማቴ 4፡4 ኢየሱስ “4 እርሱም መልሶ። ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል (ሬማ) ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።” “ሬማ” ማለት ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ለጊዜ የሚሆነውን፥ አሁን እግዚአብሔር እንደተናገረን አድርጎ ሲያቀብልን ነው። በማቴ 4፡1-11 ያለውን የኢየሱስን ምሳሌ እንደምናየው፥ የእግዚአብሔር ቃል በሬማ መልኩ መምጣት በፈተና ሰዓት ለጠላት ሽንገላ፥ ፈተና ትክክለኛውን ምላሽ የምንሰጥበትን፥ የምናሸንበትን፥ ፈተናውን የምናልፍበትን መንገድ እግዚአብሔር ይሰጠናል።
5. ስለ ‘ሬማ (Rhema)’ ከተነጋገርነው አንጻር በምሳሌ 4፡20-21 የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን እንድንደብቅ ታዞናል (“20 ልጄ ሆይ፤ የምነግርህን አስተውል፤ቃሌንም በጥንቃቄ አድምጥ።21 ከእይታህ አታርቀው፤በልብህም ጠብቀው”)። በዚህ ክፍል በልባችን መጠበቅ ወይም መደበቅ የሚያስፈልገን፥ መቼ እንደምንጠቀምበት ስለማናውቅ ነው። በዮሐ 14፡26 እንደምናየው መንፈስ ቅዱስ የሚያስታውሰን የሰማነውን በውስጣችን ያስቀመጥነውን ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በሚያስፈልገን ጊዜ “ሬማ (Rhema)” አድርጎ እንዲያስታውሰን፥ የእኛ ድርሻ ቃሉን ማጥናት፥ ማሰላሰልና በውስጣችን መደበቅ ነው።
6. በኤፌ 5፡26 መሠረት የእግዚአብሔር ቃል አንዱ ሥራ ቤተ ክርስቲያንን ማንጻት ነው። በቃሉ የተቀደሰች ቤተ ክርስታያን፥ ለጠላት የእግሩ መርገጫ እንዲያጣ ታደርጋለች።ጠላት የሚያጠቃበትን ቀዳዳ ያጣል።
7. በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን የጦር እቃዎች መከላከያ ወይም ማጥቂያ ናቸው። መከላከያ፡ እውነት(ቀበቶ)፥ ጽድቅ (ጥሩር)፥ እምነት (ጋሻ)። ማጥቂያ፡ ወንጌል።
8. ከሌሎቹ የእግዚአብሔር የጦር ዕቃዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚለየው መከላከያም ማጥቂያም ስለሆነ ነው። ይህ የሚያሰየው የእግዚአብሔር ቃል ከጠላት የምድንበት ብቻ ሳይሆን ጠላትን የምናሸንፍበትና ከእኛ የሚሸሽበት ብቸና መንገድ መሆኑን ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል ጥናት ማብራሪያው መሠረት

1. ኤፌ 6:17 በተመለከተው መሰረት የእግዚአብሔር ቃል "የመዳን ራስ ቁር" ነው ማለት ምን ማለት ነው? ኤፌ 1፡13 ይመልከቱ።
2. በኤፌ 6:17 የእግዚአብሔር ቃል "የመንፈስ ሰይፍ" ነው ሲል ስይፍነቱ ማን ወይም ምን ላይ ነው? ለምን የመንፈስ ሰይፍ ተባለ?
3. በዕብ 4፡12 መሰረት የእግዚአብሔር ቃል ሰይፍ የሆነው ምን/ማን ላይ ነው? ከላይ ከተነጋገርነው የሚለየው እንዴት ነው?
4. ማቴ 4፡4ን ስናነብ "የእግዚአብሔር ቃል" በሬማ መልኩ መምጣት ከመንፈሳዊ ውጊያ ጋር ምን ያገናኘዋል? በማቴ 4፡1-11 ያለውን የኢየሱስን ምሳሌ በመመልከት ይህን ጥያቄ መልሱ።
5. በምሳሌ 4፡20-21 ያለው የሰው ድርሻ እና እና በዮሐ 14፡26 የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው? ይህስ የእግዚአብሔር ቃል በሚያስፈልገን ጊዜ "ሬማ" ሆኖ እንዲመጣ ያለው ድርሻ ምንድን ነው?
6. በኤፌ 5፡26፣ የእግዚአብሔር ቃል ሥራው ምንድን ነው? ይህስ ለመንፈሳዊ ውጊያ ምን ጥቅም አለው?
7. በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን የጦር እቃዎች መከላከያ ወይም ማጥቂያ በማለት እየከፋፈላከችሁ ተነጋገሩ።
8. ከሌሎቹ የእግዚአብሔር የጦር እቃዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚለየው ምንድን ነው? (መከላከያም ማጥቂያም ነው)። ይህስ ልዩነቱ ምን ያስተምረናል?
9. ከዛሬው ጥናት ስለ እግዚአብሔርን ቃል የጦር ዕቃ አድርገን ለመያዝ ምን እርምጃ መውሰድ አለብህን?

**መደምደምያ፡-**

በውጊያ ሰዓት ጠላትን የምናሸንፍበትን የጊዜውን ቃል እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲሰጠን፥ ሁል ጊዜ የምንማረውን የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን ደብቀን ልንይዘው ይገባል።

## ጥናት ሃያ ሁለት

**የንባብ ክፍል፦** ኤፌሶን 6፡18

**ርዕስ**፦ ጸሎት

**ንዑስ ርዕስ አንድ**፦ ጸሎትና ልመና

**ዓላማ፦** ጸሎት እግዚአብሔር ራሱ ውጊያችንን እንዲዋጋልን የምንጠይቅበት መንገድና ለሌሎች መማለድ በጣም አስፈላጊ ነገር መሆኑን ለማስረዳት

**መግቢያ፡** ባለፉት ተከታታይ ጥናቶች ከእግዚአብሔር ተቀብለን የምንዋጋባቸውን የጦር መሣሪያዎች አይተናል። በዚህና በሚቀጥሉት የመጨረሻ ሁለት ጥናቶች ስለጸሎት እናያለን። ጸሎት በመንፈሳዊ ውጊያ ያለውን ድርሻ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጦር ዕቃዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ወይም ልዩነት እናያለን። የዚህ ጥናት መነሻ የአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው። ኤፌ 6፡16 "በሁሉ ዐይነት ጸሎትና ልመና፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤"

**ማብራሪያ፡**

1. "በሁሉ ዐይነት ጸሎት" እንዲጸልዩ ያዛል። "ሁሉ ዐይነት" ካለ ብዙ ዓይነት ጸሎት አለ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ካሉ ጸሎቶች መካከል፡ ለቅሶ፥ ንስሃ፥ ለፍትህ፥ ለፈውስ፥ የግልና የጋራ ወዘተ ዓይነት ጸሎቶች ይገኛሉ። በማቴዎስ 6፡9-13 ከተዘረዘሩት ጸሎቶች ጥቂቶቹ፡የእግዚአብሔር ፈቃድ በህይወታችን፥ በምድር እንዲሆን፥ ንስሃ፥ ስለ ዕለት እንጀራ፥ ወደ ፈተና እንዳንገባ መጸለይ ይገኙበታል።
2. ልመና በተለምዶ ስለራስ ርዳታ መጠየቅ ቢሆንም፥ ስለሌሎች ጸሎትን ማድረግ በጣም ተገቢ ነው። ስለቤተሰብ፥ ስለሀገር፥ ስለመሪዎች ወዘተ መጸለይ ነው።
3. "በማንኛው ሁኔታ" ወይም "ዘወትር" እንድንጸልይ ታዘናል። ሁኔታዎች ይቀያየራሉ። ጊዜ ይለዋወጣል። ሁኔታዎችም ሆነ ጊዜ ቢቀያየርም፥ ጸሎትና ልመና ማቅረብ የማያስፈልግበት ጊዜ የለም። ከኤፌ 1፡15-16 ከጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች ሁል ጊዜ ይጸልያል። ሁሌ የሚጸልየው፥ ሁሌ ስለሚያስባቸው ነው። ሁሌ የሚያስባቸው ስለሚወዳቸው ነው። የሚወዳቸው ደግሞ በጌታ ስለሆኑ፥ ቤተሰቦች ስለሆኑ ነው።

4. በኤፌ 3፡14-21 ጳውሎስ ስለጸሎት ያለው አመለካከትና ልምምዱን ማየት እንችላለን። ሲጸልይ ተንበርክኮ ይጸልያል። እግዚአብሔር ከጠየቅነውና ካሰብነው በላይ እንደሚሰራ ያምናል። እግዚአብሔርን ያመሰግናል።
5. በመንፈስ መጸለይ ማለት በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ርዳት መጸለይ ማለት ነው። ይሁዳ ቁ.20 በመንፈስ ቅዱስ ጸልዩ ይላል። ሮሜ 8፡26 መጸለይ ስለማንችል፥ መንፈስ ቅዱስ ለጸሎት እንደሚረዳን፥ እርሱ በውስጣችን እንደሚቃትት ይነግረናል። ስለምን እና እንዴት መጸለይ እንዳለብን ያስታውቀናል።
6. ኤፌ 5፡18-20 በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ ያዘናል። በመንፈስ ቅዱስ እንድሞላ እርስ በእርሳችን በመንፈሳዊ ቅኔ ልንነጋገር፣ ልንዘምር፣ ልናመሰግን፣ ለእርስ በእርሳችን ልንገዛ እንደሚገባን ይነግረናል። ይህን ስናደርግ መንፈስ ቅዱስን እንደ አዲስ እንቀበላለን ማለት ሳይሆን፥ በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላን፥ እንዲቆጣጠረን ይረዳናል ማለት ነው። ሲሞላን ደግሞ መልሰን እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንችላለን።
7. ጸሎት የእቃ ጦር አይደለም። እስካሁን የተዘረዘሩት የዕቃ ጦሮች ሁሉ በጦር መሣሪያ ተመስለዋል። ጸሎት በጦር መሣሪያ አልተመሰለም። ይህ የሚያሳየው በጸሎት ውስጥ እኛ ሳንሆን የምንዋጋው እግዚአብሔር ራሱ እንዲዋጋልን ለእርሱ ውጊያችንን አሳልፈን የምንሰጥበት መንገድ ነው።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በኤፌ 6:18 "በሁሉ ዓይነት ጸሎት" እንዲጸልዩ ያዛል። በማብራሪያው የተጠቀሱትንና የምታውቋቸውን የጸሎት አይነቶች ዘርዝሩ። በማቴዎስ 6፡9-13 የተዘረዘሩትን እንደመነሻ ማየት ይቻላል።
2. በማብራሪያው መሠረት ልመናና ጸሎት የሚደረገው ለማን ነው?
3. "በማንኛው ሁኔታ" ወይም "ዘወትር" እንድንጸልይ ታዘናል። ይህ እንዴት ይቻላል? ከኤፌ 1፡15-16 ከጳውሎስ ህይወት ምን እንማራለን?
4. በኤፌ 3፡14-21 ከጳውሎስ ስለ ጸሎት ካለው አመለካከትና ልምምድ የተረዳችሁትን ተከፋፈሉ።

5. በመንፈስ መጸለይ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ነው በመንፈስ መጸለይ የሚቻለው? ሮሜ 8፡26 እና ይሁዳ 20 በማጣቀስ ተነጋገሩ።
6. "መንፈስ ይሙላባችሁ" (ኤፌ 5፡18-20) የሚለው ትዕዛዝ በመንፈስ ለመጸለይ እንዴት ይረዳል? በመንፈስ እንዴት ነው የምንሞላው?
7. ጸሎት በጦር መሣሪያ አለተመሰለም። ይህ ለምን ይሆን? ማብራሪያውን መመልከት ትችላላችሁ
8. ከዛሬው ጥናት ስለ ጸሎት ዓይነቶችና አስፈላግነት የቀረላችሁን አካፍሉና የጸሎት ጊዜ ውሰዱ።

***መደምደምያ፡-*** ጸሎት መንፈሳዊ ውጊያን፣ራሳችንንና ሌሎችን ለእግዚአብሔር ለራሱ አሳልፈን የምንሰጥበት፥ እግዚአብሔር ራሱ እንዲዋጋል የምንጠይቅበት መንገድ ነው።

## ጥናት ሀያ ሦስት

**የንባብ ክፍል፡-** ኤፌሶን 6፡18-20

**ርዕስ**፡- ጸሎት

**ንዑስ ርዕስ ሁለት**፡- ለቅዱሳንና ለወንጌል መስፋፋት መጸለይ

**ዓላማ፡**ለቅዱሳን ሁሉ እና ለወንጌል መስፋፋት ለሚተጉና ዋጋ ለሚከፍሉ እንድንጸልይ ለማሳሰብ

***መግቢያ፡*** በዚህ ጥናት ባለፈው ስለ ጸሎት የጀመርነውን እንቀጥላለን። በዚህ ጥናት የምናየው ስለ ቅዱሳንና በተለይም ደግሞ ለወንጌል መስፋፋት ተለይተው የሚያገለግሉትንና ዋጋ ስለሚከፍሉት መጸለይ የቃሉ ትምህርት እንደሆነ እናያለን። ከተቻለ ለዚህ ጥናት የምንጠቀመው አዲሱን መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆን ይመረጣል። ኤፌ 6፡18-20 "ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ።19 የወንጌልን ምስጢር ለመግለጥ አፌን በምከፍትበት ጊዜ ሁሉ በድፍረት

እንድናገር ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ጸልዩልኝ። 20በሰንሰለት የታሰረ መልእክተኛ የሆንሁት ለዚሁ ነውና። ስለዚህ መናገር የሚገባኝን ያለ ፍርሀት እንድናገር ጸልዩልኝ።”

**ማብራሪያ፡**

1. “ይህንም በማሰብ” ሲል በቁጥር 18 ላይ ስለጸሎትና ልመና የተናገረውን ነው። በመንፈስ፥ ሁል ጊዜ ለራሳቸው መጸለይ ብቻ ሳይሆን፥ ለሌሎች መለመንም እንዳለባቸው ተናግሯል። ከዚህ በኋላ የሚያወራውን በዚህ ላይ መስርቶ መሆኑን ለመናገር ነው።
2. ንቁ” ሲል መንፈሳዊ አይናችሁን ከፍታችሁ፥ በመንፈሳዊው አለም እየሆነ ያለውን፥ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንዲያዩ ነው። ለመንፈስ ቅዱስ ድምጽ፥ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ሊመጣ ያለውንም ሆነ አሁን በመንፈሳዊ አለም እየሆነ ያለውን ሁሉ ለራሳችን ሊናገረን/ሊያሳየን ይችላል። በገዛ ብርታታችን የምናደርገው ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ለሚያደርገው ነገር ራሳችንን እንድንሰጥ የሚያደርግ ነው።
3. ከመንፈሳዊ ውጊያ አንጻር ለሌሎች መጸለይ ያለብን ምንክንያት አንድ አካል ስለሆንን ነው። እነርሱን የሚያገኝ፥ ያገኘናል። አንዱ በውጊያ ሲወድቅ፥ ሁላችንም መነቀፋችን አይቀርም። እንደ አንድ አካል፥ የአንዱ ጥቃት፥ የሌላው ጥቃት ነው ብለን ልንወስድ ይገባል። የጠላትም ዋና ግቡ ግለሰብን ሳይሆን ቤተ ክርስትያያንን ማጥቃት ነው።
4. “በትጋት ልመና አቅርቡ” ወይም “እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ” የሚለው ስለሌሎች ስንጸልይ ልንታክት እንደምንችል ያሳያል። ለራሳችን መልስ እስከናገኝ ልንጸልይ እንችላለን። ሌሎችን ግን ጥቂት ጊዜ ጸልየን ልናቆም እንችላለን። ለልመና ትጋት ያስፈልጋል።ለልመና መልስ አለ። መልሱ እንዲመጣ ግን በትጋት ልንጸልይ ይገባል። “እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ፥ ኢየሩሳሌምን እስኪያጸና በምድርም ላይ ምስጋና እስኪያደርጋት ድረስ አትረፉ ለእርሱም ዕረፍት አትስጡ።” (ኢሳ 62፡ 7)።
5. ሐዋርያ ጳውሎስ ወንጌል ለመናገር አፉ ለመከፈት ወስኗል። ጸሎት የጠየቀው ለዚህ አይደለም። ጸሎት የፈለገበት ጉዳይ አፉ ሲከፈት የሚናገረው እንዲሰጠው ነው።

መልዕክቱ ወንጌል ቢሆንም፥ ያንን ወንጌል ለሰሚው በሚገባ መንገድ ለማስረዳት የጌታ እርዳታ እንደሚያስፈልገው አምኗል።

6. ሐዋርያ ጳውሎስ የወንጌልን ሚሲጢር ለአህዛብ ሲገልጥ፥ በመንፈሳዊ ውጊያ እየተዋጋ እንዳለ ያምናል። ምክንያቱም በወንጌል አህዛብን ከሰይጣን ግዛት ስየሚያወጣ አምላክ የሆነው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው። በኤፌ 3፡8-10 እንደምናየው ወንጌል ለአህዛብ ከሰበከ በኋላ አህዛብ በቤተ ክርስትያን አካል ውስጥ ሲገቡ፥ በሰማያዊ ስፍራ ላሉ የዲያቢሎስ ሰራዊቶች ሁሉ ይታያል።
7. ሐዋርያው ጳውሎስ "ቃል" እንዲሰጠኝ ሲል የእግዚአብሔር ቃል ማለቱ ሳይሆን፥ ወንጌል ለማስረዳት የሚጠቀምበትን የራሱን ንግግር እግዚአብሔር ራሱ እንዲሰጠው፥ አንደበቱን እንዲቆጣጠር ወይም የጊዜው የሆነውን የማስረዳት ችሎታ ማለቱ ነው።
8. ኤፌ 6:20 "በሰንሰለት የታሰረ መልእክተኛ የሆንሁት ለዚሁ ነውና። ስለዚህ መናገር የሚገባኝን ያለ ፍርሀት እንድናገር ጸልዩልኝ"። ሰንሰለት ጠላት የሚዋጋበት አንዱ መንገድ ነው። የመንፈሳዊ ውጊያ መገለጫ ነው። በአገልጋዮችና በአማኞች ዘንድ ፍርሃትን ለመፍጠር፥ ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ ለማድረግ ይጠቀምበታል። ጳውሎስ ስንሰለትን የደምና የስጋ ሥራ ሳይሆን፥ በዋነኝነት ከዲያቢሎስ የሚመጣ፥ ስጋ ለባሽን በመጠቀም የሚዋጋበት መንገድ እንደሆነ ያሳያል። ቢታሰርም ወንጌልን ለመናገር እንዳይፈራ እንዲጸልዩለት ይጠይቃል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በዚህ ጥናት ማብራሪያ መሠረት በኤፌ 6:18 ላይ "ይህንም በማሰብ" የሚለው የሚያመለክተው ስለምንድን ነው?
2. ኤፌ 6:18 ላይ "ንቁ" ብሎ ሲያዛቸው መንቃት ከጸሎትጋር የሚያይዘው እንዴት ነው? እንዴት መንቃት ይቻላል?
3. ከመንፈሳዊ ውጊያ አንጻር ለሌሎች መጸለይ ያለብን ለምንድን ነው? ከዮሐ.17:9-12 ጋር ምን ግንኙነት አለው?

4. በዚሁ ቁጥር ላይ “በትጋት ልመና አቅርቡ” ወይም “እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ” ሲል በልመና መትጋት/መጽናት ለምን አስፈለገ?
5. ኤፌ 6:19 መሠረት ጳውሎስ ወገኖች እንዲጸልዩለት የፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው? እኛስ ከዚህ ምን እንማራለን?
6. ኤፌ 6፡19- እና 3፡8-10 በማየት “የወንጌልን ሚሲጢር” መግለጥ ከመንፈሳዊ ውጊያ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
7. ኤፌ 6:19 ላይ ሐዋርያው “ቃል” እንዲሰጠኝ ሲል ምን ማለቱ ነው?
8. ሰንሰለት በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ቦታው ምንድን ነው? በአገልጋዮችና በአማኞች ዘንድ ምን ሊፈጥር ይችላል? ሐዋርያው ከዚህ አንጻር የሚጠይቀው የጸሎት ርዕስ ምንድን ነው?
9. በዛሬ ጥናት መሰረት ቀኖቹ ክፉ ስለሆኑ ዘመኑን ለመዋጀት በመንፈሳዊ ውጊያና በጸሎት ተጋድሎ ማድረግ ስለምችልባቸው ተግባራዊ መንገዶች አካፍሉ።

***መደምደምያ፡-***

ወንጌል አንድ ጊዜ የተሰጠ የማይለወጥ እውነት ነው። ነገር ግን ወንጌልን በምንሰብክበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ለሰሚዎቹ በሚገባ መንገድ ወንጌሉን የምንገልጥበትን ቃል እንዲሰጠን ሁሌ ልንጸልይ ይገባል።